. . . እኒህ ወርቃዊና ሕያው የሕይወት ታሪክ ያላቸው ብላታ መርስዔ ኀዘን በመዘክራቸው እንደገለጹት አስተዳደጋቸውና ኑሯቸው፣ ሥራቸውም ትልቅ መምህር ሆኖ ለታዳጊ ሕፃናት መማሪያ፣ ለደቀ መዛሙርት ምሥጢር ማደላደያ፣ ለመርማሪዎች ደግሞ ትልቅ መረጃ የሚሆን ጽሑፍን ለዛን በተመላ የአጻጻፍ ዘዴ በየዓይነቱ ጽፈው አበርክተውልናል፡፡ . . .

*አቡነ መልከ ጼዴቅ*

. . . አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ያሳተመላቸው፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ፣ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922*፣ የተሰኘው መጽሐፋቸው፣ ለሁልጊዜ የሚቆይ ትልቅ ሐውልት ሆኖላቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ ይህንን፣ *ትዝታዬ፣ ስለራሴ የማስታውሰው፣* በሚል ርዕስ የጻፉትን፣ የግል ሕይወት ታሪካቸውን፣ የተባረከ ልጃቸው አቶ አምኃ መርስዔ ኀዘን በጥራት አዘጋጅቶ አቅርቦልናል፡፡ . . .

. . . ይህን መጽሐፋቸውን በእውነቱ፣ ከራሳቸውም የሕይወት ታሪክ ባሻገር፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የትምህርትና የልጅ አስተዳደግ ሥነ ሥርዓት በዝርዝር እንደሚያስተምር ትልቅ መዝገብ ልናየው እንችላለን፡፡ የንባብ ትምህርት፣ በጅሩ ገጠር በሚገኝ የአያቶቻቸው ቤተ ክርስቲያን፣ ዜማ ደግሞ፣ በድጓ መምህርነታቸው በጣም ይከበሩ በነበሩት አባታቸው፣ በአለቃ ወልደ ቂርቆስ ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር፣ ቅኔ፣ ጻድቁ አቡነ ዜና ማርቆስ ባቋቋሙት የደብረ ብሥራት ገዳም፣ እንደዚሁም የመጻሕፍት ትርጓሜ፣ ዝናቸው እስከ ቤተ መንግሥት ድረስ ከታወቀላቸው ታላላቅ መምህራን፣ የተሟላ ሥልጠና አግኝተዋል፡፡ እንደዚህ በየደረጃው ያለፉበትን የትምህርትና የመልካም አስተዳደግ መንገድ ብቻ ሳይሆን፣ በጊዜው ስለነበሩ የማኅበራዊና ጠቅላላ የሀገር ጉዳዮችም በየስፍራው ይጠቃቅሳሉ፡፡ ይልቁንም፣ በሌላ ቦታ የማይገኝ፣ ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ የትምህርት ዓይነቶችና ስለይዘታቸው የተጣራ ዝርዝር መግለጫ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ቀርቦልናል፡፡

. . .

*ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት*

. . . ብላታ ቅዱሳት መጻሕፍትና ባህል የሚያዙትን ትሕትና በተጠናቀቀ የሚጠብቁና ሰው የማይነኩ ሰላማዊ ደግ ሰው መሆናቸውን ለማወቅ ብዙ ጊዜ አይወስድም፡፡ ስለትምህርት ጓደኞቻቸው እንጂ ስለራሳቸው ጉብዝና መናገር ፈጽሞ አይሆንላቸውም፡፡ ትዝታቸውን ሳነብ የላቀ ችሎታ ያላቸው መሆኑን ያወቅሁት የየደረጃውን ትምህርት ከደረጃው አስቀድመው ሲጨርሱት በማየቴ ብቻ ሳይሆን በአንድ ሊያስወግዱት ባልቻሉት ዘገባቸው ጭምር ነው፡፡ . . . (ገጽ 118)

*ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ*

. . . የሚተርኩልኝን የተከታተልኩት በዓይነ-ሕሊናዬ እያየሁ፣ በእዝነ-ኅሊናዬ እየሰማሁና እያደመጥኩ የነበረ ይመስለኛል፡፡ ይህ ደግሞ ከተመራማሪው በተዘዋዋሪ አገኝ የነበረውን ከርሳቸው በቀጥታ ከነወዙ እንዳገኝ አድርጎኛል፡፡ . . .

. . . አንባብያንም የመርስዔ ኀዘንን መጻሕፍት እያነበቡ እንዲደሰቱ፣ እንዲገረሙ፣ እንዲቆዝሙ፣ እና እንዲማሩ በትኅትና እጋብዛለሁ፡፡ . . .

*ዶክተር ፈቃደ አዘዘ*



ብላታ መርስዔ ኅዘን በሥራ ላይ 1965 ዓ.ም.

# ትዝታዬ
# ስለራሴ የማስታውሰው

## 1891 - 1923 ዓ.ም.


## መርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ

አዘጋጅ - አምኃ መርስዔ ኅዘን

የባለቤቱ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

© by Amha Mersie Hazen, Washington, D.C.

All rights reserved.

Tezetāyé selarāsé yamāstāwesaw

Mars'é H̲ āzan Walda Qirqos

1891 - 1923

ISBN 978-0-578-02223-9

Library of Congress Control No.  2009905254

የመጽሐፉን ሽፋን ያዘጋጀው ዓለሜ ታደሰ

ይህን መጽሐፍ ለመግዛትም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ  ከታች ባለው ድረ-ገጽ

ይጠቀሙ።

www.mersie-hazen.com

Inquiries can be sent to the website listed above.



እመኒ ሐየውነ ለእግዚአብሔር ነሐዩ
ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራለን

ሮሜ ም 14 ቍ 8

## ከደራሲው

ትምህርተ ሕጻናት፣ 1917 ዓ.ም.
በአዲስ ሥርዓት የተሰናዳ የአማርኛ ሰዋስው ፣ 1935 ዓ.ም.
የአማርኛ ሰዋስው 1-2ኛ ክፍል፣ 1936 ዓ.ም.
የአማርኛ ሰዋስው መክፈቻ፣ 1936 ዓ.ም.
የትእምርተ መንግሥት ታሪክ፣ 1936 ዓ.ም.
የቤተ ክርስቲያን ዜና መጀመሪያ ቍጥር፣ 1938 ዓ.ም.
ግ ን ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጕንደርን የመጐብኘታቸው ታሪክ፣ 1939 ዓ.ም.
ዐውደ መዋዕል፣ 1939 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ መዝገበ ዕለታት፣ 1939 ዓ.ም.
የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዕረፍት መታሰቢያ፣1940 ዓ.ም.
ሢመተ ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ፣ 1942 ዓ.ም.
የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ፣ 1956 ዓ.ም.
የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣1999 ዓ.ም.

### *ትርጉም ሥራ - አዘጋጅተው ያሳተሙዋቸው መጻሕፍት*

ጥበብን መፈለግ 1-3ኛ መጽሐፍ፣ 1946 ዓ.ም.
ሔሮዶቱስ የጥንት ታሪክ 1-4ኛ መጽሐፍ፣ 1948 ዓ.ም.

### *ጽሑፎችን ሰብስበው ያዘጋጁዋቸውና የታተሙ መጻሕፍት*

ፍሬ ከናፍር ዘቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን.ነ. ዘኢትዮጵያ 1-7ኛ መጽሐፍ፣
1944 - 1964 ዓ.ም.

### *ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተዘጋጁ የቅዱሳት መጻሕፍት ሥራዎች፡፡*

መቅድመ ወንጌል ንባብና ትርጓሜው፣ 1920 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዜና፣ 1938 ዓ.ም.

### *ከሊቃውንት ጋር የተሠሩ*

አረጋዊ መንፈሳዊ ንባብና ትርጓሜ፣ 1922 ዓ.ም.
መጽሐፈ ሲራክ፣ 1914 ዓ.ም.
ሰባዓቱ ኪዳናት፣ 1917 ዓ.ም.
የቤተ ክርስቲያን ጸሎት በግዕዝና በአማርኛ፣ 1942 ዓ.ም.
መጽሐፈ ቅዳሴ በግዕዝና በአማርኛ፣ 1918 ዓ.ም.
The Liturgy of the Ethiopian Church, 1959
(Translated by Rev. Marcos Daoud, Revised by H.E. Blatta Marse Hazen)

### *በኮሚቴ የተሠሩ*

መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ በብላታ መርስዔ ኀዘን ሊቀ መንበርነት 1939 - 53 ዓ.ም.
በኮሚቴ ተሠርቶ የታተመ፡፡
ፍትሐ ነገሥት በግዕዝና በአማርኛ በብላታ መርስዔ ኀዘን ሊቀ መንበርነት
ከ1962 - 63 ዓ.ም. በኮሚቴ ተሠርቶ የታተመ፡፡

### *ያልታተሙ፡፡*

የዘመን ታሪክ ትዝታዬ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከፊል ታሪክ
የዘመናት ማገናዘቢያ፣ ዓመተ ምሕረት፣ ዓመተ ዩልዮስ፣ ዓመተ ሰማዕታት፣ ዓመተ ተንባላት፡፡
በአንኮበር ከተማ የሸዋን ነገሥታት መቃብር መጐብኘት ሰኔ፣ 1937
አስማተ ሙታን፣ ለታሪክ ምርምር የሚረዳ የሙታን ማስታወሻ፡፡

በልዩ ልዩ ርዕሶች ላይ የተጻፉ አያሌ አጫጭር ጽሑፎች፡፡

## መግለጫ

«ትዝታዬ» የተባለ ይህ መጽሐፍ የሕይወት ዘመኔ በተጓዘበት የኑሮ ጎዳና ካጋጠመኝ ውስጥ ስለራሴ ያስታወስሁትን አንዳንድ ነገር የገለጽሁበት ነው፡፡ የታሪኩ መስመር የዘመኑን ተራ የሚከተል ሆኖ ሳለ አንዳንድ ጊዜ የወደኋላ የታሪክ ሐተታ ተጠቅሶበት ይገኛል፡፡

ይህ መጽሐፍ የሕይወቴን የኑሮ ጕዞ ለመግለጽ የፈተንሁበት ለባለቤቴ መታሰቢያዋ እንዲሆን ምኞቴ ነው፡፡

# ማውጫ


መግቢያ ........ 1

መቅድም ........ 5

ማስተዋወቂያ ........ 7

ምዕራፍ 1 ........ 15

የልጅነቴ ዘመን ........ 15
ስለ ተወለድሁበት ዘመንና ስፍራ ........ 15
ስለ እምቧጮ ቈላ ........ 16
ስለ መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን ........ 20
ስለ መግደላዊት ጠበል ........ 22
ስለ እመዬት በሰሙ ከማስታውሰው በጥቂቱ ........ 23
የፊደል ትምህርት ስለመጀመሬ ........ 24
አስደንጋጭ ትርኢይት እንደ ገጠመኝ ........ 28

ምዕራፍ 2 ........ 31

1896 ዓመተ ምሕረት ........ 31
መስቀለሶስ ከእናቴ ጋር ስለመቈየቴ ........ 31
ወደ አዲስ አበባ ስለመሄዴ ........ 32
በጊዜው ካየሁት የማስታውሰው ........ 34
እንጦጦ ከአባቴ ዘንድ ስለመድረሴ ........ 36

ምዕራፍ 3 ........ 38

ስለ ወላጆቼ ዜና ባጭሩ ........ 38
ስለ አባቴ ዜና ........ 38
ስለ አስተዳደጋቸውና ስለ ትምህርታቸው ........ 41
ደብረ ሊባኖስ ስለመውረዳቸው ........ 44
ወደ እንጦጦ ማርያም ስለመምጣታቸው ........ 45
እንጦጦ ማርያምን ስለመልቀቃቸው ........ 46
ቀበና አቦን ስለ መሾማቸው ........ 48
ቀበና አቦን ትተው ወደ ሀገራቸው ስለመመለሳቸው ........ 49
ስለ እናቴ ዜና ........ 50

ምዕራፍ 4 ........ 53

1897 ዓመተ ምሕረት ........ 53
ስለ ዳዊት ትምህርት ........ 53
የዜማ ስልት ለማዳመጥ እንደ ተመደብሁ ........ 54
በስሕተት ስለደረሰብኝ ቅጣት ........ 54

ምዕራፍ 5 ........ 56

1898 ዓመተ ምሕረት ........ 56
ስለ ዜማ ትምህርት ........ 56
ስለ መሬት መንቀጥቀጥ ........ 57
ክህነት ስለመቀበሌ ........ 58
ስለ ሆሳዕና በዓል ........ 60

ምዕራፍ 6 ........ 63

1899 ዓመተ ምሕረት ........ 63
የማርያምና የራጉኤል የደብር ቦታ ስለመከለሉ ........ 63
ከጃንሆይ እጅ ብር ስለመቀበሌ ........ 64

## ማውጫ


ምዕራፍ 7 ... 66

1900 ዓመተ ምሕረት ... 66
ስለ ፈንጣጣ ክትባት ... 66
ስለ አጼ ምኒልክ መታመም ... 66

ምዕራፍ 8 ... 67

1901 ዓመተ ምሕረት ... 67
ጃንሆይ ለጠበል ወደ ደብረ ሊባኖስ ስለመሄዳቸው ... 67
ወደ ጅሩ ስለመሄዴ ... 68
የቅኔ ትምህርት ስለ መጀመሬ ... 69
ምሥጢር ስለማየቱ ... 72
ወደ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ስለመሄዴ ... 73

ምዕራፍ 9 ... 75

1902 ዓመተ ምሕረት ... 75
ወደ እንጦጦ ስለመመለሴ ... 75
ጅራታም ኮከብ ስለመታየቱ ... 77

ምዕራፍ 10 ... 78

1903 ዓመተ ምሕረት ... 78
ከእንጦጦ ስለመጥፋቴ ... 78
ወደ አዲስ ዓለም ስለመሄዴ ... 79
ወደ ሰላሌ ስሄድ ስለደረሰብኝ ችግር ... 82
አሮጌንዳን ስለማየቴ ... 85
ወደ ጅሩ ስለመሄዴ ... 86
ወደ እንጦጦ ስለመመለሴ ... 87
በእንጦጦ ሳለሁ ... 87
ልጅ ኢያሱ የመድኃኔ ዓለምን ታቦት ስለ መትከላቸው ... 87

ምዕራፍ 11 ... 89

1904 ዓመተ ምሕረት ... 89
ስለ ኪዳነ ምሕረት ጠበል ... 89
ናዝራዊና ባሕታዊ አስደንጋጭ ስብከት ስለመስበካቸው ... 91
የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ስለመተከሉ ... 91
ወደ አዲስ አበባ ስለመውረዴ ... 92
በአዲስ አበባ ሥላሴ ሳለሁ ... 92
ሥራ ለመያዝ ስለመሞከሬ ... 93

ምዕራፍ 12 ... 94

1905 ዓመተ ምሕረት ... 94
ልጅ ኢያሱ ከጊሚራ ዘመቻ ሲመለሱ ስለማየቴ ... 94
አዲስ አበባ ላይ ስለተደረገው ተኩስ ... 94
ለወምበር በጸሐፊነት ሥራ ስለመግባቴ ... 96

ምዕራፍ 13 ... 97

1906 ዓመተ ምሕረት ... 97
ስለ አጼ ምኒልክ መሞት ... 97
ስለ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ መሞት ... 98
ወምበሩን ተከትዬ ወደ ጅሩ ስለመሄዴና ስለመመለሴ ... 98
የወምበር ጸሐፊነትን ስለመተዌ ... 99


ማውጫ


ምዕራፍ 14 ... 101

1907 ዓመተ ምሕረት ... 101
ወደ ጅሩ ስለመሄዴ ... 101
በሠርፀ ክርስቶስ ማርያም ሳለሁ ... 101
ወደ አዲስ አበባ ስለመመለሴ ... 103
ስለ አፈ ንጉሥ ጥላሁን የቤት ሥርዓት ወግ ... 103
በቀበና አቦ ሳለሁ ... 105

ምዕራፍ 15 ... 107

1908 ዓመተ ምሕረት ... 107
በአዲስ አበባ ሥላሴ ለትምህርት ስመላለስ ... 107
ወደ ጅሩ ስሄድ በመንገድ ላይ ስላጋጠመኝ ችግር ... 107

ምዕራፍ 16 ... 109

1909 ዓመተ ምሕረት ... 109
በመጽሐፍ ትርጓሜ ትምህርት ቤት ሳለሁ ... 109
በሐዲስ ትምህርት ቤት ሳለሁ ... 110
በትምህርቴ ላይ ስለደረሰው ችግር ... 110
በተላላፊ በሽታ ስለመታመሜ ... 114
መኖሪያዬን ስለመለወጤ ... 116

ምዕራፍ 17 ... 117

1910 ዓመተ ምሕረት ... 117
ትምህርቴን በመቀጠል ላይ ሳለሁ ... 117
ስለ ሽልማት ... 118
የተስቦ በሽታ በተማሪ ቤቴ ስለመግባቱ ... 119
ወደ ሐረር ስለመውረዴ ... 120
ሐረር ላይ ሳለሁ ... 121
ስለ ሐረር ከተማ ... 122

ምዕራፍ 18 ... 124

1911 ዓመተ ምሕረት ... 124
በሐረር ሳለሁ ... 124
ወደ አዲስ አበባ ስለመመለሴ ... 125
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ... 126

ምዕራፍ 19 ... 129

1912 ዓመተ ምሕረት ... 129
በትምህርት ቤቴ ሳለሁ ... 129
ስለ መምህር አካለ ወልድ ሞት ... 129
ስለ መጻሕፍት ትርጓሜ ድርጅት ... 130
ለሥራ ስለመጠራቴና ስለመግባቴ ... 132
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ... 137

ምዕራፍ 20 ... 141

1913 ዓመተ ምሕረት ... 141
የትርጓሜ ረቂቅ በመሥራት ላይ ሳለሁ ... 141
ስለ ወንጌል ትርጓሜ ... 142
ስለ የውጭ አገር ትምህርት ... 144

ምዕራፍ 21 ... 148

1914 ዓመተ ምሕረት ... 148

## ማውጫ


የአባቴን ሞት ስለመስማቴ ........ 148
ለአርባ ተዝካር ወደ ጅሩ ስለመሄዴ ........ 148
ለመንፈቅ ተዝካር ወደ ጅሩ ስለመመለሴ ........ 151
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 152

ምዕራፍ 22 ........ 155

1915 ዓመተ ምሕረት ........ 155
በአዲሱ ዓመትና በአቦ በዓል ላይ ........ 155
ወደ ጅሩ ስለመሄዴ ........ 157
በተላላፊ በሽታ ስለመታመሜ ........ 157
ስለ መጽሐፈ ሲራክ ትርጓሜ ........ 158
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 158
ሚስት ስለማግባቴ ........ 160

ምዕራፍ 23 ........ 162

1916 ዓመተ ምሕረት ........ 162
ስለ መጽሐፈ ሲራክ ትርጓሜ ........ 162
ስለ አሰቦት ገዳም ........ 162
ወደ ጅሩ ስለመሄዴ ........ 163

ምዕራፍ 24 ........ 164

1917 ዓመተ ምሕረት ........ 164
ከሥራ ወደ ሥራ ስለመዛወሬ ........ 164
ስለ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ........ 164
ስለ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት መከፈት ........ 167
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 174

ምዕራፍ 25 ........ 175

1918 ዓመተ ምሕረት ........ 175
ስለ ሽልማት ........ 175
ስለ ሥራ መስፋፋት ........ 175
ስለ አማርኛ ሰዋስው ........ 176
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 176

ምዕራፍ 26 ........ 178

1919 ዓመተ ምሕረት ........ 178
ስለ አማርኛ ሰዋስው ........ 178
ስለ ዓለም ጅዖግራፊ ........ 178
ስለ ፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ........ 180
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 180

ምዕራፍ 27 ........ 183

1920 ዓመተ ምሕረት ........ 183
ስለ ዓለም ጅዖግራፊ ........ 183
በትምህርት ቤት ስለተደረገ ሥነ በዓል ........ 185
ሐኪም ወርቅነህ ከአውሮጳ ስለመመለሳቸው ........ 186
ስለ ፍቅርና አገልግሎት ዓመታዊ በዓል ........ 188

ምዕራፍ 28 ........ 190

1921 ዓመተ ምሕረት ........ 190
በአስተማሪነት ሥራ ሳለሁ ........ 190
የአማርኛ ሰዋስው ከሌሎች ጋር እንዳስተዋወቀኝ ........ 190
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 192
ሌላ ሥራ ለመያዝ እንደፈተንሁ ........ 194


## ማውጫ


ምዕራፍ 29 ........ 195

1922 ዓመተ ምሕረት ........ 195
ወደ ሌላ ሥራ ስለመዛወሬ ........ 195
ወደ ጅጅጋ ስለመሄዴ ........ 196
የጅጅጋ ትምህርት ቤት እንደተከፈተ ........ 197
የጅጅጋ ኑሮዬ ስለ መጀመሩ ........ 199
ቤተሰቤን ወደ ጅጅጋ ስለማስመጣቴ ........ 201
ስለ አገሩ ሁናቴ ........ 203
በጅጅጋ የማሠልጠኛ ተማሪ ቤት ስለ መቆሙ ........ 204
ስለ ወሰን ጠባቂዎች ........ 205
በወሰን ላይ ስለ ደረሰ ግጭት ........ 206
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 208

ምዕራፍ 30 ........ 211

1923 ዓመተ ምሕረት ........ 211
በአውሮፕላን ነጅነት ስለ ተመረቁ ወጣቶች ........ 211
ስለ ጦር መኮንኖች ........ 213
ስለ ዘውድ በዓል ........ 213
ስለ አዲሱ የጅጅጋ አገረ ገዥ ........ 216
ስለ ትምህርት ቤት በዓል ........ 216
ስለ ሕገ መንግሥት በዓል ........ 218
ስለ ውጋዴን ........ 219
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ........ 221

ምዕራፍ 31 ........ 223

ማሳረጊያ ........ 223
ከጠላት ወረራ በፊት ........ 223
የጠላት ወረራ ዘመን ........ 223
ከጠላት ወረራ በኋላ የመንግሥት ሥራ አገልግሎት ........ 224
በልዩ ትእዛዝ የፈጸሟቸው አገልግሎቶች ........ 224
የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማት ........ 226
የወይዘሮ እታገኘሁ ዕረፍት ........ 228
ጡረታ ........ 228
አብዮት ........ 228
የአማርኛ ሰዋስው 50ኛ ዓመት ........ 230
ፍጻሜ ........ 231

አባሪ ሀ ........ 233

የደብርቹን የትውልድ ሐረግ በከፊል የሚያሳይ ........ 235
ቄስ ደፈር ከሞረት ጥዱ የሚዛመድበት የትውልድ ዘርፍ ........ 236
የመርስዔ ኀዘን የእናታቸው የትውልድ ሐረግ (የግንድ አባቱ አዲሱ) ........ 237
የወይዘሮ እታገኘሁ የትውልድ ሐረግ በእናታቸው በኩል ........ 238
የወይዘሮ እታገኘሁ የትውልድ ሐረግ በአባታቸው በኩል ........ 239

አባሪ ለ ........ 241

የቤተ ክህነት ትምህርት መግለጫ ........ 241

አባሪ ሐ ........ 247

የአለቃ ገብረ መድኅን አጭር ታሪክ ........ 247

አባሪ መ ........ 253

የሐኪም ወርቅነህ የሕይወት ታሪክ ........ 253

አባሪ ሠ ........................................ 257
መተርጐመ ቃል ........................................257
አባሪ ረ ........................................ 263
የገዳምና የደብር አስተዳዳሪዎች የክብር ስም ........................................263
አባሪ ሰ ........................................ 265
የማዕርግ ስሞች........................................265
የስሞች ፊደላዊ ማውጫ ........................................ 267

## ፎተግራፎች

1 መግደላዊት የዋሻው ውስጥ መቅደስ ........................................ 16
2 ቅብርያል ዋሻ........................................ 17
3 መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን........................................ 21
4 መግደላዊት ጠበል........................................ 22
5 የበደበጅ ገደል........................................ 26
6 እመት መሽገሪያ ሲሳይ........................................ 32
7 አጼ ምኒልክ ሰርኪስ ባቡርን ሲመለከቱ ........................................ 34
8 ራስ መኰንን ድልድይ ........................................ 35
9 እንጦጦ ማርያም በ1897 ዓ.ም. ገደማ........................................ 37
10 እመዬት የሸዋ ወርቅ ምናጣ........................................ 50
11 አቡነ ማቴዎስ........................................ 59
12 አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን (የመጀመሪያው ሕንፃ)........................................ 62
13 አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን (ከአድዋ ጦርነት በኋላ የተሠራው) ........................................ 62
14 ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን........................................ 64
15 አጼ ምኒልክ የመጀመሪያውን አውቶሞቢል ሲገቡኙ........................................ 68
16 ጅሑር መድኃኔ ዓለም ........................................ 72
17 የቅኔ ትምህርት ቤት በ1900 ዓ.ም. ገደማ........................................ 76
18 በ1902 ዓ.ም. የታየው ጅራታም ኮከብ........................................ 77
19 አዲስ ዓለም ማርያም........................................ 80
20 ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ........................................ 88
21 አቤቶ ኢያሱ (ፈረስ ላይ የተቀመጡት)........................................ 95
22 አፈ ንጉሥ ጥላሁን........................................ 104
23 ቀበና አቦ ቤተ ክርስቲያን........................................ 105
24 ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ ........................................ 118
25 ሐረር ከተማ 1920 ዓ.ም........................................ 123
26 አለቃ ታዬ........................................ 147
27 የአሰቦት ደብረ ወገግ ገዳም........................................ 163
28 ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች ........................................ 167
29 አርባዎቹ የአርመን ልጆች........................................ 168
30 ሐኪም ወርቅነህ ........................................ 177
31 ሐኪም ወርቅነህ ከወጣቶች ጋር ........................................ 181
32 በልዩ የቆመ ትምህርት ቤት (ነፃ ለወጡ ባሮችና የድኾች ልጆች)........................................ 189
33 የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ........................................ 189
34 ሞንሲኞር ኒቆላዎስ ከንግሥት ዘውዲቱና ከንጉሥ ተፈሪ ጋር........................................ 191
35 የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር አባላት ........................................ 193
36 ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል በ1923 ዓ.ም........................................ 197
37 ልጅ ተሰፋ ያየህ ይራድ ........................................ 202
38 ፊታውራሪ ታፈሰ፣ ሙሴ ቤጼል፣ ካፕቴን ዊድማር ........................................ 205
39 መርስዔ ኀዘን ጅጅጋ ከቤተሰባቸው ጋር........................................ 209



40 ወይዘሮ እታገኘሁ ጅጅጋ ከወዳጆቻቸው ጋር ........................................ 210
41 አስፋው ዓሊ በልምምድ ላይ ........................................ 213
42 የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንግሥ በዓል ........................................ 214
43 ሐረር ላይ የንግሡ በዓል ሲከበር ........................................ 215
44 የቀ.ኃ.ሥ. ሽልማት ድርጅትን የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማትን ሲቀበሉ........................................ 227
45 ብላታ መርስዔ ኀዘን ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ሲነጋገሩ ........................................ 227
46 ብላታ መርስዔ ኀዘን ከመጽሐፉ አዘጋጅ ከልጃቸው ከአምኃ ጋር 1962 ዓ.ም.... 229
47 የወይዘሮ እታገኘሁና የብላታ መርስዔ ኀዘን የቤተሰብ መካነ ቀብር ........................................ 231
48 አዛዥ ወርቅነህ በርማ በነበሩ ጊዜ ........................................ 255

## የፎተግራፎች ምንጭ

| ፎተግራፍ | ቍጥር |
|---|---|
| ሐረግ ግርማ (ወይዘሮ) | 37 |
| መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ (ልዕልት) | 45 |
| ምሥራች አስፋው (ወይዘሮ) | 41 |
| ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት | 27 |
| አምኃ መርስዔ ኀዘን | 1 2 3 4 5 6 10 16 30 39 40 44 46 |
| ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን | 11 |
| ኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ | 8 17 24 28 29 |
| ኤልሳቤጥ ወሰን (ወይዘሮ) | 36 |
| ዕሌኒ መኩሪያ (ወይዘሮ) | 31 48 |
| ዘለዓለም እንዳርጌ (ካፕቴን) | 20 23 47 |
| Bancroft , Agnes Willoughby | 42 |
| Correspondance d"Ethiopie, Mars 1929, 4e Anne, No 14 | 34 |
| Curtis, Christian | 38 |
| Ilg Collection, University of Zurich | 7 9 12 13 14 15 19 |
| Life Magazine | 32 |
| L'Empire d'Ethiopie, Adrien Zervos | 35 |
| Martin Rikli Photographs, George A. Smathers Libraries, University of Florida | 33 |
| Plowman, Stephen | 25 43 |
| Smidt, Wolbert | 21 22 26 |
| Wikimedia Commons | 18 |

## ማውጫ

### ሰነዶች

1 በ1922 ዓ.ም. የታተመው አረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ ........ 135
2 ከመምህር ወልደ ሚካኤል ለዜና ማርቆስ ካህናት የተላከ መልእክት ........ 149
3 የአለቃ ወልደ ቂርቆስ ኑዛዜ ........ 150
4 የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የመጀመሪያው እትም ........ 165
5 ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ታኅሣሥ 23 ቀን 1917 ዓ.ም. ........ 166
6 ትምህርተ ሕፃናት፣ የመርስዔ ኀዘን የመጀመሪያ መጽሐፍ ........ 173
7 በ1935 ዓ.ም. የታተመው የአማርኛ ሰዋስው መጽሐፍ ........ 179
8 በ1920 ዓ.ም. የታተመው የዓለም ጅዖግራፊ መጽሐፍ ........ 184
9 ሐኪም ወርቅነህ የጅዖግራፊውን መጽሐፍ መብት ለታሪክ ጸሐፊው የሰጡበት ... 185
10 የበረራው የምስክር ወረቀት ........ 212
11 ስለ ትምህርት ቤቱ በዓል ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ የወጣ ........ 217
12 የታሪኩ ጸሐፊ በሥራቸው ላይ የጅጅጋ ዲሬክተርነትን የተሾሙበት ........ 222

### ካርታ

1 ጅሩ ........ 19
2 ሸዋ ........ 84
3 ውጋዴን ........ 220

### ሥዕል

1 የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ክፍሎችንና አቀማመጥን የሚያሳይ ሥዕል ........ 30

# መግቢያ

የብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የዘመን ታሪክ ትዝታቸው *«የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ»* በሚል ርእስ በእኔ አዘጋጅነትና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ አሳታሚነት በ1999 ዓ.ም. ታትሞ ወጥቷል። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ክፍል የዘመን ታሪክ ትዝታቸውም በእግዚአብሔር ፈቃድ በቅርቡ የሚታተም ይሆናል።

ይህ ለአንባቢ የቀረበው መጽሐፍ ከ1891 እስከ 1923 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የግል ታሪካቸውን የያዘ ነው። ብላታ ከ1923 ዓ.ም. በኋላ ያለውን የግል ታሪካቸውን ከአንዳንድ ማስታወሻዎች በስተቀር በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅተው አልተዉልንም። ስለዚህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ከ1924 ዓ.ም. በኋላ ያለውን ታሪካቸውን ከዘመኑ ታሪክ ጋር በማዛመድ ወደፊት እኔ የምጽፈው ይሆናል።

ብላታ በኑሯቸው ጉዞ ያጋጠማቸውን፣ ያዩትንና የሰሙትን አቅርበውልናል። መጽሐፉ የብላታን የግል ታሪክ የሚተርክ ብቻ ሳይሆን የጊዜው መስታወት ሆኖ አንባቢው የዘመኑን ሁናቴ ለመረዳት ይረዳዋል ብዬ እገምታለሁ።

ብላታ መርስዔ ኀዘን በዘመኑ የነበረውን የቦታና የብሔር አጠራር ተጠቅመዋል። አንዳንዱ አጠራር በአሁኑ ጊዜ ስለቀረ በአሁኑ ጊዜ ተግባር ላይ በዋሉና ተቀባይነት ባላቸው አጠራሮችና ስያሜዎች ተተክተዋል። ከዚህ በስተቀር የብላታ ጽሑፍ ላይ አንዳችም የተቀየረ ወይንም የተጨመረ ነገር እንደሌለ ለአንባቢው ልገልጽ እወዳለሁ።

መጽሐፉን በማዘጋጅበት ጊዜ አንድ ወጣት አንባቢ በቀላሉ እንዲያነበውና እንዲረዳው ለማድረግ ሞክሬአለሁ። ግርጌ ማስታወሻዎችና አባሪዎች እንዲሁም ታሪኩን የሚያዳብሩ ፎቶግራፎች፣ የሰነድ ቅጂዎች፣ ካርታዎችና ሥዕል ተጨምረዋል። በመጽሐፉም መጨረሻ የስሞች ፊደላዊ ማውጫ ቀርቧል።

በግርጌ ማስታወሻዎች የቃላት ፍቺዎች፣ ገለጻዎች፣ አጫጭር የሕይወት ታሪኮችና የቅኔዎች ትርጉምና ምሥጢር ቀርቧል። የታሪኩ ጸሐፊ ያዘጋጁዋቸው የግርጌ ማስታወሻዎች (መ.ኀ.ወ.ቂ.) የሚል ምልክት አለባቸው። ምንም ምልክት የሌለባቸው ግርጌ ማስታወሻዎች ግን የአዘጋጁ ናቸው። የግርጌ ማስታወሻዎቹ ምንጮች ተጠቅሰዋል፤ ምንጭ ያልተጠቀሰባቸው ግርጌ ማስታወሻዎች ምንጭ ግን አዘጋጁ ነው።

በመጽሐፉ ውስጥ የግዕዝ ቅኔዎችና የግዕዝ ቃላት ይገኛሉ። የግዕዝ ቅኔ ምሥጢር አዘል ስለሆነ ሲተረጉም ምሥጢሩ ይጠፋል በማለት የድሮ

ሊቃውንት ቅኔ አይተረጎምም የሚል አቋም ነበራቸው:: ይኸውም የብላታም አቋም ነበር:: ዘመናዊው አንባቢ የግዕዝ ዕውቀት ስለሌለው ስሜቱን እንኳን እንዲረዳው መተርጐም ይኖርበታል ብዬ የሰጠኋቸውን አስተያየት በኋላ ተቀብለውት ትርጕሙን አዘጋጀዋለሁ ብለው ነበር:: ግን የቅኔዎቹን ትርጉምና ምሥጢር ሳያዘጋጁት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ስለዚህም ቅኔዎቹን የቅኔው ሊቅ መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ትርጕሙን ከነምሥጢሩ አዘጋጅተው አቅርበውልናል:: እንዲሁም በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት የግዕዝ ቃላት ተተርጕመዋል::

በመጽሐፉ ድኅረ አካል ውስጥ ሰባት አባሪዎችና የስሞች ፊደላዊ ማውጫ ይገኛሉ:: አባሪ ሀ ይህን መጽሐፍና ሌሎች የብላታን ጽሑፎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ የብላታ መርስዔ ኀዘንና የባለቤታቸው የወየዘሮ እታገኘሁ ባዬ የትውልድ ሐረግ ነው:: አባሪ ለ ብላታ መርስዔ ኀዘን ያዘጋጁት የቤተ ክህነት ትምህርት መግለጫ ነው:: አባሪ ሐ እና መ ብላታ ያዘጋጁዋቸው የአለቃ ገብረ መድኅንና የሐኪም ወርቅነህ አጭር ታሪኮች ናቸው:: አባሪ ሠ በአሁኑ ዘመን ያልተለመዱትን ቃላት የሚፈታ መተርጕመ ቃል ነው:: አባሪ ረ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የገዳምና የደብር አስተዳዳሪዎችን የክብር ስም የያዘ ሲሆን አባሪ ሰ ደግሞ የማዕርግ ስሞችን የያዘ ነው::

ለሆሄያቱ መሠረት ያደረግሁት የብላታ መርስዔ ኀዘንን ጽሑፍ ነው:: ሥርዓተ ነጥቡና አኃዙን ግን ለአንባቢው እንዲቀናው ዘመናዊውን ተጠቅሜአለሁ::

ታሪኩን ለማዳበር ፎተግራፎች፣ ካርታዎች፣ የሰነድ ቅጂዎች እንዲሁም የገጠር ቤተ ክርስቲያንን ክፍሎች የሚያሳይ ምስል ተጨምሯል::

የዚህ መጽሐፍ ኅትመት የእግዚአብሔርና የብዙ ወዳጆቼ እርዳታ ባይጨመርበት ኖሮ ፍጹም ባልተሳካ ነበር:: ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት መሳካት ዕውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ጭምር መስዋዕት ያደረጉትን ተባባሪዎቼን ላመሰግን እውዳለሁ::

በመጀመሪያ ላመሰግን የምወደው ትልቁን ባለውለታዬን ክቡር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴን ነው:: ደጃዝማች ዘውዴ ጊዜያቸውን፣ ሰፊ ዕውቀታቸውን ካለመቆጠብ አካፍለውኛል:: ድጋፋቸውም ምንጊዜም አልተለየኝም ነበር:: ደጃዝማች ዘውዴ የዚህን መጽሐፍ ኅትመት ሳያዩ መጽሐፉ ከመታተሙ ከጥቂት ወራት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩን ትልቅ ኀዘን ይሰማኛል::

ብላታ መርስዔ ኀዘንን በቅርብ ከሚያውቁ፣ ረጅም ዘመን አብረዋቸው ከሠሩት ሰዎችን አሁን በሕይወት ካሉት ጥቂት ሰዎች አንዱ አቡነ መልከ ጼዴቅ ናቸው:: አቡነ መልከ ጼዴቅ በእርማት ላደረጉልኝ እርዳታና ስለ ብላታ



መርስዔ ኀዘን ከቅርብ ዕውቀታቸው አስተያየታቸውን ለመጻፍ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ::

ዶክቶር ፈቃደ አዘዘ በእርማት ከፍተኛ እርዳታ አድርጎልኛል:: እንዲሁም መጽሐፉን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተዋወቅ ለጻፈልኝ ማስተዋወቂያ ምስጋናዬ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው::

ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ስለ መጽሐፉ ስለጻፉልኝ አስተያየታቸው ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ::

ካፕቴን ዘለዓለም እንዳርጌ በእርማት፣ ፎተግራፍ በማፈላለግ እንዲሁም በማናቸውም ባስፈለገ ጊዜ ደራሽ በመሆን ጉልበቱን ሳይቆጥብ ለሰጠኝ ከፍተኛ ድጋፍና እርዳታ ታላቅ ምስጋና የማቀርብለት ባለውለታዬ ነው:: አቶ መስፍን ሽንቁጥም እንዲሁ ድጋፉና እርዳታው ምንጊዜም ያልተለየኝ ባለውለታዬ ነው::

አቶ ልሳነ ወርቅ ንጉሤ ለሰጠኝ ከፍተኛ እርዳታ ምስጋና ሳቀርብለት የአጎቱ የብላታም መንፈስ እንደሚመርቀው አልጠራጠርም::

ቀለመ ወርቅ ጀምበር የግዕዝ ቃላትን በመተርጐም የረዳኝና በማናቸውም ባስፈለገኝ ጊዜ የተገኘልኝ ትልቅ ምስጋና የማቀርብለት ቅንና ታዛዥ ወንድሜ ነው::

አቶ አጥናፍ ሰገድ ይልማ በአርትዖቱ ሥራ ላይ ስለ አደረጉልኝ እርዳታ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው::

መረጃ በማሰባሰብና በእርማት የረዱኝን የሚከተሉትን ግለ ሰቦች ለማመስገን እወዳለሁ፤ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ፣ ሊቀ መአምራን ዶክቶር አማረ ካሣዬ፣ አቶ ዘውገ ገድሉ፣ ዶክቶር አክሊሉ ሀብቴ፣ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ፣ ዶክቶር አሰፋ ነጋሽ፣ ዶክቶር ጌታቸው መታፈሪያ፣ መጋቤ አእላፍ መክብብ አጥናው፣ ዶክቶር ፒተር ጋሬትሰን::

ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ በገጽ 227 የሚገኘውን ፎተግራፍ ስላበረከቱልኝ ምስጋናዬ በጣም ከፍ ያለ ነው:: የቤተሰቦቻቸውን ፎተግራፎች ለሰጡኝና እንድጠቀም ለፈቀዱልኝ ለሚከተሉት ባለውለታዎቼም ምስጋና አቀርባለሁ፤ ወይዘሮ ሐረግ ግርማ፣ ወይዘሮ ዕሌኒ መኩሪያ፣ ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ወሰን፣ እንዲሁም ሚሲስ ክርስቲያን ከርቲስ (Mrs. Christian Curtis)፣ ሚስተር ስቲቨን ፕላውማን (Mr. Stephen Plowman)::

አቶ ፈንታሁን ጥሩነህ በእርማት፣ መረጃዎችና ፎተግራፎችን በማሰባሰብ ትልቅ እርዳታ ያደረገልኝ ባለውለታዬ ነው:: እንዲሁም ብዙ መረጃዎችን የሰበሰበኩበትን ላይብረሪ ኦፍ ኮንግሬስንና (Library of Congress) በተለይም ፖል ዜኒን (Paul Zani) ላመሰግን እወዳለሁ::

መረጃ ለመሰብሰብ የረዳኝን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲን በተለይም አቶ አትክልት አሰፋን፣ ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ ወልደ ገብርኤልንና አቶ ሉሉ መርሻን አመሰግናለሁ።

መረጃ በማሰባሰብና በሌላም ረገድ የረዱኝን ዘመዶቼን ግርማ ደባይን፣ ሻምበል ሠይፉ ሽንቁጤን፣ አቶ ዜና ገብረ አምላክን፣ አቶ ሥዩም ዘነበን፣ አያሌው ፈለቀንና ተገኜ ገብሬን ሳመሰግን እወዳለሁ።

ከዚህ የሚከተሉት ወጣቶች በታላቅ ፍላጎትና በቅንነት ላደረጉልኝ እርዳታ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ። ኢያሱ በላይ በገጽ 30 የሚገኘውን የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ሥዕል በትልቅ ችሎታና ቅልጥፍና ሠርቶ አቅርቦልናል። በገጽ 19፣ 84 እና 220 ላይ የሚገኙትን ካርታዎች በመሥራት የረዱኝ ማርቆስ ታደሰና ጆ ሄይስ (Joe Hayes) ናቸው። ዓቢይ ሙሉጌታ ኮምፕዩተር በመስገስ ተባብሮኛል። በኃይሉ ዘሪሁን ብዙ ልዩ ልዩ እርዳታ ያደረገልኝ ቅን ወጣት ነው።

በመጨረሻም አስጀምሮ ላስፈጸመኝ ፈጣሪ አምላክ ምስጋና ይግባው።

አምኃ መርስዔ ኀዘን

# መቅድም

ትውልድ በትውልድ ይተካል፤ ሰዎችም እንዲሁ ኑረው ያልፋሉ። ይህ ለዘላለም የተደጋገመ የሚደገምም የዓለም ታሪክ ነው። አብዛኛው ሰው ወደዚህ ዓለም ለመምጣቱ፣ በዚህም ዓለምም ለመኖሩ ምልክት ሳይተው በማለፉ የእርሱንም የዓለምንም ከንቱነት ሲያንጸባርቅ ይኖራል። እግዚአብሔር ያደላቸው የተወሰኑ ሰዎች ግን ስለራሳቸውም ሕልውና ስለሌላውም ሁናቴ በመጠኑም ቢሆን መዝግበውልን ስላለፉ ለብዙዎች ተመራማሪዎች በር ከፍተው ለታሪክ ተመራማሪዎችም መነሻ የሚሆን ቅርስ እየተዉ በመሄዳቸው ምንም በሙሉ አስረጅ እንኳን ባይሆን ዓለም ከየት እንዴት ተነሥታ የት እንደደረሰች፣ ይኸንንም ያህል ዘመን ስትጓዝ ያስገኘችው ውጤት ወይም ጥፋት እንደሆነ ሁኔታዎችም ሁሉ እንዴት እንዳለፉ ለማስረዳት ዋቢ ሁነዋል።

የዘመኑ አብነት የሆኑ ሰዎች እየተነሡ ለብዙ ነገር መረጃ የሰጡ፣ ብዙ ግንዛቤም የሚገኝበትን ጽሑፍ የዘገቡልን ሰዎች ይገኛሉ። የአለፉት ዘመናት ምን ይመስሉ እንደነበር፣ በዚያም ጊዜ ምን ቁም ነገር እንደተፈጸመ፣ የራቀውን አቅርበው ከዛሬው ጋር አገናዝበው፣ ትንቢታዊውንም ዘመን ከዛሬው ጋር በማገናኘት የታሪክን ሂደት በሁኔታው በዓይነቱ ተከታትለው ጽፈው ፈርመው፣ አትመውም ያስረከቡን አባቶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ አንደኛው ናቸው።

የእኒህ ታላቅ የታሪክ አባት ብላታ መርስዔ ኀዘን የሕይወት ታሪክ ምን ያህል የተደላደለ ወደ ዕውቀትም ብቻ ያዘነበለ እንደነበር ስንመለከት በዚህ ዓለም ከተኖረ እውነተኛው የሰው ሕይወት ይኸን የመሰለ መሆን እንዳለበት በግልጽ ያስረዳል።

የክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ሕይወት በሁለት መልክ ብናየው ሚዛናዊ ሕይወት እንደነበራቸው እንጂ አንዱ ወደ ሌላው ያጋደለ አልነበረም፣ ማለት በወጣትነት ሕይወታቸው በቤተ ክህነት ትምህርት ተጠምደው ሲመሰገኑበት በዚሁ ሠርገው ሳይቀሩ ወደ ሥራ ዓለም ገብተው ቀልጣፋ ሠራተኛ ሁነው በአለቆቻቸው እየተመሰገኑ ደህናም ደሞዝ እያገኙ ሳለ በዚሁ ደግሞ ተስበው ሳይቀሩ እንደገና ወደ መንፈሳዊ ትምህርት ተመልሰው ገብተው የወጣላቸው ደቀ መዝሙር መሆን ቻሉ። እንደገናም ወደ ሥራው ዓለም ሲመለሱ ከታላላቆችና ከዐዋቂ ሰዎች ጋር በመሰለፋቸው እርሱም የጥናት መስክ ሆናቸውና አራት ዓይና ለመሆን በቁ። አማርኛም ግዕዝም ጥሩ አድርገው በማወቃቸው በቤተ መንግሥቱም በቤተ ክህነቱም ሊሠለጥኑበት ቻሉ። የግዕዝና የአማርኛ ጥልቅ ዕውቀት ስላላቸው ወደፊትም ወደኋላም ለማየት ከሁሉ የላቀ ችሎታ ነበራቸው፣ ስለዚህም አስተውለው የተመለከቱትን የሰሙትን ራሳቸው የሠሩትን መዝግበው አቀረቡልን።

ብላታ መርስዔ ኀዘን ደንበኛውና ቋሚ ሥራቸው በመንግሥት ይሁን እንጂ በልዩ የዕውቀት ችሎታቸው በቅዱስ መጽሐፍ የትርጕም ሥራ፣ በልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የትርጕም ሥራ፣ እንዲሁም በተለያዩ በግል የድርሰት ሥራ፣ በታሪክ ምርምርና ምዝገባ ዘመናቸውን አሳልፈዋል። የብላታ ሕይወት ይኸን በመሰለ ተግባር ያለፈ ሲሆን ሰለቸኝ፣ በቃኝ የማይሉ፣ ፍጹም የሥራ ሰው ነበሩ። በቡድን በሚሠራ ሥራ እኔ ልታይ ወይም ልታወቅ፣ ወይም የኔ አስተያየት ብቻ ተቀባይነት ይኑረው የማይሉ ትሑት፣ ስብዕና የነበራቸው አባት ነበሩ። በአጠቃላይም የመልካም ጠባይ አርአያ እንደነበሩ ሥራቸው ይመሰክራል።

ብላታ መርስዔ ኀዘን ከኔ ጋር ለመተዋወቅ የቻልነው ካህን እንደ መሆናቸው መጠን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ በመገናኘት በአገልግሎት ስንሳተፍ፤ ሁለተኛ ለፍትሐ ነገሥቱ የትርጕም ሥራ በእሳቸው ሰብሳቢነት ስንሰበሰብ የወ.ወ.ክ.ማ. የቦርድ አባል ሁነው ስንሰበሰብ እኔም አባል ስለነበርሁ በመገናኘታችን፤ የዩኒቨርሲቲ ኰሌጅ ቦርድ አባል ሆኜ ስሠራ እሳቸው የቦርዱ ሊቀ መንበር ስለነበሩ በመገናኘት ብዙ ጊዜ አብረን አሳልፈናል።

አንድ ሰው ታላቅ የሚሆነው ዕውቀት ከፈሊጥ ጋር ሲኖረው ነው። ዕውቀትና ማስተዋል በዘመን አይለካም ከሞያው ጋር ባሕርዩ የተስተካከለ ሲሆን ብቻ ነው። ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ከሞያቸውና ከሥራ ችሎታቸው ጋር ሚዛናዊ የሆነው ጠባያቸው ሁሉን ወደ አድናቆት የሚስብ ነበር። በእርግጥም ይኸን ያህል የታሪክ መዝገብ በተለያየ መልክ ሊመዘግቡልን የቻሉት በረጋ መንፈስ፣ በመልካም ጠባይ ዘመናቸውን ሁሉ ያሳለፉ በመሆናቸው እንደሆነ ያስረዳል።

ብላታ መርስዔ ኀዘንን በተለያየ ገጽታ ብንመለከታቸው ሥራቸው፣ ጠባያቸው፣ ችሎታቸው ልዩ ጥናትን የሚሰጥ ሆኖ እናገኛለን። ይሁን እንጂ ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስን ስናስታውሳቸው የምንኖረው አንደኛ፣ ግምት በማይሰጣቸው ጽሑፎቻቸው፤ ሁለተኛ፣ በረጋ መንፈስ ያሳለፉት ሕይወታቸው፤ ሦስተኛ፣ በሥነ ምግባር አንጸው ያሳደጉት ይኸንን ሥራቸውን ሁሉ ወደ አደባባይ ይወጣና ይታወቅ ዘንድ የሚሠራው ልጃቸው አምኃ ነው።

መጻሕፍታቸውን በየተራ የተመለከትናቸው እንደሆነ እርሳቸውን እንዳገኘናቸው እንገነዘባለን። የሕይወት ታሪካቸውንም በምናጠናበት ጊዜ ድንቅ የሆኑ ሥራቸውን በሚገባ መዝግበው፣ በዚህ ዓለም በሚገባ አኑረው እንዳለፉ እንረዳለን። ከሌላው ኃላፊና ጠፊ ከንቱ ፍጥረትም ለይተን በትክክል ሰው እንደነበሩ፣ ሰው የሚያሰኛቸውን ተግባር ፈጽመው እንዳለፉ እንረዳለን።

«የደግ ሰው መታሰቢያው ለዘለዓለም ነው።» (መዝ. 114 ቍ. 6)

አቡነ መልከ ጼዴቅ፣ ሊቀ ጳጳስ

# ማስተዋወቂያ

ግለ-ታሪክ ያንድ ግለሰብ ሕይወት ትረካ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ተራኪው በሕይወት ዘመኑ የወጣ የወረደበትን ሁሉ ይናገራል ማለት እንዳይደለ ግልጽ ነው። ስለዚህ መምረጥ አለበት ማለት ነው። ከመረጠ ደግሞ ሆነ ብሎም ይሁን ሳያውቅ የሚገለገልባቸው መስፈርቶች ይኖሩታል። አንዱ መስፈርት ግለታሪኩን ለመጻፍ ከወሰነበት መሠረታዊ ዓላማ ይመነጫል። በፈቃዱ በራሱ ላይ የሚጥለው ማእቀብ ወይም ግላዊ ስንሰራም ይኖራል። ለባህልና ወጉ ያለው ታማኝነት "እኔም፣ ያደግሁበትና የኖርኩበት ባህሌም በአደባባይ ለመናገር የማልፈቅደው አለ!" ብሎ ከጽሑፉ የሚያስወግዳቸውም ይኖራሉ። በሚጽፍበት ጊዜ ያልመጣለት፣ ያላስታወሰው ቁምነገርም ሳይጻፍ የሚቀርበት ጊዜም አይኖርም አይባልም። እንዲህ እንዲህ ያሉትንና እነርሱን የመሳሰሉ መላ ምቶችን ከተራኪው ጽሑፎችና ከሌሎች ምንጮች የሚያገኛቸውን መረጃዎች አጥንቶ ዕውቀታችንን ይበልጥ የሚያዳብር ተመራማሪ ይመጣል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እስከዚያ፣ ትዝታዬ ስለ ራሴ የማስታውሰው የተባለውን የመርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ መጽሐፍ ሳጣጥም ከቀሰምኩት መጽሐፉን ለአንባብያን ለማስተዋወቅ ይጠቅማሉ ያልኳቸውን አንዳንድ ነጥቦች ከዚህ በታች አቀርባለሁ። የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ - የዘመን ታሪክ ትዝታዬ - ካየሁትና ከሰማሁት፣ 1896 - 1922 (1999 ዓ.ም.) ስለተባለው መጽሐፋቸውም አልፎ አልፎ አነሳለሁ። ይህንን የማደርገው፣ በአጋጣሚው በመጠቀም ሁለቱ መጻሕፍት ለምርምር ያላቸውን አስተዋጽኦ ለማጉላት ስል ነው።

ጥሩ ግለ-ታሪክ፣ ተመራማሪዎች ነጣጥለው የሚያጠኗቸውን ቁም ነገሮች አዋህዶ፣ በመሀከላቸው ያለውን መስተጋብር ጠብቆ፣ የሕይወትን ቡራቡሬ መልክ ይመስላል። ለምሳሌ፣ መርስዔ ኀዘን ትዝታዬ . . . ስለ ቤተሰብ ሲተርክ አኗኗሩን፣ የልጅ አስተዳደጉን፣ የሥራውን ዓይነትና ጥረቱን፣ ሕመምና ጤናውን ፣ መድኃኒትና መርዙን ወዘተ. በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ እያስተሳሰረ በየቦታው ያቀርባል። ይህንን በማድረጉም፣ የጸሐፊውን ማንነት፣ ማለትም የሰብእናውን አወቃቀር፣ ሊያመለክት የማኅበረሰቡንም ምንነት ሊያሳይ የቻለ ይመስለኛል። እርግጥ፣ ከጽሑፉ ውስጥ እነዚህን ቁምነገሮች ሥርዓት ባለው መልክ አበጥሮ ማውጣት የልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች ባለሙያዎች ፈንታ ነው። በጽሑፉ ውስጥ በመደጋገማቸው ምክንያት አፍጥጠው የሚወጡ ቁምነገሮች ሲኖሩ፣ እነዚህ የዘመኑ አሻራ ይሁኑ አይሁኑ ማስረጃዎችን እያጠናቀሩ ያለ ብዙ ድካም አንዳንድ መላ ምት መሰንዘር ደግሞ የንቁ አንባብያንም ፈንታ ይሆናል።

መጽሐፉ ስለ ዘመኑ ግለሰቦች የአካል ብቃትና ጥንካሬ፣ የመንፈስ ጽናት፣ እልህ፣ ወኔ፣ ትዕግስት፣ ብልሃት፣ ፍቅርና ጸብ፣ መተሳሰብ ወዘተ. በመገረም ጭምር እንዳስብ አድርጎኛል። ትረካው ስለሚኪያሂድባቸው ልዩ ልዩ

አካባቢዎች (ጫካ፣ ወንዝና ተራራ፣ ከብቶችና አራዊት ወዘተ.) የሚቀርቡትን ገለጻዎች ዛሬ ስለሀገራችን እና ስለዓለማችን ከሚነገረው ጋር እያነጻጸርኩ ስለ ሰው ልጅ የወደፊት ዕጣ እንዳሰላስል የተገደድኩባቸው ጊዜያት ጥቂት አይደሉም። በወቅቱ ይመረቱ የነበሩትን የሰብል ዓይነቶች ገልጸው፣ እነዚህን ከገበሬው ይነጥቁ የነበሩትን የሰማይ አእዋፍና አውሬዎች በስም ዘርዝረው፣ በቂ የእርሻ መሬት ባለመኖሩ ባለርስትና ተጋዥ የሚደርስባቸውን ልፋትና ይኖሩት የነበረውን ዝቅተኛ ኑሮ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሰው ሲያዝኑ ዘመኔን እያሰብኩ እኔም አዝኛለሁ። የመልክአ ምድር እና የሥነ ምኅዳር ተማራማሪዎች ከእንደነዚህ ዓይነት መጻሕፍት (የየዘመኑን ልብ ወለዶችና ሌሎች መጻሕፍት ጨምሮ) ስላለፈው ዘመን የተለያዩ ሐሳቦችን ሊቀስሙ እንደሚችሉ ተገንዝቢያለሁ። ሌላው ቢቀር በሙያቸው ለሚያደርጓቸው ምርምሮች አንዳንድ ፍንጮች ያገኛሉ የሚል ግምት አለኝ።

በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ስላሉ፣ ነዋሪዎቹን እጅ ለእጅ፣ ልብ ለልብ ስላያያዙ እሴቶችም የተገነዘብኩት ብዙ አለ። የትውልድ ስሞች፣ ሐረጎችና ዘርፎች ዝርዝር ለእንደኔ ዓይነቱ የሸሮሜዳ (የአዲስ አበባ) ልጅ «አሪት ዘፍጥረት»ን ያስታውሳሉ። አፈ-ታሪክ (ፎክሎር) በጥንቃቄ ካልተመረመረ ታሪክን እንዴት ሊያዛባ እንደሚችል ስለ ቅብርያል ዋሻ የጻፉት ጥሩ ምሳሌ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፉ፣ "የዋሻው ስም ቅብርያል የተባለበት በአጼ ሱስንዮስ ጊዜ ቅብርያል የተባለ ሰው ዋሻውን ምሽግ አድርጎ ከንጉሡ ተቀምጦበት ስለነበረ ነው። የበደበጅ ባላገር ግን <u>ታሪኩ ጠፍቶበት</u> 'ቅብርያል የተባለ ቀይ ዘንዶ ነበረበት አሉ' እያለ በመላ ሲያወራ ሰምቻለሁ" (ገጽ 17፣ አጽንኦት የኔ) ይሉና የታሪክ ማስረጃቸውን ይጠቅሳሉ (ገጽ 17)። ስለ አተራረክ ስልታቸው ሳወሳ የቅብርያልን ጉዳይ እመለስበታለሁ። አሁን ግን፣ ለአፈ-ታሪክ ጥናት የሚረዳ ሌላ ምሳሌ ላክል።

የመርስዔ ኀዘን የእናታቸው አባት አቶ ምናጣ ይባላሉ። «ክፉ ቀን» በመባል በሚታወቀው የችግርና የረሃብ ወቅት ለወገኖቻቸው ስላደረጉት እርዳታ ለማመስገን «በምናጣ፣ ወጣሁ ስቀናጣ» (ገጽ 51) ተብሎ ተገጠመላቸው። ይህን ግጥም ሌጣውን ባገኘው ምን ማለት እንደሆነ በቀላሉ አልረዳም ነበር። «ምናጣ» ራሱ የሰው ስም መሆኑን ስለማላውቅ የአማርኛ ቅኔን አንድ መንገድ ተከትዬ ባነበብኩበት ቅጽበት ያልሆነ ፍች ልሰጠው እችል ነበር። እንዲህ ከታሪኩ ጋር ስለቀረበ ግን ከብዙ ድካም አድኖኛል። በተመሳሳይ መንገድ፣ ከነአውዳቸው የቀረቡ ሌሎች ቁም ነገሮች በመጽሐፉ ውስጥ አሉ።

ትዝታዬ. . .ን ሳነብ፣ ይገናኛሉ ብዬ የማላስባቸው ነገሮች ተገናኝተው በማግኘቴ ካድናቆት ጋር የቀሰምኳቸው ቁምነገሮችም አሉ። አጠር ያለ ምሳሌ በጥያቄ አጅቤ ላቅርብ። የማርያም መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን በሐ ላይ በመሠራቱ ብዙው የእምቧጮ ሰው ቤተ ክርስቲያኑን ተከትሎ መኖርያውን ወደ በሐ እንዳዞረ መርስዔ ኀዘን ባይጽፉት በምን ይታወቅ ነበር? ዛሬ በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ይህንን ታሪክ ያውቁ ይሆን? ካላወቁ፣ ያካባቢውን ሕዝብ የአሰፋፈር ታሪክ የሚያጠኑ ሰዎች አንድ የአሰፋፈር ምክንያት



አመለከቱቸው ማለት አይደለም? በተጨማሪም፣ አንዳንድ በመሠረቱ ያልተለወጡ ነገሮችን በትዝብት አስተውያለሁ። ለምሳሌ፣ ዛሬ የራስ መኰንን ድልድይ የሚባለው ለመጀመሪያ ጊዜ የዛሬ 105 ዓመት ገደማ በኖራና በግንብ ሲሠራ "ሕዝብ ሁሉ እንደ ብርቅ ይመለከተው ነበር" (ገጽ 34) ብለው ሲጽፉ፣ ከብቦት የነበረውን ሰው ብዛት ገምቼ፣ "ዛሬስ ምን ያህል ተለውጠናል?" ብዬ ጠይቄ፣ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸውን አውጥቼ አውርጄም፣ ነገሩ እስካሁን ይከነክነኛል፣ አንዳንዴም ያሳፍር ያሳዝነኛል።

ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸውን የሚመስሉ፣ በዕለታዊ ኑሮ ውስጥ እየተነገሩና እየተገበሩ ሳይመዘገቡ የቆዩ፣ ስለራሳችን እንድንመራመር የሚረዱ ብዙ ቁም ነገሮች በመጽሐፉ ውስጥ አሉ። መዛግብትን፣ ብራናዎችን፣ እና የታተሙ ጽሑፎችን መሠረት አድርጎ ያንድን ሀገር ታሪክ ጽፎ የማሳተም ልምድ ስለገነነ በቃል የሚነገረው፣ በአካል የሚተወነው እና በቁሳቁስ የሚተረከው ተንቆ ቆይቷል። ሰሚ ያጡ የማኅበራዊ ታሪክ ድምጾችም («መዝገቦች» ልንላቸው እንችላለን) በየአጥቢያው፣ በየመንደሩ፣ በየተራራውና በየሜዳው እያስገመገሙ ኖረዋል፣ ዛሬም እየኖሩ ነው። ስለዚህም ነው፣ የመርስዔ ኀዘን መጻሕፍት ለአንባብያን፣ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ትምህርትን፣ ለተመራማሪዎች መነቃቃትን፣ ለባህል የመስክ ሠራተኞች ደግሞ ትጋትን ይቸራሉ ብዬ ተስፋ የማደርገው።

<u>ትዝታዬ. . .</u> ስለ መርስዔ ኀዘን ልጅነት፣ ጨዋታ፣ እልህ፣ ስለደረሰባቸው ቅጣት፣ ቡተለይ ደግሞ ስለተከታተሉት ትምህርትና በሥራ ዓለም ስላጋጠማቸው ውጣ ውረድ በብዛት ይተረካል። በአካባቢው እምነት መሠረት ወደ ፊደል ቆጠራ በአራት ዓመት ከአራት ወራቸው ሲገቡ፣ የደብተራ እንደብልሃቱ አለንጋ የማስተማሪያ መሣሪያ ሆኖ ይጠብቃቸዋል። ትምህርት ቤት መሄድ ይጠላሉ። ቤተሰብ ግን አሁንም በድብደባ እንዲሄዱ ሲያስገድዳቸው "በበደበጅ ገደል ገርው ብዬ እገባለሁ. . ." (ገጽ 25) እያሉ ለጓደኞቻቸው ማጫወት ይጀምራሉ። በኋላ ግን ያመርሩና እናታቸው ወዳሉበት ወደ መስቀለሶስ ይኮበልላሉ። ከዚያም ወደ አክስታቸው ወደ እምዬ በስሙ ዘንድ ይሄዱና፣ "ከዚህ ቀን ጀምሮ ትምህርት ቀረልኝና ሥራዬ ጨዋታ ብቻ ሆነ" (ገጽ 28) ሲሉ በደስታ ይናገራሉ። አባታቸው ዘንድ እንጦጦ ከተመለሱም በኋላ ልዩ ልዩ የገበታ ሥርዓት (ለምሳሌ «ድምጽ ሳያሰሙና ሳያጮሁ ማላመጥ») ሲማሩ የተሳሳቱ እንደሆነ ስሕተታቸው የሚነገራቸው በኩርኩምና በቁንጥጫ ነበር። አለቃ ወልደ ቂርቆስ ተማሪዎቻቸውን የሚቀጡበት አለንጋ «በላዔ ሰብእ» (ገጽ 44) ይባል እንደነበረ ይነግሩንና ባላጠፉት ጥፋት በዚሁ አለንጋ ተጠብጥበው እንደነበርም ይተርካሉ (ገጽ 54)። ዝርዝሩ ብዙ ነው። የሶሲዮሎጂና የሥነ ልቡና ባለሙያዎች መጽሐፉን በጥሞና ከዳር እስከ ዳር ወጥተው ቢመረምሩ ስለ ቤተሰብ፣ ስለ ልጅ አስተዳደግ፣ ስለ ልጅነት ጨዋታ፣ ተንኮል፣ አመጽ እና ከእነዚህ ጋር ስለሚዛመዱ ሌሎች ጉዳዮች ለምርምር የሚጠቅም ብዙ ሐሳብ እንደሚያገኙ ጥርጥር የለኝም። አንባብያንም፣ ብዙ ጊዜ በወላጆችና በባህሉ ዓይን ከሚተረኩት የልጆች ልምዶች ወጣ ተብሎ በሕፃናቱና በልጆቹ ዓይን እየታዩ

የሚቀርቡ ትረካዎችን ያነብባሉ:: በሌላ ዘመንና ቦታ ተፈጽመው ያልተጻፉትን ልምዶቻቸውን እያስታወሱ ፈገግ ይላሉ:: ወይም ደግሞ አልፈው የመጡትን፣ በየምክንያቱ በውስጣቸው ያንቀሳፋውን ልጅነታቸውን እየቀሰቀሱ እንደኔ በትዝታ ይኮረኩራሉ፣ በሰኖሳስ ይፍነከነካሉ::

የትምህርት ባለሙያዎች ደግሞ ስለ ጥንቱ የግዕዝ ትምህርት ቤት አኪያሄድ፣ በየደረጃው ስለሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች፤ የትምህርት ዓይነቶቹ ስለሚጠይቁት ችሎታ፣ ትዕግስትና ትጋት፣ ተማሪው በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ሲያልፍ በየደረጃው ስለሚገነባው ስብእና፣ በመምህራኑና በተማሪዎች እንዲሁም በሊቃውንቱ መሀከል ስለነበሩ ግንኙነቶች ወዘተ. ልኩ በቀላሉ የማይሰፈር ዕውቀት ያገኛሉ:: ሳናውቀው በስሕተት፣ በድፍረት፣ በአጉል ትዕቢት፣ በንቀትና በጭፍኑ ያንኳሰስነውን የቃል ትምህርትን ጥቅምና ጉዳት «ምሁራን» የምንባለው ሁሉ እንደገና መመርመር እንዳለብን የሚያሳስቡ ብዙ ቁም ነገሮች በሁለቱ የመርስዔ ኀዘን መጻሕፍት ውስጥ አሉ:: አንድ ምሳሌ ከ<u>ትዝታዬ. . .</u> ልጥቀስ::

የአረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ በመባል የሚታወቅ፣ መምህር አካለ ወልድ ከሞቱ አብሯቸው ይሞታል የሚል ሥጋት ያሳደረ መጽሐፍ ነው:: ሥጋቱ የመጣው የዚህ መጽሐፍ የትርጓሜ ትምህርት በቃል ይተላለፍ ስለነበረ ነው:: ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ለመምህር አካለ ወልድ ደብዳቤ ጽፈው ንባቡን ከነትርጓሜው እንዲጽፉ ጠይቀዋቸው ነበር:: ነገር ግን ጀምረው ሳይጨርሱት ኅዳር 9 ቀን 1912 ዓ.ም. ስላረፉ ሥራውን ተፍጻሜ የሚያደርስ ሰው ሲፈለግ መምህር ደስታ ይገኛሉ:: ከዚህ በታች የምጠቅሰው መምህር ደስታ የትርጓሜው ትምህርት ከማን፣ ለማን እየተላለፈ እርሳቸው ዘንድ እንደደረሰ ለመርስዔ ኀዘን የነገሯቸውን ነው::

> *ጊዮርጊስ ሶርያዊ ለድምሆይ ዘምሥሐለ ማርያም አስተማረ*
> *ድምሆይ ዘምሥሐለ ማርያም ለጥበበ ክርስቶስ አስተማረ*
> *ጥበበ ክርስቶስ ለሐዋርያነ ክርስቶስ አስተማረ*
> *ሐዋርያነ ክርስቶስ ለሊቀ ካህናት ወልደ ዮና አስተማረ*
> *ሊቀ ካህናት ወልደ ዮና ለእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ አስተማረ*
> *እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ለዓቃቤ ሰዓት አብራንዮስ አስተማሩ*
> *ዓቃቤ ሰዓት አብራንዮስ ለመንፈቆ ወልደ ሃይማኖት አስተማሩ*
> *መንፈቆ ወልደ ሃይማኖት ለመምህር ሙሴ አስተማሩ*
> *መምህር ሙሴ ለመምህር ሐሲብ አስተማሩ*
> *መምህር ሐሲብ ለመምህር ሀብቱ አስተማሩ*
> *መምህር ሀብቱ ለመምህር አካለ ወልድ አስተማሩ*
> *መምህር አካለ ወልድ ለመምህር ደስታ አስተማሩ (ገጽ 137)*

በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን፣ ጊዮርጊስ ሶርያዊ ለድምሆይ ዘምሥሐለ ማርያም ካስተማረበት ጊዜ ጀምሮ መርስዔ ኀዘን ተምረው በ1912 ዓ.ም. እስከጻፉት ድረስ የአረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ፡ የትርጓሜ መጽሐፍ ትምህርት እየተሰጠ ከዘመን ዘመን የተላለፈው በቃል ጥናት ብቻ ነበር:: ትርጓሜውን በማስተላለፍ፡



ሥራ የተካፈሉት ሊቃውንት መርስዔ ኀዘንን ጨምሮ 14 ነበሩ:: መጽሐፉ በ1922፣ ድሬዳዋ በነበረው፣ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት መታተሙን አቶ አምኃ በግርጌ ማስታወሻ ገልጸዋል:: ከዚህ ምን መማር እንደሚገባ ለአንባብያንና ለተማሩ ኢትዮጵያውያን እተወዋለሁ::

ስለ <u>ትዝታዬ. . .</u> መጥቀስ ያለብኝ ሌላው ነጥብ የአተራረክ ስልታቸውን ይመለከታል:: ማስተዋወቂያዬ እየረዘመ ስለመጣ በተቻለ መጠን አሳጥሬ ልናገር:: የአተራረክ ስልታቸው ሁለቱን መጻሕፍት ይዞ፣ ሌሎች ሥራዎቻቸውንም ጨምሮ ራሱን ችሎ የሚጠና ነው:: ከዚህ ቀጥዬ ለአብነት ያህል የማነሳው ግን ግለ-ታሪካቸውን ለመጻፍ ለሚያስቡ ሁሉ መልካም ማስታወሻ ይሆናል የምለው ነው:: ይኸውም አንድ ታሪክ እየተረኩ፣ በመሃል የሚመጣ ሌላ ትረካን ያለ እክል የመቀጠል ክሂላቸውን የሚመለከት ነው:: እንዲህ ነው::

ቀደም ብዬ ያነሳሁት፣ የኦርቶዶክሳዊው ግብጻዊ የቅብርያል ታሪክ (ገጽ 17-18) የመርስዔ ኀዘን ዓቢይ አካል አይደለም:: ቅብርያል የሚባለውን ዋሻ ያነሱና ስለዋሻው ስያሜ አገሬው የሚለውንና በታሪክ ድርሳን የተመዘገበውን ይነግሩናል:: ከዚያ በኋላ፣ "ቅብርያልን ካነሣሁ ዘንድ ስለ ታሪኩ ጥቂት መግለጫ መስጠት ይገባኛል" በሚል ማስታወሻ በትረካቸው ውስጥ ስለሚመጣ ሌላ ተረክ (narrative) አንባቢውን አሳስበው ይቀጥላሉ:: የቅብርያልን ታሪክ ሲጨርሱ ደግሞ፣ "እንግዲህ ወደ ታሪኬ እመለሳለሁ" ብለው ወደ ዋናው ትረካ ይመለሳሉ:: ከዋናው የታሪክ መስመር ሲወጡና ጣልቃ የገባውን ታሪክ ሲጨርሱ መናገራቸው አንባቢ በሥርዋጽ ትረካው እንዳይደናቀፍ፣ ዓቢይ ትረካውም ከቆመበት ተነሥቶ ኮለል ብሎ እንዲፈስ አድርጓል:: ይህ የመልካም ተራኪ፣ የልባም አውጊ አንድ መለዮ ይመስለኛል:: የምዕራፍ 2 የመጨረሻ ዓረፍተ ነገርም በተከታዩ ምዕራፍ የሚመጣውን ሌላ ሥርዋጽ ትረካ የሚያመለክት ነው:: በምዕራፍ ሦስት ስለ ወላጆቻቸው ከጻፉ በኋላ የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር "እነሆ የወላጆቼን ዜና ባጭሩ ጽፌ አቆምሁ" ይሉና በምዕራፍ አራት ውስጥ የራሳቸውን ታሪክ ያወሳሉ:: ሌሎች የትረካ ዘዴዎችም አሉ:: የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ትረካውን፣ ዓረፍተ ነገሮቹን፣ ቃላቱንና ሐረጎቹን በመመርመር ጸሐፊው ሐሳባቸውን ለአንባቢም ይባል ለትውልድ ለማስተላለፍ የተጠቀሙባቸውን ስልቶች እንዲያጠኑ እመክራለሁ:: ያንድን ቁም ነገር ታሪካዊነትና ቀጣይነት (continuity) አንባቢ እንዳይስት ለማድረግ በአጽንኦት ስልት የሚጠቀሙባቸውን ጊዜያት፣ አንባቢ ትረካውን በትኩረትና በትጋት እንዲከታተል የሚያደርጉባቸውን መንገዶች፣ አንባቢ የሚያስተላልፉትን መልእክት እንዳስተላለፉለት እንዲቀበላቸው ሲፈልጉ የሚገለገሉባቸውን ተደጋጋሚ ስልቶች፣ አንባቢን፣ የሰዎችን ሐሳብና ስሜት፣ የተመለከቷቸውን አንዳንድ ድርጊቶች የሚገልጹባቸውን ብልሃቶች እና ሌሎች ቴክኒካዊ ጉዳዮች ፈልፍለው ሲያወጡ፣ ስለ መርስዔ ኀዘን የአጻጻፍ ዘዬ/ዘዬዎች ሊተውሩ ይችላሉ የሚል እስተያየት አለኝ:: ከፍ ብዬ ባቀረብኩት ምክንያት የትረካን ጉዳይ በዚሁ አበቃለሁ::

በአፈ-ታሪክ ምርምር ክቡር ስፍራ ካላቸው ምሁራን አንዱ ያን ቫንሲና (Jan Vansina) ትውፊት እንደ ታሪክ (Oral Tradition as History) በተባለው፣ የዛሬ 25 ዓመት ገደማ በታተመው መጽሐፉ፣ አንድ መረጃ ወይም መልእክት ከየት-ከየት እንደሚገኝ፣ እንዴት ከሰው ወደ ሰው፣ ከቦታ ወደ ቦታ፣ ከዘመን ዘመን እንደሚተላለፍ፣ እንዴት እንደሚሰበሰብ፣ እንደሚደራጅ እና እንደሚጠና በሰፊው ያትታል። አንዱ መልእክት ከአንዱ ወደ ሌላው በሹክሹክታ የሚተላለፍ የቅርብ ጊዜ ዜና ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ አንድ ግለሰብ ስለራሱ ምኞት፣ ትናንት ሌሊት በሕልሙ ስላየው ነገር፣ ስላጋጠመው ራዕይ፣ የሚያወራው ወሬ በሹክሹክታ ሊራባ ይችላል። በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚነገሩ ትንቢቶችም መልካቸውን እየለዋወጡ በነዋሪዎቹ መሀከል ይተላለፋሉ። በትዝታ መልክ የሚተረኩ፣ ስለአንዳንድ የቦታ ስያሜዎች ምንጭ እና ስለነገራት አመጣጥ የሚነገሩም አሉ። በግጥም፣ በተረት፣ በምሳሌያዊ ንግግር መልክ የሚቀርቡም አሉ። ሌላው መልእክት፣ አንድ ድርጊት ሲፈጸም አይቶ፣ ያንን ያየውን እና የሰማውን ጉዳይ፣ የአድማጮቹን ማንነት፣ ያለበትን ቦታና ሁኔታ፣ እና ጊዜውን እየመዘነ አንድ የዓይን ምስክር የሚያቀርበው ቃልም ሊሆን ይችላል። ዝርዝሩ ብዙ ነው። ባጭሩ፣ እነዚህ እና እነዚህን የመሳሰሉ መልእክቶች ሁሉ የአንድ ግለሰብ፣ የአንድ መንደር፣ ወይም ሀገር ታሪክ ሲጠና የሚያበረክቱት ነገር አለ። ስለዚህም የሚሰበሰቡበት፣ የሚጣሩበት፣ የሚጠናቀሩበት እና ተደራጅተው የሚቀርቡበት መንገድ-መንገድ አለ። እነዚህን መንገዶች መሠረት አድርጎ ታሪክ መጻፍ ቀላል ሥራ አይደለም። በውትድርና ቋንቋ የግለ-ታሪክና የአፈ-ታሪክ ምርምር ፈንጂ የሚበዛበት መስክ ስለሆነ እያዩ፣ እያስተዋሉ፣ እየመረመሩ፣ በጥንቃቄ የሚኳዙበት መስክ ነው ማለት ማጋነን አይሆንም። ተጠንቅቆም ሁሉን ባይሆን ብዙውን የሚያረካ ሥራ ሠርቶ ማቅረብ ከተአምር የሚቈጠር ነው ማለት ይቻላል።

ዛሬ፣ ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸውን ዓይነት ያምርምር ዘዴዎችና ትውሮች ይዞ፣ የግለሰብ ታሪክ የሚያጠና ተመራማሪ ከመረጃ አቀባዮች በኢንተርቪው ከሰበሰበው መረጃ አብዛኛው አስተማማኝ የዓይን ምስክር መረጃ ከሆነለት ለሥራው ደኅንነት አንድ መነሻ ፍንጭ አገኘ ማለት ስለሆነ በደስታ ይቦርቃል። መርስዔ ኀዘን ባለፉት 45 ገደማ ዓመታት እየዳበሩ ከመጡት የቃል ታሪክ ጥናት ዘዴዎችና ትውሮች (methods and theories) ጋር ሳይተዋወቁ በእኔ አስተያየት፣ በተግባር ግን ጥቂት የማይባሉትን ፈጽመዋል። ያዩትን "አየሁ!"፣ የሰሙትን "ሰማሁ!" እያሉ ነው በየቦታው የተረኩልን። በአፈ-ታሪክ፣ በግለ-ታሪክ ወይም በፎክሎር ተመራማሪ ቢጠየቁ የሚናገሩትን በወግ፣ በጨዋታ መልክ ራሳቸው ያቀረቡልን መስሎ ነው የተሰማኝ። ሁለቱንም መጽሐፎች ሳነብ፣ የሚተርኩልኝን የተከታተልኩት በዓይነ-ሕሊናዬ እያየሁ፣ በእዝነ-ኅሊናዬ እየሰማሁና እያደመጥኩ የነበረ ይመስለኛል። ይህ ደግሞ ከተመራማሪው በተዘዋዋሪ አገኝ የነበረውን ከርሳቸው በቀጥታ ከነወዙ እንዳገኝ አድርጎኛል። ካካበቱት ልምድና ዕውቀት፣ የ20ኛውን ክፍለ ዘመን መባቻ የሚያጠኑ ተመራማሪዎች፣ እንዲህ እቅጭ-እቅጩን፣ ግልጽ በሆነ



ቋንቋ፣ ቁልጭ አድርገው ያቀረቡ፣ ወደፊትም የሚያቀርቡ ኢትዮጵያውያን ስንት ይሆኑ? ቊጥራቸው እንዲበዛ እመኛለሁ።

አቶ አምኃ ትዝታዬ. . .ን አንብቤ ማስተዋወቂያ እንድጽፍ ስለጠየቀኝ ስለ እኚህ ታላቅ ሰው መጻሕፍት አንዳንድ ትንንት አስተያየቶች ጭሬያለሁ። በዚህ የተነሣ፣ እልፎ እልፎ ስሜ ከእርሳቸው ሥራዎች ጋር፣ ፈቀድኩም አልፈቀድኩም፣ መነሣቱ አይቀርም። ለዚህ መብቃት መታደል ነው። አቶ አምኃን ከልብ አመሰግነዋለሁ።

የአባቱን መጻሕፍት በጥንቃቄ አዘጋጅቶ፣ ለአዘጋጁ በጣም አድካሚ ለአንባቢና ለተመራማሪ ግን እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን ግርጌ ማስታወሻዎች፣ አባሪዎችና መጠቆም (ለ index ፕሮፌሰር ጌታቸው የሰጡት መጠሪያ ነው) አደራጅቶ ስላሳተመ በድጋሚ አመሰግነዋለሁ። አንባብያንም የመርስዔ ኀዘንን መጻሕፍት እያነበቡ እንዲደሰቱ፣ እንዲገረሙ፣ እንዲቆዝሙ፣ እና እንዲማሩ በትኅትና እጋብዛለሁ። እመው እና አበውም፣ በሕይወት ዘመናቸው ያዩትንና የሰሙትን እንዲጽፉልን፣ ወይም ደግሞ በዘመናዊዎቹ የድምጽና የምስል መቅረጫዎች እንዲያቀርቡልን አደራ እላለሁ!

ፊቃደ አዘዘ
በ «የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት»፣ መምህር
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

መጋቢት 8 ቀን 2001 ዓ.ም.

# ምዕራፍ 1

## የልጅነቴ ዘመን

**ስለተወለድሁበት ዘመንና ስፍራ፣ ስለ እምቧጮ ቁላ፣ ስለ መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ መግደላዊት ጠበል፣ ስለ እምዬ በሰሙ፣ የፊደል ትምህርት ስለመጀመሬ**

### ስለ ተወለድሁበት ዘመንና ስፍራ

እኔ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ዕለተ ልደቴ መጋቢት 17 ቀን 1891 ዓ.ም. በዕለተ ቀዳሚት መሆኑን ወላጆቼ ነግረውኛል። አባቴ አለቃ ወልደ ቂርቆስ አልታመን፣ እናቴ ወይዘሮ የሸዋ ወርቅ ምናጣ ይባላሉ። የተወለድሁት ጅሩ ቁላ ውስጥ እምቧጮ መግደላዊት በምትባል ስፍራ ነው። ክርስትና የተነሣሁትም በዚሁ በመግደላዊት ቤተ ክርስቲያን ሚያዝያ 25 ቀን የፋሲካ ረቡዕ 1891 ዓ.ም. መሆኑን እናቴ አስረድታኛለች።

የተወለድሁበት ቀን መጋቢት 17 የአልዓዛር የዕረፍቱ መታሰቢያ በዓል ስለመሆኑ በስንክሳር ተጽፎ ይገኛል። በተጨማሪም እኔ ክርስትና የተነሣሁበት ቀን የፋሲካ ረቡዕ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የአልዓዛር በዓል ተብሎ የሚከበርበት ቀን ነበርና ከእነዚህ ከሁለቱ ምክንያቶች የተነሣ የክርስትና ስሜ አልዓዛር እንዲባል አባቴ ከደብረ ሊባኖስ መልእክት ስለላኩ አልዓዛር ተብሎ ተሰየመ።

አባቴ በዚያ ጊዜ መዝገበ ድጓ (ዜማ) እያስተማሩ ደብረ ሊባኖስ ላይ ነበሩ። እናቴ ወደ እምቧጮ የመጣችበትም ምክንያት የአባቴ ታላቅ እኅት እመዬት በሰሙ መኖሪያዋ በዚህ አገር እምቧጮ ስለነበረና የእኔ መወለድና ማደግ በእርስዋ ዘንድ እንዲሆን አባቴ ስለተመኙ ነበር። እምዬ በሰሙ በዚህ የምትኖረው የባልዋ የመምሬ ወሰን መሪ የትውልድ አገር በመሆኑ ነው እንጂ የእርስዋና የአባቴስ የትውልድ አገር ላምዋሻና እንጀራ[1] ነበር።

እምቧጮ መግደላዊት ጥንታዊት ታቦት ናት። በግራኝ ወረራ ዘመን በ1530 ዓ.ም. ግድም ቤተ ክርስቲያኗ በተቃጠለ ጊዜ እምቧጮ ሸለቆ ውስጥ በትልቅ ገደል ሥር ከሚገኝ ከአንድ ዋሻ አስገብተዋትና በዚያው በዋሻው ውስጥ ቤተ መቅደስ አበጅተውላት ትኖራለች። የአገሩም ተወላጆች ቀድሞ በግራኝ ጊዜ፣

---

[1] ሲነበብ ጀ ይጠብቃል።

ኋላም በኦሮሞዎች ወረራ ምክንያት ከጅሩ ደጋ እየሸሹ ቤታቦቷ አካባቢ የሰፈሩበት ዋሻ በዚያው በገደሉ ዙሪያ ይገኛል፡፡ ለማስረጃም የሰዎቹ ምግብ ማብሰያና የመኝታ ክፍል የከብቶቻቸውም ጋጣ ዛሬም በዋሻው ውስጥ ተለይቶ ይታያል፡፡



*1 መግደላዊት የዋሻው ውስጥ መቅደስ*

እኔ በተወለድሁበትና በነበርሁበት ዘመን ሰዎቹ ዋሻውን ለቀው እታች አዘብጡ በየእርሻቸው ላይ በሠሩት ቤት ውስጥ ተቀምጠው ነበር፡፡ ታቦቷ ግን እዚያው እዋሻው ውስጥ ነበረች፡፡ ክርስትና የተነሣሁትም እንደዚህ ባለ የዋሻ ቤተ መቅደስ ነው፡፡ በልጅነት ዓይኔ ያየሁት ያ የዋሻ ቤተ መቅደስና ሽማግሌዎቹ ቄሶች እነ መምሬ እንዳዘናው፣ እነ አባ አንተን አየሁ፣ አክስቴ እምዬ በሰሙና ባለቤትዋ መምሬ ወሰን መሪ የነበሩባቸው መንደሮች በጣም ትዝ ይሉኛል፡፡

## ስለ እምቧጮ ቈላ

ስለ እምቧጮ ቈላ አቀማመጥ ትንሽ መግለጫ እጨምራለሁ፡፡ በቀድሞ አነጋገር ሸዋ ሜዳ አሁን ግን ጅሩ የሚባለው አገር ለእምቧጮ ደጋው ነው፡፡ በእምቧጮ በኩል የደጋው አፋፍ መስቀለሶስ ይባላል፡፡ ከገደሉም በታች ዛጉራ፣ ዳኖት የተባሉ ሰፋፊ ቀጣናዎች[2] አሉ፡፡ እነዚህ ቀጣናዎች ለእርሻ

[2] ሽንጡ ቀጠን ብሎ የረዘመ መሬት፡፡



የሚመች መሬትና ውሐ ስለአለባቸው ብዙ ሕዝብ ይሰፍርባቸዋል፡፡ ቅብርያል የሚባለውም ታሪካዊ ዋሻ የሚገኘው በዛጉራ ደቡብ በኩል ሆኖ የዛን ወንዝ ፏፏቴ በሚወርድበት ላይ ነው፡፡



2 ቅብርያል ዋሻ

የዋሻው ስም ቅብርያል የተባለበት ምክንያት በአጼ ሱስንዮስ ጊዜ ቅብርያል የተባለ ሰው ዋሻውን እንደ ምሽግ አድርጎ ከነጓዙ ተቀምጦበት ስለነበረ ነው፡፡ የበደበጅ ባላገር ግን ታሪኩ ጠፍቶበት "ቅብርያል የተባለ ቀይ ትልቅ ዘንዶ ነበረበት አሉ" እያለ በመላ ሲያወራ ሰምቻለሁ፡፡ ቅብርያልን ካነሣሁ ዘንድ ስለ ታሪኩ ጥቂት መግለጫ መስጠት ይገባኛል፡፡

ቅብርያል አንድ ኦርቶዶክሳዊ የግብጽ ሰው ነው፡፡ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ ወልደ ቅብርያል ይለዋል፡፡ በቅብጥ ቋንቋ ቅብርያል ማለት ገብርኤል ማለት ነው፡፡ ይህ ሰው በኢትዮጵያ የነበረው በአጼ ሱስንዮስ ጊዜ ነው፡፡ አጼ ሱስንዮስ ካቶሊክ በሆነ ጊዜ ለጥንታዊው ኦርቶዶክስ ሃይማኖት የተቈረቈረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቈጥቶ ሸፈተበትና በየስፍራው የሃይማኖት ጦርነት አነሣበት፡፡ በተለይም ደጃዝማች ዩልዮስ ጠዳ ላይ፣ ደጃዝማች ዮናኤል ላስታ ላይ ጦርነት ገጥመው ተዋጉት፡፡ ሆኖም ድል አድራጊው ንጉሥ አጼ ሱስንዮስ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ቅብርያል ለነዚያ ለሃይማኖት ተዋጊዎች ደጋፊያቸውና ተባባሪያቸው ስለነበረ ከሱስንዮስ ከተማ ሸሽቶ በወዳጁ በክፍለ ኢየሱስ መሪነት ወደ ሸዋ መጣ፡፡ መልዛ ላይ ሲደርስ የአጼ መልአክ ሰገድ ልጅ ነኝ ብሎ ራሱን በንጉሥ ልጅነት አስታወቀ፡፡ በዚህ ጊዜ ከመንዝና ከግሼ፣ ከመራቤቴና

ከበደበጅ፣ ከተጕለትና ከምሑይ ብዙ ሠራዊት ተሰበሰበለት። ሠራዊቱ ወዲያው ስመ መንግሥቱን «ቴዎድሮስ» ፀሐይ ብለው ስደመው አንግሠንሃል አሉትና ነጋሪት እያስመታ ንጉሥ ነኝ አለ።

አጼ ሱስንዮስ ይህን ወሬ በሰማ ጊዜ ደጃዝማች ሥርፀ ክርስቶስንና ዘማርያምን ከአምስት ጭፍራ ጦር ጋር ላከበት። ወልደ ቅብርያልም ሐያ ጭፍራ ጦር ሠራዊቱን ሰብስቦ ከተዋጋ በኋላ ድል ሆኖ አመለጠ። ሆኖም እንደገና በመራቤቴና በበደበጅ፣ በመንዝና በተጕለት፣ በሐዲስጌም ጦር ሰብስቦ ይዋጋ ጀመር። ውጊያውም በበረታበት ጊዜ ካንዱ አገር ወደ ሌላው እየተዘዋወረ አስቸገራቸው። ቅብርያል ዋሻ ብዬ ከዚህ በላይ በጠቀስሁት በዚያ ዋሻ ሰፍሮ የነበረውም በዚሁ ጊዜ ነው።

ወልደ ቅብርያል በየስፍራው እየተዘዋወረ ውጊያውን ቀጠለ። የአገሩም ሕዝብ ተሰብኮለት ነበር። ምክንያቱም አጼ ሱስንዮስ ሃይማኖት ስለለወጠ ሕዝቡ በንጉሡ ላይ ጥላቻ አብዝቶ ስለነበረ ነው። በዚህ ጊዜ ዋናው የጦር እንደራሴ፣ ራስ የማነ ክርስቶስ፣ ከብዙ ጭፍራ ጋር ወደ ሸዋ መጥቶ ወልደ ቅብርያልን ካገር ወዳገር ያባርረው ጀመር። ሊያገኘው አለመቻሉን በተረዳ ጊዜም በተንኰል ሊያስገድለው ፈለገ። ስለዚህም ኛዕ ሠርጼ የተባለውን ሰው በገንዘብ ተዋውሎ በምሥጢር ላከው።

ወልደ ቅብርያልም በ1618 ዓ.ም. ከሐዲስጌ ሸሽቶ ቁንዲ ላይ ሰፍሮ ሳለ ኛዕ ሠርጼ አሽከር ሆኖ ገብቶ ያገለግለው ጀመር። በአገልግሎቱም ደስ ስላሰኘው ባለሟልና አማካሪ አደረገው። ከዚህ በኋላ ወልደ ቅብርያል ከቁንዲ ወደ ፈጠጋር ተዛውሮ ሳለ ኛዕ ሠርጼ ጠለታ ከሚባለው የኦሮሞ ጐሣ ጋር በገንዘብ ተስማምቶ በድንገት አስገደለው። ራሱንም ቈርጦ ለራስ የማነ ክርስቶስ ላከለት። ራስ የማነ ክርስቶስም የራስ ቅሉን ቆዳ ከነጺሙ አስገፍፎ ለአጼ ሱስንዮስ ወደ ስሜን ላከው። በዚያ ጊዜ አጼ ሱስንዮስ ስሜን ላይ ነበረ።


እነሆ ታሪኩን ባጭሩ ጽፌአለሁ። ነገር ግን በሙሉ ለማወቅ የሚፈልግ ቢኖር አዛዥ ጢኖ በጻፈው በአጼ ሱስንዮስ ታሪክ ውስጥ ከምዕራፍ 72 እስከ 77 ላይ የሚያገኘው መሆኑን እገልጻለሁ። እንግዲህ ወደ ታሪኬ እመለሳለሁ።

ከዛጕራ በታች አንድ ትልቅ ገደል ይገኛል። ይህ ገደል የማርያም መግደላዊት የዋሻ መቅደስ የሚገኝበት ነው። በስተደቡብ ዛን የተባለ ወንዝ አለ። ወንዙ በበጋ ወራት መጠነኛ ወይም አነስተኛ ውሐ ይወርድበታል። በክረምት ግን ከሸዋ ሜዳ (ከጅሩ) የሚሰበሰበው ጎርፍ ትልቅ ጅረት ያደርገውና በቅብርያልና በእምባጮ ገደል ላይ ቁልቁል እየተወረወረ ሲወርድ የፏፏቴው ድምፅ ቀበሌውን ሁሉ ያስገመግመዋል።

እምቧጮ ሸለቆ እንደመሆኑ መጠን ሞቃት ነው። ከዚህም በላይ፣ ቍጥቋጦና ጫካ እንዲሁም ጉራንጉር ነገር ስለሚበዛበት ተንቀሳቃሾች እነ ዘንዶና እነ እባብ፣ አውሬዎች እነ ነብርና እነ አነር ይገኙበታል። በተለይም የዛን ወንዝ



አካባቢ የእነርሱ ሰፈር ነው። ባላገሩ ዘንዶውን፣ እባቡን ወይም ነብሩን ጕዳይ ስለማይለው በዱላም ሆነ በጦር እየቀጠቀጠ ይከላከለዋል። የፀሐይ ሐሩር በጠነከረበት ዘመን ግን ዘንዶው ያይልና መንገድ ተላላፊዎችን እየጠበቀ ይውጣቸው ነበር።




1 ጅሩ

በሸለቆው ውስጥ ለእርሻ የሚጠቅመው መሬት በመጠኑ ነው። ያንኑም ተወላጆቹ ድርሻ ድርሻቸውን ተከፋፍለው ያርሱታል። አብዛኛው ሰብላቸው ማሽላና ጤፍ፣ ሱፍና ጥጥ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። ሎሚ በየጫካው ውስጥ ወፍ አራሽ[3] ሆኖ ይበቅላል። በተጨማሪም እንኮይ፣ ገባ፣ ሸዮ፣ ሾላ፣

[3] ወፍ ፍሬውን አርቶት ወይም በውሐም በንፋስም ኃይል ሄዶ በዱር የበቀለ።

የሚባለውን የመብል ፍሬ የሚያፈሩት ዛፎች በየጫካው በብዛት ይገኛሉ። የሆነ ሆኖ በቂ የእርሻ መሬት ስለሌለ አብዛኞቹ ሰዎች ወደ በደብጅና ወደ ሽማ ቄላ እየተሰማሩ (መቼም በየስፍራው ተወላጅነት አያጡምና) በየርስት ድርሻቸው ወይም በተጋኝነት እያረሱ የዓመት ቀለባቸውን በድካም ይሰበስባሉ። በድካማቸው ከሚያገኙትም ላይ አውሬዎች እነ ጥቁሬ ዝንጀሮ፣ እነ ነጭ ዝንጀሮ፣ እነ ጦጣ፣ የሰማይ ወፎች እነ ጨረባ፣ እነ ምማይ፣ እነ ርግብ፣ የሰብላቸው ተካፋዮችና በላተኞች ናቸው። የልፋታቸውን ሁናቴ ስመለከተው፣ «ብላዕ በሐፈ ገጽከ»[4] ተብሎ ለአዳም የተነገረውን ቃል የፈጸሙ የዚህ አገር ሰዎች ናቸው።

እኔ የተወለድሁበት ቄላ እንዲህ ያለ ነበር ለማለት እስከዚህ ድረስ ዘረዘርሁ፣ እንግዲህ ሌላውን እቀጥላለሁ።

## ስለ መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን

እኔ ከተወለድሁ ከሦስት ዓመት በኋላ፣ (ምናልባት በ1894 ዓ.ም.) የአጥቢያው ሕዝብ በበደብጅ ውስጥ በሐ በሚባል ስፍራ ላይ አንድ ጥሩ ቤተ ክርስቲያን በጭቃ ግንብና[5] በሣር ክዳን አሠራና ታቦተ ማርያም መግደላዊትን ከዚያ ከዋሻው መቅደስ አውጥቶ ከዚያ ላይ ተከላት። እምቢጮ ላይ የነበረውም ሕዝብ ጥቂት ብቻ ሲቀር አብዛኛው ታቦቲቱን ተከትሎ በሐ ላይ ሰፈረ።

በዚያ ጊዜ የተሠራው የቤተ ክርስቲያኑ ግንብ አሁንም መልኩና ቅርጹ ሳይለወጥ በዚያው በቀድሞው ዓይነት ይገኛል። ጣሪያው ግን አሁን በቅርቡ በቆርቆሮ ክዳን ተከድኗል። ቤተ ክርስቲያኒቱ የተሠራችው በደልዳላ ቦታ ላይ ሆኖ በስተምሥራቅ በኩል እንደ አጥር ተገን፣ ከለላ የሆነላት ገደል አለ። ገደሉ በሐ[6] (ብኻ) ድንጋይ ነው። የስፍራው ስም በሐ የተባለውም በዚህ ምክንያት ነው።

የማርያም መግደላዊት የዓመት በዓል የሚከበረው ሚያዝያ 28 ቀን ነው። በዚህ ቀን ካህናቱ በዘመነ ፋሲካ ድጓ ስለ አንስት የተጻፈውን አንድ አንገርጋሪ[7] አምጥተው በማኅሌት ላይ እያዜሙ ያሸበሽባሉ። አንገርጋሪውም ይህ ነው።

ኢየሱስ ቆመ ማእከለ የማና፣ ወኢያአመረቶ»[8]

[4] በላብህ በወዝህ ጥረህ ግረህ ብላ።


[5] ግንብ ሲገነባ እንደ ሲሚንቶ አድርገው የሚጠቀሙበት ጭቃን ነበር። ቀይ ወይንም ጥቁር አፈር ከጭድ፣ ጭድ ከሌለም ከስንዴና ከገብስ ገለባ ጋር ተደባልቆ ከአራት እስከ ስምንት ሳምንታት በተወሰነ ቀን እየተገላበጠ፣ እየተረገጠ ይቦካል። ከዚያም ግንቡ በድንጋይና በተቦካው ጭቃ ይገነባል፣ የእንጨት ቤት ከሆነም በግድግዳው ላይ ይለጠፋል፣ ሲደርቅም ይለሰናል።

[6] በቀላሉ የሚሰበር ድንጋይ ዓይነት።

[7] መሪው ከቃኘው በኋላ በቅብብሎሽ የሚዘመር ዜማ።



ከመ ክርስቶስ ውእቱ። ተናገራ ኢየሱስ
ወይቤላ ማርያም መግደላዊት በሐ



3 መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን

በአንገርጋሪው መጨረሻ «በሐ» የሚለው ቃል በአጋጣሚ ከስፍራው ስም ጋር ተመሳስሎ ስለተገኘ ሕዝቦቹ የመንደራቸው ስም የተሞገሰ እየመሰላቸው እልልታውን ያቀልጡት ነበር። እኔም ራሴ እንደዚሁ አስብ ነበርና በዚያ ጊዜ ተሞኝቻለሁ። ሌሎች ጓደኞቼም አስተሳሰባቸው በዚሁ ዓይነት ነበር። ለዚሁም ማስረጃ አጥቢያውና መኖሪያው ሽማ ገብርኤል ላይ የሆነ ጓደኛ ነበረኝ። የአጥቢያው ታቦት የተተከለበት ስፍራ ኢከፈሮ ይባላል። እኛ መግደላዊት በሐ እያልን እያዜምን ስንጨፍር (መቼም ዜማው በሁላችን ዘንድ የተለመደ ሆኗልና) ጓደኛዬ ደግሞ አጥቢያውን ለማሞገስ "ገብርኤል ኢከፈሮ" እያለ ይጨፍር ነበር።

[8] ትርጉሙ
ኢየሱስም በቀኝ በኩል ቆመ
እርሷ ግን ክርስቶስ እንደሆነ አላወቀችውም።
ኢየሱስ ተናገራት፣ እንዲህም አላት
ማርያም መግደላዊት እንዴት ነሽ?።
ምሥጢሩ
አንገርጋሪው ጌታችን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በመጀመሪያ የተገለጠ ለመግደላዊት ማርያም መሆኑን በተገለጠላትም ጊዜ ለእርስዋና ለሌሎች ቅዱሳት ሴቶች «ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ ደስ ይበላችሁ!» ማለቱን ያመለክታል። (ማቴ. 28፤ 1-9፤ ዮሐ. 20 11-18)

## ስለ መግደላዊት ጠበል



4 መግደላዊት ጠበል

የመግደላዊት ቤተ መቅደስ እምቧጮ ባለው በገደሉ የዋሻ መቅደስ ውስጥ ስለመሆኑ ባለፈው ተናግሬአለሁ:: አሁን ደግሞ ስለ ጠበሉ ሁናቴ መግለጫ እሰጣለሁ:: በዚያ በዋሻው መቅደስ ውስጥ ከአለት ድንጋይ የሚመነጭ አንድ ምንጭ አለ:: ማርያም መግደላዊት በተአምራት አፈለቀችው ተብሎ የሚታመንበት ጠበል ነው:: ጠበሉ የሚፈውሰው እንቅርታሞችን ብቻ ነው:: እንቅርት ይፈውሳል (ያሟሽሻል) ተብሎ በብዙ ይታመንበታል:: ይሁን እንጂ ጠበሉ ሊፈውስ የሚችለው ከመግደላዊት አጥቢያ ውጭ የመጣውን እንቅርታም ነው እንጂ በዚያው በአጥቢያው ውስጥ ያለውን አይፈውስም ይባላል:: እስከዛሬም ድረስ ይኸው ታሪክ እንደ ቀጠለ ነው:: እኔ ቀድሞ ሕፃን ሳለሁ ታሪኩ ያስደንቀኝ ነበር:: ካደግሁ በኋላ ግን ምክንያቱን መርምሮ ማወቅ እንደሚያስፈልግ ስለ ተረዳሁ አንዳንድ ሰዎችን ብጠይቅ "ታይሮይድ የሚባለው ዕጢ በሙሉ ወይም በክፊል ሲያብጥ እንቅርት ይባላል" አሉኝ የሚያብጥበትን ግን ተመራማሪዎች ዛሬም ቢሆን በመላው አልተስማሙበትም :: አዮዲን የተባለ ጥንተ ንጥር ከሰውነት ባነሰ ጊዜ እንቅርት ይመጣል የሚሉ ብዙዎች ናቸው:: ሌሎች ደግሞ ከአንዳንድ ተራራማ አገር የሚመነጭ ውሐ እንቅርት ያስይዛል ይላሉ:: በዘር የሚተላለፍ ሕመም ነው ሲሉ የሚያምኑበትም አይታጡም፣ ነገሩ ብዙ ያከራክራል ይሉኛል:: የመግደላዊት ሰዎችም ስለ እምቧጮ ጠበል ያላቸው የተለየ አስተያየትም ለነገው ዕውቀት መነሻ ሊሆን ይችላልና ለሰማሁት ሁሉ የታመነ የሳይንስ ማፍረሻ ሳላገኝለት ለምን አድናቆቴን ልንፈጋቸው ብዬ ምርምሬን አቆምሁ::



## ስለ እመዬት በሰሙ ከማስታውሰው በጥቂቱ

ዕድሜዬ አምስት ዓመት ከመንፈቅ እስኪሆን ድረስ የነበርሁት ማርያም መግደላዊት በተባለች ቦታ በሐ ላይ ነው:: በዚያ ጊዜ ዘመዶቼ ያወጡልኝ የመጠሪያ ስሜ ዓባይነህ ነበረ:: ያሳደገችኝ የአባቴ ታላቅ እኅት እመዬት በሰሙ ናት:: እኔን ልጅ አድርጎ ለማሳደግ የፈለገችበትን ምክንያት ከመግለጼ በፊት ስለ እምዬ በሰሙ የኑሮ ሁናቴና ስለ ጠባይዋ በአጭሩ እገልጻለሁ::

በሰሙ ለአባቴ በእናትም በአባትም የማትለይ የሦስት ጊዜ ታላቅ እኅት ናት:: መምሬ አልታመን (ስመ ጥምቀቱ ወልደ ኢየሱስ) ከላምዋሻ አቦ የቄስ ደፈርን ሴት ልጅ እስታሉን አግብቶ ዓሥራ ሁለት ልጆች ወለደ:: ከነዚሁም ስምንቱ ለትዳርና ለንብረት ሳይደርሱ ሞተዋል:: የቀሩት አራቱ ግን ለትዳርና ለንብረት ደርሰው የነበሩት ናቸው:: እነርሱም አንደኛ በሰሙ፣ ሁለተኛ ወሉተ ወልድ፣ ሦስተኛ ወለተ ሚካኤል፣ አራተኛ ወልደ ቂርቆስ ናቸው::

በሰሙ (ስመ ጥምቀቷ ወለተ ጊዮርጊስ) የተወለደችው በ1836 ዓ.ም. ግድም ነው:: አባቴን 12 ዓመት ያህል ትበልጣለች ይባል ስለነበረ የዓመተ ምሕረቱን ግምት የወሰድሁት በዚህ መንገድ ነው::* ለአካለ መጠን በደረሰች ጊዜ ወሰን መሪ ለተባሉ ሰው ተዳረች:: እርሳቸውም በመግደላዊት አጥቢያ የበደበጅና የእምቧጮ ተወላጅ ናቸው:: መምሬ ወሰን መሪ ለበሰሙ እንደ አባት ያክል ነኝ፣ በልጅነትዋ አግብቼ አሳድጌያታለሁ እያሉ ሲጫወቱ በልጅነቴ የሰማሁት ትዝ ይለኛል:: በጨዋታም ላይ ስለ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ያናገሩ ነበር:: በእኔ ግምት መምሬ ወሰን መሪ በሰሙን ከ17 ዓመት ያላነሰ ዘመን እንደሚበልጧት አስባለሁ::

መምሬ ወሰን መሪ ቅስና ስለተቀበሉበት ዘመን ሲናገሩ፤ "በአጼ ቴዎድሮስ ጊዜ ከአቡነ ሰላማ ቅስና ለመቀበል ወደ ጐንደር ስሄድ አገሩ ሁሉ ሽፍቶ ነበርና መተላለፊያ መንገድ አጥቼ ተመለስሁ:: አጼ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ግን አቡነ አትናቴዎስ የተባሉ ጳጳስ መጥተዋል ማለትን ብሰማ በቶሎ ወደ መቀሌ ሄድሁና ከእርሳቸው ቅስና ተቀበልሁ" ይሉ ነበር::

እመዬት በሰሙና መምሬ ወሰን መሪ ሁለት ሴቶች ልጆች ወልደው ነበር:: እነርሱም አድገውና ተድረው ቤት፣ ንብረት ከያዙ በኋላ፤ አንዲቱ በወሊድ ሁለተኛዪቱም በበሽታ ስለሞቱባቸው የወላድ መካኖች ሆነዋል:: ሁለቱም ልጆቻቸው የሞቱት ዘር ሳይተኩ ስለሆነ፣ ከኀዘን ለመጽናኛ የሚሆን የልጅ ልጅ እንኳን ባለማግኘታቸው፣ ሁለቱም ያዝኑ ነበር:: እኔም ሕፃን ሳለሁ እያስከተለችኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሄደች ቍጥር በልጆችዋ መቃብር አጠገብ እየተቀመጠች በመሪር ኀዘን ስታለቅስ የነበረው ትዝ ይለኛል::

---

* አባቴ የተወለዱት በ1848 ዓ.ም. ነበር:: (መ.ኀ.ጠ.ቂ)

እንግዲህ እኔ የተወለድሁት ልጆችዋ ሁሉ ሞተው ኀዘን ከተጫናት በኋላ ነው። እኔን ልጅ አድርጋ ለማሳደግ ከእናቴ የተቀበለችውም የልጆችዋ ምትክ እንድሆንላት በመመኘት ነው፣ የእምዬ በሰሙ ደግነትና ርኅራኄ እጅግ ከመጠን ያለፈ ነው፣ ቤትዋ ወደ ጅሩ በሚያስወጣው በአውራው መንገድ ዳር ስለነበረ በዚያ በኩል የሚያልፍ ቆለኛ ከቤቷ ገብቶ ሳይበላና ሳይጠጣ የሚሄድ አልነበረም። ከደግነትዋም የተነሣ አራስ ውሻ እንኳ ያየች እንደሆነ አነባበሮ[10] ጋግራ ትወስድላት ነበር። የአገሩም ሰው ትልቁም ትንሹም ስምዋን የሚጠራው እምዬ በሰሙ እያለ ነበር። እኔንም ስታሳድግ የነበረባት ድካም እጅግ ብዙ ነበር።

በልጅነቴ እርሷን ካስቸገርሁባቸው ነገሮች አንዳንዶቹን በሚከተለው እገልጻቸዋለሁ።

በክረምት ወራት ጎርፍ በመንገድ ላይ ሲሄድ ያየሁ እንደሆነ ከእምዬ በሰሙ ጓዳ ድልህ እየዛቅሁ እወስድና ከጓደኞቼ ጋር በጎርፍ እየበጠበጥን እንጫወት ነበር። ደስታችንም ጎርፉ ቀይ ሆኖ ሲወርድ ማየታችን ብቻ ነበር።

እንዲሁ ደግሞ በፀሐይ እንዲደርቅ የሚሰጣውን የወፍጮ እህል ስበታትንና ለወፎች ስመግብ ደስ ይለኝ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን እምዬ በሰሙ ከመሳምና ከማባበል በቀር በምንም ነገር አታስቀቅኝም ነበር።

## የፊደል ትምህርት ስለመጀመሬ

አራት ዓመት ከሞላኝ በኋላ የትምህርት መጀመሪያዬ ጊዜ ደረሰ። ከበሐ መንደር ወደ ምዕራብ ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሚገኝ ገና መምቻ በሚባል መንደር የሚያስተምር ደብተራ እንደብልሃቱ የሚባል አስተማሪ ነበረ። ሰውዬው ጓያ የሰበረው[11] አንካሳ ነው። ዋና አስተማሪነቱ ፊደል ለማስቈጠርና ዳዊት ለማስደገም ሲሆን፣ በተጨማሪ ከተጕለቴ ዜማ[12] እንደ ሰዓታት ያለውን ያስተምራል። በዚያ ጊዜም ከአምሳ ያላነሱ ትንንሾችና ትልልቆች ተማሪዎች ነበሩት።

ዕድሜዬ አራት ዓመት ከአራት ወር ከአራት ቀን ሲሆን እምዬ በሰሙ ወደ ደብተራ እንደብልሃቱ ወስዳ ለትምህርት አስገባችኝ። የቀኑ ልክ ይህን ያህል ተጠንቅቆ የተጠበቀበት ምክንያት በአራት ዓመት ከአራት ወር ከአራት ቀን ትምህርት የሚጀምር ልጅ ትምህርት ይቀናዋል የሚል አስተሳሰብ በዚያ ዘመን ስለነበረ ነው።

መጀመሪያ እንደ ገባሁ የዕድሜ እኩዮቼን በአንድነት ተሰብስበው በማየቴ ደስ አለኝና ለጨዋታው ስል ለጥቂት ሳምንታት ሳልሰለች ተመላለስሁ። እንግዲህ ፊደል ተጀመረ። ፊደሉም በሚጠቀለል ብራና በጉልህ ተጽፎ ከዲልዲላ ከአባቴ ዘንድ የተላከልኝ ነበር። አባቴ በዚያን ጊዜ ዜማ እያስተማሩ ዲልዲላ ማርያም ነበሩ። ይኸውም እንጦጦ ማርያም ማለት ነው። በዚያ ጊዜ ዲልዲላ ወይም እንጦጦ እየተባለ በሁለት ስም ይጠራ ነበር።

ደብተራ እንደብልሃቱ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀኖች እርሱ ራሱ ፊደሉን አስጀመረኝ። በኋላ ግን በወምበር ገፍ[13] ሌላ ፊደል አስቈጣሪ አዘዘልኝና ተማር ተባልሁ። አስተማሪው ወደ ፊደሉ ሲያመለክተኝ የኔ ዓይን የሚያየው ወደ ልጆቹ ጨዋታ ብቻ ነበር። እስከሰማመድ ድረስ ጥቂት ቀን ታገሠኝና ከዚያ በኋላ "ፊደሉን እያየህ ተማር" እያለ በቁንጢጥ ያደብነኝ ጀመር። ደብተራ እንደብልሃቱም ተማሪዎቹን የሚቀጣበት አንዲት አለንጋ ነበረችውና ያችን እየወዛወዘ "ኋላ አይሆንም አቀምስሃለሁ፣ ፊደሉን እያየህ ተማር" ብሎ አስፈራራኝ። እኔም ያን ልማዴን አልተውሁ ስላልሁ በዚያች አለንጋ ይሸነቁጠኝ ጀመር። ከዚያ በኋላ ትምህርት የተባለውን ነገር በፍጹም ጠላሁና ወደ ተማሪ ቤቱ አልሄድም ብዬ ዘመዶቼን አስቸገርሁ። እነርሱም እየደበደቡና በግድ እየጎተቱ ወሰዱኝ። ይሁን እንጂ ጥላቻው እየባሰብኝ ሄደና ፊደሉን ብቻ ሳይሆን የትምህርት ጓደኞቼን እንኳን ለማየት እስከ መጥላት አደረሰኝ።

እንዲያውም ፊደል ተማር የሚሉኝ ከሆነ በበደበጅ ገደል ኝው ብዬ እገባለሁ እያልሁ ለጓደኞቼ እጫወትላቸው። በተለይም ሣህሌ እንደብልሃቱ የሚባለው የአስተማሪዬ ልጅ የቅርብ ጓደኛዬ ነውና ገደል ልገባ ነው ብዬ በቁም ነገር አማክርሁትና እንላቀስ ጀመር። ሣህሌ የአስተማሪዬ ልጅ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የዕድሜዬ እኩያዬ ስለሆነ በጣም እንፋቀር ነበር። የበደበጅ ገደል የሚባለውም ከቤታችን በስተምዕራብ የሚገኝ ሁለት መቶ ሜትር ያህል ርዝመት ያለው ትልቅ ገደል ነው።

[10] ሦስት እንጀራ ተነባብሮ ተጋግሮ በሁለቱም በኩል ዓይን ያለው። ቅብዓ ኑግ፣ ቅቤ ወይም ዘይት በድልህ ይመታና አነባበሮው ላይ ይለቀለቃል እምጣዱ ላይ እንዳለ።


[11] ጓያ የጥራጥሬ ወይም የእህል ዓይነት ነው። ጓያ ከየትኛውም የጥራጥሬ ወይም የእህል ዓይነት በተሻለ ድርቅን ተቋቁሞ ለሰው ምግብነት ወይም ለከብት መኖነት የሚያገለግል በችግር ቀን ደራሽ ነው። በጓያ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ፕሮቲን ይገኛል። በጓያ ውስጥ የሚገኙት የፕሮቲን ገንቢ አካል አሚኖ አሲዶች ነርቭ አጥቂ የሆነ ጠባይ ወይም ባሕርይ አላቸው። እነዚህ በጓያ ውስጥ የሚገኙት ንጥረ ነገሮች የመቀመጫና የእግር ጡንቻዎችን የሚያንቀሳቅሱትን የነርቭ ሴሎች በማጥቃት ጓያ ተመጋቢ ሰዎችን ለሽባነት ሊዳርጉ ይችላሉ። በዚህ የተነሣ ጓያ በመመገብ ሽባ የሆነ ወይም የተሽመደመደ ሰው ጓያ የሰበረው ተብሎ ይጠራል። ምንጭ - ዶክቶር አሰፋ ነጋሽ።

[12] የዜማ ስልት በየጊዜው በታላላቅ መምህራን በጥቂቱ ተለውጧል። የዜማውም ስልት በለወጡት መምህራን ወይንም በሀገራቸው ስም ይጠራል። ስማቸውም ተጕለቴ (የተጕለት ዜማ)፣ ቤተልሔም (የቤተልሔም ዜማ)፣ ቆሜ (የቆሜ ዜማ)፣ ወንጨሬ (የወንጨሬ ዜማ)፣ አጫብሬ (የአጫብር ዜማ) ነው።



[13] ቀተከ፣ አንድ መጽሐፍ ብቻ ኖሮ ብዙ ልጆች በዛ መጽሐፍ በተራ ሲማሩ።

ከዚህ በኋላ አሳቤ ሁሉ ገደል ለመግባት ወይም ወደ እናቴ ዘንድ ለመኰብለል ብቻ ሆነ። እናቴ ወይዘሮ የሸዋ ወርቅ ያለችው መስቀለሶስ በሚባል በደጋው አፋፍ ላይ መሆኑን ዐውቅ ነበር። አንድ ጊዜም ከእምዬ በሰሙ ጋር ወደዚያው ወጥተን ነበርና መንገዱን ለአንድ ጊዜ አይቼዋለሁ። በጉዳዩ ካሰብሁበት በኋላ ገደል ገብቶ መሞት አስፈራኝና ወደ እናቴ ቤት መኰብለልን መረጥሁ። መስቀለሶስ የተባለው ስፍራ የጥንት ስሙ መስቀለ ክርስቶስ ነው። እስከ ግራኝ ወረራ ድረስ መስቀለ ክርስቶስ የሚባል ቤተ ክርስቲያን ነበረበት። ግራኝ አጥፍቶታል። አሁን ግን በስፍራው ላይ አንድ አርጌ የወይራ አጸድ ብቻ ይገኝበታል።



5 የበደበጅ ገደል

አንድ ቀን ወደዚያ ተማሪ ቤት ሄጄ ዋልሁና ለምሳ ተመለስሁ። ምሳ ከበላሁ በኋላም ወደ ተማሪ ቤት እንደምሄድ ዓይነት ከቤት ወጣሁና ሽቅብ ወደ መስቀለሶስ ጉዞ ጀመርኩ። ከኋላዬ የሚይዘኝ ሰው የተከተለኝ እየመሰለኝ በየጊዜው እገላመጥ ነበር። የመጀመሪያውን ዳገት ወጥቼ ዳኖት ከሚባለው ቀጣና ደረስሁ። ይኸውም የእነመምሬ አብቴና የነአቶ ሳቀው መንደር ነው። የመንደሩ ሰው እንዳያየኝ የሚጥሹን ቅጠል ከለላ እያደረግሁ ሁለተኛውን ዳገት ተያያዝኩት። በዚያ በገረረ የፀሐይ ሙቀት ስለተዳከምኩ አለክልክ ነበር። የሆነ ሆኖ ለመመለስ ተስፋ አልነበረኝምና ማረፊያ ከሚባለው ከላይኛው ቀጣና አፋፍ ደረስሁ። ይህ ስፍራ መንገደኞች ብርቱውን ዳገት ጨርሰው የሚያርፉበት ቦታ ነው። እኔም እዚያ ስደርስ ከፀሐይ ሙቀት እንዲጋርደኝ የትልቁን ቋጥኝ ጥላ ተገን አድርጌ ተጋደምሁ። አንድ ሰዓት ያህል እዚያ ተኝቼ እፎይ ካልሁ በኋላ፣ የቀረኝን መንገድ ቀስ በቀስ ተጉዤ ማታ ለዓይን ሲይዝ መስቀለሶስ ከእናቴ ቤት ገባሁ።



እዚህ ላይ መግለጥ የሚገባኝ አንድ ነገር አለ። እናቴ በዚያ ጊዜ ባሻ ዳምጠው የተባሉትን የመንግሥት ነፍጠኛ[14] አግብታ መስቀለሶስ ላይ ነበረች። አባቴና እናቴ ከሁለት ዓመት በፊት ተፋትተው ነበርና።

እናቴ ባየችኝ ጊዜ በድንጋጤ ተቀብላ የጓጉለውን ሰውነቴን በቅቤ አሻሸችልኝ። ለእናቴ የሰጠሁትም ምክንያት ስለ ናፍቆት እንደመጣሁ እንጂ ኰብልዬ ስለመምጣቴ አልነበረም። እርሷም እኔን በማግኘትዋ ደስ ብሏት ነበርና ደኅና መድረሴን ለአክስቴ ማስታወቅን እንኳ ሳታስታውስ ቀረች።

እምዬ በሰሙ እኔ ከቤት በወጣሁ ጊዜ ለትምህርት ወይም ለጨዋታ ጓጉቼና ቸኩዬ የሄድሁ መስሏት ነበር። ወደማታ ጓደኞቼ በየቤታቸው ሲመለሱ እኔ ሳልገባ ስቀር ጊዜ ምናልባት ለጨዋታ ሲል ዘግይቶ ይሆናል በማለት ትጠባበቅ ጀመር። ነገር ግን ፀሐይ ጠለቀች፣ ጊዜውም መሸ፣ በዚህ ጊዜ አንድ መላእክተኛ ወደ ደብተራ እንደብልሃቱ ቤት ላከችና ብታስጠይቅ ከምሳ በኋላ በጭራሽ አልተመለሰም፣ አላየነውም የሚል መልስ አመጣላት። ጓደኞቼንም በየመንደሩ እየዞረች ብትጠይቅ "አላየነውም ከእኛ ጋር አላመሸም" እያሉ መለሱላት። በመጨረሻም ከማህሌ እንደብልሃቱ ጋር ያለኝን ፍቅር ታውቃለችና እርሱን ጠይቂልኝ ብላ ሰዎች ላከች። እርሱም ዛሬ ከምሳ በኋላ አልተገናኘንም ካለ በኋላ "እረ አንድ ጊዜ ገደል ልገባ ነው ብሎ አማክሮኝ ነበር" ብሎ ምሥጢሩን አወጣላቸው። ይህ ወሬ ለእምዬ በሰሙ በደረሳት ጊዜ መጮህና ማልቀስ ሆነ። የመንደሩም ሰዎች ተሰብስበው ያላቅሷት ጀመር። አክስቴ ዘነበችና አጎቴ የሻላ ወልደ ሐና፣ የአክስቴ ዘነበች ልጆች፣ ምንጉዳውና ኩበረት ተጠርተው እያለቀሱ መጡ። ጊዜው መሸ፣ ጨለማም ሆነ። እምዬ በሰሙ "አዬ ጉዴ ልጆቼን ሁሉ ጨረስሁ። አሁን ደግሞ ይህን ልጄን አጣሁ፣ እንግዲህስ እኔም ገደል ገብቼ እሞታለሁ" ብላ ተነሣች፤ ጓደኛዬ፣ ማህሌ በተናገረው ቃል አምናበት ነበርና። ቤተ ዘመዶቻችንም እርስዋን በመቀነት አስረው ይጠብቋት ጀመር። ደብተራ ወንድማገኘሁ የተባለ አንድ ዘመዳችን ግን "ልቀቋት ገደል ትግባ፣ እነ ደነነችን ቀበረች፣ አሁን ደግሞ አንድ ልጅ ቢተርፋት እርሱ ገደል ሲገባ ምን ትሁን! እንግዲህስ ትሙት" ብሎ የብስጭት ቃል ተናግሮ ነበር። ነገር ግን ሌሎቹ አልለቀቋትም። ደነነች የተባለችው ልጅ ከእምዬ በሰሙ ልጆች አንዲቱ ናት። በጣም ቆንጆ ስለነበረች ቤተ ዘመድ ሁሉ በየምክንያቱ ያስታውሳታል።

ከዚህ በኋላ እስቲ ገደል ገብቶ እንደሆነ ሰዎች በስርጥ[15] መንገድ ወርደው በዳቦት ይፈልጉ ተብሎ ተመከረና ዳቦት ተበርቶ ፈላጊዎች ተላኩ። ደግሞም በበደበጅ ቁላ ሳለው ለመምሬ ወሰን መሬ ወንድም፣ ለአቶ አራምዴ በአቀባይ

[14] ባለ ነፍጥ (ጠመንጃ) ወታደር፣ ነፍጥ ያለው የንጉሥ፣ የሻለቃ አሽከር። ምንጭ - ደስታ ተክለ ወልድ፣ መዝገበ ቃላት።

[15] በገደልና ገደል መሃል ያለ ጠባብ መተላለፊያ።

ጥሪ[16] ተነገረውና ወገኖቹን ሰብስቦ ዳቦትም አብርቶ የፍሊጋው ተባባሪ ሆነ። የፍሊጋው ውጤት ድካም ብቻ ሆኖ፣ ፈላጊዎቹ ወደ ቤት ተመለሱ።

በዚህ ጊዜ መምሬ ዘወልደ ማርያም (እርሱም የመምሬ እንዳዘናው ልጅ ነው) አንድ መላ አመጣ። "ይህ ልጅ ምናልባት እናቱ ዘንድ ሄዶ እንደሆነ ወደ መስቀለሶስ ሰው ብንልክና ብናስጠይቅ ይሻላል። ቢገኝ መልካም ሆነ። ባይገኝም እናቱስ ይህን ጉድ ነገር ብትሰማው ምን ይከፋል" ብሎ አማከረ። ቤተ ዘመድም በዚህ ሐሳብ ተስማማና ሁለት ሰዎች ወዲያው ሌሊቱን ወደ መስቀለሶስ ተላኩ። እዚያም ደርሰው ቢጠይቁ የእኔን መኖር ከእናቴ አፍ ሰምተው ተረዱ። "ገደል ገብቷል ተብሎ እዚያ ይለቀሳል። እንዲያው ለነገሩ ደኅና ገብቷል እንኳ አይባልም ወይ! ለምን አላስታወቅሽም፣ ኧረ አንቺ ምን ጉድ ነሽ" ብለው በእናቴ ላይ አፈጠጡባት። እርስዋም ኩብልሎ መምጣቱን ባላውቅ ነው ብላ በድንጋጤ ቃል መለሰችላቸው። ዓባይነህ በዚህ ጊዜ ተኝቶ እንቅልፉን ይለጥጥ ነበር። እነዚያም መልእክተኞች አፋፍ ላይ ቆመው "ዓባይነህ ደኅና ነው እናቱ ዘንድ ተገኝቷል" የሚል ቃል በአቀባይ ጥሪ አስተላለፉ። በዚህም ጊዜ ቤተ ዘመድ ደስ አለው። እምዬ በሰሙ ግን ድንጋጤው ገና አልለቀቃትም ነበር።

ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን እምዬ በሰሙ በአንድ አገልግል ሙዝና አነባበሮ አሽክማ እኔን ለማየት ወደ መስቀለሶስ መጣች። በዚያ ጊዜ እኔ በሜዳው ላይ ከእጉቴ ከወለተ ጻድቅና ከሌሎች ልጆች ጋር እጫወት ስለነበረ፣ መጀመሪያ አግኝታኝ እያለቀሰች ሳመችኝ። ከዚያም ወደ ቤት ገባንና እናቴን ክፉኛ ወቀሰቻት። ከወቀሳው በኋላ በአገልግል የመጣውን ድግስ መብላት ጀመርን።

ከዚህ በኋላ እምዬ በሰሙ ወደ ቤትዋ ለመመለስ ስትነሣ እኔም አብሬ ለመሄድ ተነሣሁ። እርስዋ ግን ጥቂት ቀን ከእናትህ ጋር ሰንብትና በኋላ ትመጣለህ አለችኝ። የኰበለልሁበት እናቴን በመናፈቅ ምክንያት መስሏት ስለነበረ ነው። እኔ ግን ከእናቴ ይልቅ የምናፍቀው እምዬ በሰሙን ነውና "እምቢ አልቀርም" እያልሁ አለቀስሁ። አክስቴንም ተከትዬ ወደ መግደላዊት ወረድሁ። ከዚህ ቀን ጀምሮ ትምህርት ቀረልኝና ሥራዬ ጨዋታ ብቻ ሆነ። ቤተ ዘመድም ይህ ልጅ እንዲማር ከተፈለገ ወደ ዲልዲላ፣ ወደ አባቱ መላክ ነው እንጂ፣ ዳግመኛ እዚህ ተማር እንዳይባል ብሎ አክስቴን መከራትና በዚሁ ተወሰነ።

## አስደንጋጭ ትርእይት እንደ ገጠመኝ

ከዚህ በኋላ ሥራዬ ጨዋታ ብቻ ሆኗልና እንደ እኔ ሥራ ፈቶች የሆኑትን የመንደር ልጆች እየፈለግሁ እንጫወት ጀመር። የምንጫወተው በመግደላዊት ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ከቅጽሩ ውጭ በሚገኘው በማርገጃው ላይ ነበር።

[16] አፋፍ ላይ ተቆሞ በጩኸት የሚተላለፍ መልእክት።



ይህን ሜዳ የመረጥንበት ምክንያት ሌላው ስፍራ በሚጥሽ ቁጥቋጦ የተሸፈነና ኩርንችታም ሲሆን፣ ይኸኛው ግን ለማርገጃው ሲባል ተመንጥሮ የተደለደለ ስለነበረ ነው። በዚያ ሜዳ ገና ጨዋታ ኳስ ወይም ሌላ ማናቸውንም ጨዋታ እንጫወትበታለን። ዳግመኛም እየተንጠላጠልን የምንጫወትባቸውና ፍሬ የምንለቅምባቸው ዋንዛዎች በዚያው በሜዳው ዳር ስለሚገኙ፣ ለመጫወት የሚመችን ስፍራ ይኸው ነበር። አንድ ቀን ያጋጠመኝን አስደንጋጭ ትርእይት በሚከተለው እገልጻለሁ።


አንድ ጊዜ፣ (እሑድ ቀን ይመስለኛል) ከቀትር በኋላ ወደዚሁ ስፍራ ለጨዋታ ሄድሁ። ጓደኞቼ ገና አልመጡም ነበርና እነርሱ እስኪመጡልኝ ድረስ ሥዕል ለማየት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄድሁ። በቤተ ክርስቲያኑ የውጭ ግንብ በተለይም በቅኔ ማኅሌቱ በኩል ልዩ ልዩ ኅብረ ቀለም ባለው ጭቃ እንደ ነብር እንደ አንበሳ የመሰለ ረጋ ሠራሽ[17] ሥዕል ተሥሎበት ነበርና እርሱን በማየት እየተደነቅሁ ጥቂት ቈየሁ። እየተዘዋወርሁም ስመለከት ከቤተ ክርስቲያኑ መስኮቶች አንዱን ክፍት ሆኖ አገኘሁትና አንገቴን አሾልኬ ወደ ውስጥ ብመለከት ግምጃ መጋረጃ የተጋረደለት የማርያምና የጊዮርጊስ ሥዕል በጨረፍታ ታየኝ።


እኔም ሥዕሉን በቅርብ ለማየት ጓጓሁና በመስኮት ሾልኬ ወደ ውስጥ ገባሁ። መጋረጃውንም ገላልጬ ሥዕሎቹን ተመለከትሁ። ከዚያም አለፍሁና ወደ ቅድስቱ ገብቼ በድርገት መውረጃው በር ላይ ያለውን ሥዕል እመለከት ጀመር። መጋረጃውን ስገልጥ በድንገት የመቅደሱ በር ተከፈተ። ቀጥሎም አንድ ቀይ ወጣት ከመቅደሱ ብቅ አለና "እዚህ ምን ታደርጋለህ አትሄድም ወይ" ብሎ በቊጣ ቃል ጮኸብኝ። ወጣቱ ልጅ ቀይ ግምጃ የለበሰና ለምድ የደረበ፣ ጠጉሩም ቀምቀም[18] የሆነ ነበር፤ በዚህ ጊዜ ክፉኛ ደነገጥሁና በዚያ በገባሁበት መስኮት ዘልዬ ወጥቼ ወደ ቤቴ ሮጥሁ። ሲቃ ይዞኝ እያቃሰትሁ ስደርስ ጊዜ እምዬ በሰሙ ምን ሆነሃል ብላ ጠየቀችኝ። ሲቃው እስኪቆምልኝ ድረስ ለጊዜው ዝም አለችኝ፣ በኋላም የደረሰብኝን ሁሉ ብነግራት መልአክ ያሆን ወይም ጋኔን ይሆን እያለች ትጨነቅ ጀመር። ጭንቀቷም ቅስፈት ሊያገኘው ነው በማለት ነበር። እንደ እውነቱ እኔም ድንጋጤው ከሆዴ አልወጣ ብሎኝ እስከ ሁለት ቀን ድረስ እንቀጠቀጥ ነበር። መምሬ ወሰን መሪ ድርሳነ ሚካኤል እየደገሙ ሲያጠምቁኝ ሰነበቱና ውሎ አድሮ ቀለለኝ።

ያሁን ትርእይት ሳስታውሰው ዛሬም ይገርመኛል። እምዬ በሰሙ እንዳለችው መንፈስ እንደሆነ ወይም ሰው እንደሆነ ለመለየት ሳልችል ብዙ ጊዜ ጥራአለሁ። በእምዬ በሰሙ በኩል ግን መንፈስ መሆኑ አመዝኗል።

[17] መሣኛ፣ ብዙ ጥበብ የማይታይበት ተራ ሥራ።

[18] ጎፈሬ ያልሆነ፣ ብቅ ብቅ ያለ ጸጉር።




1 የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ክፍሎችንና አቀማመጥን የሚያሳይ ሥዕል

# ምዕራፍ 2

## 1896 ዓመተ ምሕረት

**በመስቀለሶስ ከእናቴ ጋር ስለመቄየቴ፣ ወደ አዲስ አበባ ስለመሄዴ፣ እንጦጦ ከአባቴ ዘንድ ስለመድረሴ**

### መስቀለሶስ ከእናቴ ጋር ስለመቄየቴ

የትምህርቴ ነገር እንጦጦ ከአባቴ ዘንድ እንዲሆን በምክር በተወሰነው መሠረት እምዬ በሰሙ ወደ አባቴ መልእክት ላከች:: ያገኘችውም መልስ "መልካም ነው እናቱ ታምጣው" የሚል ሆነ:: ዕድሜዬ በዚህ ጊዜ አምስት ዓመት ተኩል ያህል ሆኗል:: እምዬ በሰሙ ይህ ልጅ አሁን በዚህ ዕድሜው ከእኛ ተለይቶ ወደማያውቀው አገር ሲሄድ ምናልባት እኛን በመናፈቅ ይከሳ ይሆናል የሚል ሥጋት አደረባትና ባይሆን እንኳን ስድስት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ቢቄይ ይሻላል ብላ እንደገና አሰበች፣ እስከዚያም ድረስ ከእናቱ ጋር ቢቀመጥ ወደፊት ናፍቆት ይቀነስለት ይሆናል ብላ ወደ መስቀለሶስ ይዛኝ ወጣች:: ከእናቴ ጋር ለብቻ ከተመካከሩ በኋላም "ዓባይነህ እዚሁ ከእናትህ ጋር ቄየኝ አይዞህ ነገ መጥቼ እወስድሃለሁ" እያለች አባበለችኝና ጉንጬን ስማ ተመለሰች:: ነገር ግን በማግሥቱ አልተመለሰችም:: እኔ አላወቅሁም እንጂ እናቴና አክስቴ በቄይታ የተማከሩት እዚያ የመቅረቴን ነገር ኖሯል:: ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ እኔ ከእናቴ ጋር እየወረድሁ ወይም አክስቴ እየመጣች መገናኘታችንና መተያየታችን አልቀረም ነበር::

ከዚህ በኋላ ከመንደሩ ልጆች ጋር በቶሎ ተለማመድሁና አዲሶች የጨዋታ ጓደኞች ለማግኘት ቻልሁ፤ የዚያ ጊዜ የቅርብ ጓደኛዬ ወጋየሁ የሚባል ልጅ ነበር:: አንድ ቀን በአንድ ሸርተቴ ስፍራ ልጆች ሁሉ ተሰብስበን እየተንሸራተትን ስንጫወት መቼም እኔ መተንኮስ እወዳለሁና በአንድ ነገር ስተነኩሰው ጊዜ ጠጠር አንሥቶ ቢወረውር ግንባሬን መታና ፈነከተኝ፣ ደም በሆነብኝ ጊዜ ደንግጦ እርሱ ራሱ ጭምር ደግፎ ወደ ቤቴ ወሰደኝና እንጀራ አባቴ ባሻ ዳምጠው በጨርቅና በቅቤ ተኩሰው ደሙ እንዲቆም አደረጉልኝ:: ሆኖም ጠባሳ መተዉ አልቀረም፤ እስከ ዛሬም ድረስ ጠባሳው በግራ ግምባሬ ላይ ይታያል:: በልጅነት ጠባይ የቂም ነገር አልተፈጠረምና ወዲያው በማግሥቱ ጓደኝነታችንን ቀጥለናል::

መስቀለሶስ በቄየሁበት ጊዜ እንጀራ አባቴ ባሻ ዳምጠውና ሌሎችም የመንደሩ ታላላቅ ሰዎች እንደ ብርቅ ስለሚያዩኝ በየቤታቸው ያንቀባርሩኝ ነበር:: አሁንም ትዝ የሚሉኝ አቶ ዳማና ባለቤታቸው ወይዘሮ ዝምታ፣ አቶ ሸገና ልጃቸው ሀብተ ማርያም፣ አቶ ወንድ አፍራሽና አቶ ልቤ ደርጋ ናቸው:: እንዲሁም ደግሞ የእናቴ የቅርብ ዘመድዋ እመዬት ጌቤ መንበሩና ባልዋ አቶ

ዲማ ከጂ፣ ልጆችዋ ካብታምዋ፣ ጠንፌለሽ፣ ተዋበችና ክብረት በየጊዜው የማይለዩን ቤተሰቦቻችን ነበሩ።

እናቴ ከሌላ የወለደቻቸው የእኔ ታላላቆች ሁለት እኅቶች አሉኝ። የመጀመሪያይቱ ታላቋ መሻገሪያ ሲሳይ የምትኖረው ከአባትዋ ጋር ጠንበላ እስጢፋኖስ ሲሆን ለጣቂዋ ታላቅ እኅቴ ወለተ ጻድቅ መስቀለሶስ ከእናታችን ጋር ነበረች። በዚያን ጊዜም የ12 ዓመት ዕድሜ ስለሆነች፣ እኔን በመጠበቅ ብዙ ድካምና አገልግሎት ነበረባት።



6 እመት መሻገሪያ ሲሳይ

ታላቅ እኅታችን መሻገሪያ ለባል የተዳረችው በዚሁ ዘመን ነበር፤ ምናልባት በኅዳር ወር ይመስለኛል። በዚሁም ጊዜ እኔና ወለተ ጻድቅ እናታችንን ተከትለን ለሠርጉ ወደ ጠንበላ ወርደን ነበርና ሁናቴው ሁሉ በአእምሮዬ ተቀርጾ ትዝ ይለኛል።

## ወደ አዲስ አበባ ስለመሄዴ

በመስቀለሶስ አራት ወር ያህል ከተቀመጥሁ በኋላ፣ እናቴ ወይዘሮ የሸዋ ወርቅ እኔን ወደ አዲስ አበባ ለመውሰድ ትደራጅ ጀመር። እኔም ቁላ ወርጄ እምዬ በስሙንና አክስቴ ዘነበችን ሌሎቹንም ዘመዶቹን ተሰናበትሁ። ጊዜው በጥር ወር 1896 ዓ.ም. ነው። ከዚህ በኋላ ጉዞ ተጀመረ። አብረውን የሚሄዱ አራት ሰዎች ነበሩ። ሁለቱ ለንግድ ጉዳይ ሙዝ በአህያ የጫኑ ሲሆኑ፣ ሁለቱ ደግሞ



ለወር ተራ[19] የሚወጡ ነፍጠኞች ናቸው። ነፍጠኞቹ እያንዳንዳቸው የኮርቻ በቅሎ ስላላቸው አብዛኛውን ጊዜ አፈናጠውኛል። በእግሬም የቻልሁትን ያህል ሄጃለሁ። እነዚህ አራቱ ሰዎች እናቴ የምታውቃቸውና አብሮ ለመጓዝ በቀጠሮ ስትጠብቃቸው የነበሩ የመስቀለሶስ ሰዎች ናቸው። ስማቸውን አሁን ረስቼዋለሁ።

ከጅሩ በተነሣሁበት ቀን ደነባን አልፈን ሪኤቻ ወንዝ ስንደርስ የአባቴን የአጎት ልጅ አባ ፍሬ ሰንበትን ከሁለት ልጆቻቸው ጋር አገኘናቸውና የጉዞ ጓደኞቻችን ሆኑ። ከዚያ በኋላማ ለድንጋይ ቅጥቀጣ ታዘው ወደ አዲስ አበባ ከሚመጡ የጅሩ ሰዎች ጋር በየመንገዱ ተገናኘንና ቍጥራችን ሲበዛ ቻለ።

«ድንጋይ ቅጥቀጣ» ብዬ አሁን ስለጠቀስሁት ቃል ትንሽ መግለጫ ልጨምር ነው። ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ከአዲስ አበባ እስከ አዲስ ዓለም ድረስ ያለውን መንገድ በድንጋይ ንጣፍ ለማሠራት ስለፈለጉ፣ መንገዱን መጀመሪያ በመሀንዲሶች አስቀየሱት፣ መሀንዲሶቹ በአድዋ ጦርነት ላይ የተማረኩት እነ ሙሴ ካስተኛ[20] ናቸው። እንዲሁ ደግሞ አጼ ምኒልክ ኢጣሊያኖችን ጠይቀው ከአሥመራ የተላከላቸው ቴኔንቴ ባንዲ ጭምር ነው ሲባል ሰምቻለሁ።

የመንገዱ ቅየሳ በ1894 ዓ.ም. ከአለቀ በኋላ አፈሩን ለመደልደልና ድንጋዩን ለማንጠፍ የሰው ጉልበት አስፈለጋቸው። ስለዚህም በ1895 ዓ.ም. መንገዱ በገመድ እየተለካ ሸዋ ለሚገኝ ሻለቃ ሁሉ እንዲታደል አደረጉ። ሻለቃውም ከዚያ በኋላ በግዛቱ ያለውን ገባሩንና ጭፍራውን በወር ተራ እየጠራ መሬቱን እንዲቆፍርና እንዲደለድል ድንጋይ እየፈለጠ እንዲሠራ አደረገው። ለዚህ ሥራ ከሸዋ የተሰበሰበው ባላገር ብዙ ነበረ። በዚህም ምክንያት የሸዋ ገባር ያንን ዘመን የ«ድንጋይ ቅጥቀጣ» ጊዜ ብሎ ጠራው። እንግዲህ ወደ ጉዞዬ ታሪክ እመለሳለሁ።

ቀን ስንጓዝ ውለን ማታ በአንድ ጥጋት ሰፍራ እንሰፍር ነበር። መቼም የሌሊቱ ብርድ አይጣል ነው። በዚህ አኳኋን ተጉዘን በአራተኛው ቀን አዲስ አበባ ገባን። ሰፈራችን በቀኛዝማች መኰንን ተወንድ በላይ ቤት አጠገብ የጅሩዎች ሰፈር በሚባለው ቦታ ሆነ። በዚህ ሰፈር ዓሥር ቀን ያህል ቈይተንበታል።

---

[19] በየወሩ በመተካከት ሥራ የሚሠራበት ወይም ጥበቃ የሚደረግበት ወረፋ።

[20] ካስተኛ (ሙሴ ቀስተኛ) የሲሲሊ ተወላጅ ኢጣልያዊ ነው። ለ39 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያ ኖሯል። ባህሉን በሚገባ ለምዶ አማርኛ አቀላጥፎ ይናገር ነበር። በሥራ ሚኒስቴር ውስጥ በመሀንዲስነት ይሠራ ነበር። ከኢጣልያ ወረራ በፊት የጠላት ዜጎች ከሀገር ሲወጡ እሱም ወጥቶ ነበር። ከኢጣልያኖች ጋር ተመልሶ መጥቶ አርበኞች ለኢጣልያ እንዲገቡ ያግባባ ነበር። መስከረም 19 ቀን 1931 ዓ.ም. አርበኛው ግራዝማች ገረሱ ዱኪ (በኋላ ደጃዝማች) በስቅላት ቀጥተውታል።

## በጊዜው ካየሁት የማስታውሰው

በዚያ ጊዜ አዲስ አበባ ከተማ ካየሁት ነገር የሚከተለው ትዝ ይለኛል፡፡

አንደኛ፣ በእሳትና በውሐ እንፋሎት እየተነዳ የሚሄደው የሰርኪስ ባቡር ወደ አዲስ አበባ የመጣው በዚያን ዘመን ነበርና እየተንቸሰቸሰ ወደ አራዳ ሲሄድ አየሁ፡፡ ደግሞም አንድ ቀን ጃንሆይ አጼ ምኒልክ በአቶ ደቦጭ ቦታ አጠገብ ድንኳን ተተክሎላቸውና በተደላደለ ከፍተኛ ስፍራ ላይ በወንበር ተቀምጠው ባቡሩን ሲመለከቱ ማየቴን አስታውሳለሁ፡፡




7 አጼ ምኒልክ ሰርኪስ ባቡርን ሲመለከቱ

ሁለተኛ፣ ወደ አራዳ ጊዮርጊስ የሚወስደው መንገድ በሚያልፍበት በወንዙ ላይ በኖራ ግንብ[21] የሚሠራውን ድልድይ ሕዝቡ ሁሉ እንደ ብርቅ ይመለከተው ነበርና ለኔም እናቴ አሳይታኛለች፡፡ ይኸውም ድልድይ አሁን የራስ መኮንን ድልድይ የሚባለው ነው፡፡ እንዲሁም ከጃንሆይ ግቢ[22] እስከ አራዳ ገበያ ድረስ መንገዱ ተቆፍሮና ተደልድሎ በድንጋይ ንጣፍ የተሠራው ሥራ (አሁን የባቡር መንገድ የሚባለው) አዲስ ነገር በመሆኑ፣ ሕዝብ ዕፁብ ዕፁብ እያለ ያደንቅ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል፡፡

[21] ኖራ ከኖራ ድንጋይ (limestone) ወይንም ከኖራ አፈር በእሳት ኃይል ይመረታል፡፡ ኖራው ከተቦካ በኋላ ከአሸዋ ጋር ተለውሶ ግንብ ይገነባል፡፡ በኋላ ዘመን ኖራ ከሲሚንቶና ከአሸዋ ጋር ይደባለቅም ነበር፡፡ በአሁኑ ዘመን ኖራን መጠቀም ቀርቶ ሲሚንቶ ከአሸዋ ጋር ብቻ እየተለወሰ ይገነባል፡፡

[22] የጃንሆይ ግቢ ወይንም አንዳንዶ በነጠላው ግቢ ተብሎ የሚጠራው አራት ኪሎ የሚገኘው የምኒልክ ቤተ መንግሥት ነው፡፡





8 ራስ መኮንን ድልድይ

ሦስተኛ፣ ፈረንጆች በእግራቸው ወይም በፈረስ እየሆኑ በመንገድ ሲሄዱ ትንንሾቹ የመንደር ልጆች ተሰብስበው እንደ ጉድ ያዩዋቸው ነበር፤ ወዲያውም «ፈረንጅ ፈረንጅ» እያሉ እየጮሁ ይከተሏቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ድንጋይ እየወረወሩባቸው ይሸሹ ነበር፡፡ እኔም አንድ ጊዜ በዚህ የብልግና ሥራ ተካፋይ ሆኜበታለሁ፡፡

አራተኛ፣ ሌሊት ከተማውን የሚጠብቁት ዘበኞች ከሐረርጌ የመጡ ሱማሌዎች ነበሩ፡ ሕዝቡ «ደወሪያ» ይላቸዋል፡፡ ማታ ሦስት ሰዓት ሲሆን ለሕዝብ የሚያሰሙት አንድ የጩኸት ድምፅ አላቸው፡፡ ሕዝቡም ያን ድምፅ ሲሰማ በየቤቱና በየግቢው መከተት አለበት፡፡ ሱማሌ ከጮኸ በኋላ ከአጥሩ ውጭ በመንገድም ሆነ በሜዳ ላይ የተገኘውን ሰው እየያዙ ይወስዱና አስረው ያሳድሩታል፡፡ በማግሥቱም መቀጫ አስከፍለው ይለቁታል፡፡ መቀጫውም አንድ ሩብ[23] እንደ ነበረ አስታውሳለሁ፡፡ በዚያ ጊዜ የእነዚህ ዘበኞች ሥልጣን የቱን ያህል እንደሚፈራና እንደሚከበር በጣም ትዝ ይለኛል፡፡

አምስተኛ፣ የጉቦ ጓደኞቻችን እህዮቻቸውንና በቅሎዎቻቸውን ሣር ለማጋጥ ወደ ቀበና ወንዝ ሲሄዱ አንድ ቀን እኔም ተከትዬ ሄጄ ነበር፡፡ በዚያ ቀን ጃንሜዳን ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴን አስታውሳለሁ፡፡ ዙሪያውን በማዕዘን እንጨት ታጥሮና አልፎ አልፎ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ተተክሎበት በጥንት

[23] አጼ ምኒልክ በ1901 ዓ.ም. ከብር አሠርተው ያወጡት ገንዘብ፡፡ አንድ ብር በ2 አላድ፣ በ4 ሩብ፣ በ8 ተሙን፣ በ16 መሐለቅ ይመነዘር ነበር፡፡

ሁናቴው አይቼዋለሁ:: በዚያ ሰሞን የፈረስ እሽቅድድም የሚደረግ ሆኖ የተደራጀ ዝግጅት ነው:: ነገር ግን ፈረሶች ሲሽቀዳደሙ አላየሁም:: ከዚያም አልፎ በቀበና ወንዝ (አሁን የፈረንሳይ ሌጋሲዮን በሆነው ውስጥ) አህዮች ስጠብቅ ውዬ በጣም ርቦኝና ደክሞኝ ተመለስሁ::

## እንጦጦ ከአባቴ ዘንድ ስለመድረሴ

ከዚህ በኋላ እናቴ ይዛኝ ከአዲስ አበባ ወደ እንጦጦ ወጣችና ለአባቴ አስረከበችኝ:: አባቴም በናፍቆት ስመው ተቀበሉኝ:: እናቴ አንድ ቀን አድራ በማግሥቱ ወደ ቤትዋ ወደ ጅሩ ተመለሰች:: በዚህ ጊዜ እኔ ክፉኛ አለቅስ ነበር:: በቤት ያለችው የአባቴ ሚስት (እንጀራ እናቴ) ከአዲስ አበባ የመጣች ልጅ እግር ቢጤ ናት:: ለጊዜው ሁለት ሦስት ቀን ያህል እያባበለች አረጋጋችኝ:: በኋላ ግን ሰለቸችና ልቅሶ ባለቀስሁ ጊዜ "ውይ እቴ ምን አመለኛ ነው" እያለች ታገጣብረኝ ጀመር:: ነገሩ ሁሉ ተለዋወጠብኝና እስከ ወር ድረስ ፍዝዝ እንዳልሁ ቈየሁ::

ከዚህ በኋላ አባቴ ፊደል አስጀመሩኝ:: እንደኔ ጀማሪዎች የሆኑ ብዙ ልጆች ስለነበሩ፣ ከእነርሱ ጋር ተራ በተራ ፊደል መቍጠር ጀመርሁ:: ከትምህርት በኋላ ወደ ቤት ስገባም የባላገር ልማዱን እንድተው በማለት ልዩ ልዩ ሥርዓት ያስለምዱኝ ጀመር፤ ይኸውም ገበታ ሲቀርብ ሙቅ ውሐ ይዞ መቅረብና እጅ ማስታጠብ፤ እነርሱ በልተው ገበታው እስኪተነሣ ድረስ ፊትን ወደ ግድግዳ አዙሮ መቆም፤ ጉርሻ በተሰጠ ጊዜ መሬት ስሞ መቀበል፤ ከሙብል በኋላ እጅ ማስታጠብና ገበታ ማንሣት፤ በገበታው ላይ የተተወልኝን ሙብል በጸጥታ ሆኖ መብላት፤ እንጀራው ሲበላ ድምፅ ሳያሰሙና ሳያጮሁ ማላመጥ፤ ይህንና ይህን የመሳሰለውን ነው:: በመጀመሪያው ጊዜ ግራ ገብቶኝ ሲደናገረኝ ሰነበተ:: በኋላም ሁለት ሦስት ቃል ይናገሩኝና ሲሳሳተኝ በኵርኵም እየገጩ ያስጠነቅቁኝ ጀመር:: ያለቀስሁ እንደሆነም "በል እንባህን መልሰህ ጠጣት" እያሉ በቊንጢጥ ይመዠርጉኛል:: ከሁሉም የሚብሰው ቅጣት ከቶ ፊት አይሰጡኝም ነበር:: ስለዚህ ቅጣትን ፈርቼ እሽቆጠቆጥ ጀመር:: መንቀባረር ገና ድሮ ከአክስቴና ከእናቴ ዘንድ ቀርታለች::

ፊደሉን በተወራጅ አስተማሪ ከጓደኞቼ ጋር እንድማር ታዘዝሁ:: ጓደኞቼ ያወቁትን እኔ የተሳሳትሁ እንደሆነ መልሱ የሚነገረኝ በቊንጢጥ ብቻ ነበር:: ስለዚህ እየተጠነቀቅሁ መማርና ማወቅ ግድ ሆነብኝ:: በእቡጊዳ ጊዜ የነበረኝን ጣጣ ከቶ አልረሳውም:: የሆነ ሆኖ ፊደል በብዙ ድካም ታለፈችና ወደ ፊደለ ሐዋርያ ተዛወርሁ:: አሁን ትምህርቱ የፊደሉን ያህል አልጨለመብኝም፤ ከጓደኞቼ እንዳላንስ በማለት መጽሐፉን እያስተዋልሁ እማር ጀመር:: ከአንድ ወር በኋላም እንደ ጓደኞቼ ወደ ገበተ ሐዋርያ ስለተላለፍሁ ደስታ ተሰማኝ:: ምክንያቱም ወደ ገበተ ሐዋርያ ያለፉት ልጆች ፊደል ጀማሪዎችን



በተወራጅነት እንዲያስተምሩ ይታዘዙ ነበርና ከእነርሱ ማዕርግ በመድረሴ ነበር:: የተማርሁበት ገበተ ሐወርያ[24] ከእንጦጦ ማርያም ዕቃ ቤት የመጣ ገድለ አባ ሊባኖስ ይባላል::



፱ እንጦጦ ማርያም በ1897 ዓ.ም. ገደማ

ንባቡ አስቸጋሪና ከባድ ስለሆነ፣ ጥቂት ወራት አሳልፎብኛል:: ቢሆንም እርሱን እጥርቼ በመማሬ ምክንያት ለመጪው ትምህርት መንገድ ጠራጊ ሆኖኛል:: ከእርሱ የሚለጥቀውም ትምህርት ዳዊት[25] ነበረ:: እርሱንም ለትምህርቴ ሁለተኛ እርምጃ አድርጌ እመለከተዋለሁ:: እንግዲህ ወደዚያ ከማለፌ በፊት ስለ ወላጆቼ ዜና በሚከተለው ምዕራፍ ትንሽ ቃል እጽፋለሁ::

---

[24] ወይንም ገበተ-ዋርያ:: ከፊደል ቀጥሎ ንባብ የሚጠናበት ትምህርት::

[25] ዳዊት የተባለው መጽሐፍ ነቢዩ ወይም ንጉሡ ዳዊት የደረሰውና ያስደረሰው፤ በኋላም እየመላለሰ ይዘምረው የነበር ነው:: የዳዊት መድገም ከጥንት ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ ከፍተኛ ትምህርት ተቈጥሮ፤ በጣም የከበረ ሥርዓት ነበረው:: ስለዚህም ዳዊት የትምህርቱ መጨረሻ እንደሆነ ይገመት ስለነበር ልጆች ሁሉ ከዚህ ለመድረስ ይኸንንም ደረጃ ለማለፍ የሚያደርጉት ጥረት በጣም ከፍ ያለ ነበር:: ምንጭ - ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት::

# ምዕራፍ 3

## ስለ ወላጆቼ ዜና ባጭሩ

**ስለ አባቴ ዜና፣ ስለ አስተዳደጋቸውና ስለ ትምህርታቸው፣ ደብረ ሲባናስ ስለመውረዳቸው፣ ወደ እንጦጦ ማርያም ስለመምጣታቸው፣ እንጦጦ ማርያምን ስለመልቀቃቸው፣ ቀበና አቦን ስለመሾማቸው፣ ቀበና አቦን ትተው ወደ ሀገራቸው ስለመመለሳቸው፣ ስለ እናቴ ዜና**

### ስለ አባቴ ዜና

የአባቴ የትውልድ አገር በአባታቸው በኩል እንጀራ ማርያምና ዳኖት አቦ ሲሆን፣ በእናታቸው በኩል ደግሞ ሳምዋሻ አቦ ነው።

የእንጀራ ማርያም ትውልድ ከላይ ግንዱ ዕደ ይባላል እርሱም የደጃዝማች ዕደ ክርስቶስ ከፊለ ቃል ነው። ከሰገሌ ዘመቻ[26] በፊት እኔ ራሴ ወደዚሁ ስፍራ ወርጄ ነበርና ከግንድ አለቃችን ከየሻላ[27] ዘመድኩንና ክርስት ባላንጣችን ከየሻላ ማታሪ ጋራ ተገናኘቼ የርስት ግብርና የጦም ቆሎ[28] ባገሩ ልማድ መሠረት ለግንድ አለቃ ግብር ገብሬ ነበርና አገሩን ዐውቀዋለሁ። በዚያ ጊዜ ብሪት አፈር የሚባለውን ድርሻ ርስቴን አሳዩኝና ከእርሻው ላይ የተገኘውን የመጋገር[29] ድርሻ አንድ ቁርበት ሙሉ ጥጥ አስጭኜ ተመልሻለሁ። መሬቱን የሚጠብቀውና ለተጋገር እያጋዛ የሚሳርሰው የርስት አካፋያችን አጎቴ የሻላ አዳፍር ይባላል። ይህ ሰው አባቴን አጥብቆ የሚወድና የሚያስብልን ነው። ከዚያ ወዲህ ግን ወደ እንጀራ ሄጄ ስለማላውቅ አሁን ርስቱ በምን ሁናቴ እንደሚገኝ አላውቅም።

የዳኖት አቦ የትውልድ ስም ዝዋ ይባላል። ዝዋ መምሬ አልታመንንና የፍሬ ሰንበትን አባት ይወልዳል። መምሬ አልታመን ከሳምዋሻ እስታሉን አግብቶ፣ በሰሙን፣ ወለተ ወልድን፣ ወለተ ሚካኤልን፣ ወልደ ቂርቆስን ይወልዳል(ገጽ

[26] ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም. በንጉሥ ሚካኤል የተመራው የወሎ ጦርና በልዑል ራስ ተፈሪ የተመራው የሸዋ ጦር ሰገሌ ላይ የተዋጉበት። ዝርዝር ታሪኩን መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ*፣ ገጽ 172 ይመልከቱ።

[27] የቀድሞ ማዕርግ ስም፣ የሻለቃ ክፊል፤ ባለ ግምጃ ሱሪ። ምንጭ - ደስታ ተክለ ወልድ፣ *መዝገበ ቃላት*።

[28] በጾም ጊዜ ምዕመናን ለካህናት የሚሰጡት ቆሎ።

[29] አራሹ ለባለርስት የሚያካፍለው ድርሻ።



23 ይመልከቱ)። የፍሬ ሰንበት ዘሮች ብዙ ናቸው። እነርሱም የሚገኙት እዚያው ዳኖት ነው።

የሳምዋሻው የትውልድ ስም ደብርቼ[30] ይባላል። የትውልዱም ሐረግ ከደብርቼዬቱ ከወይዘሮ መስቀሉና ከአቶ ገርጊስ ተነሥቶ እስከ ቄስ ደፈር ይደርሳል። ቄስ ደፈር ከመራቤቴ ዘይታ ከሚባለው ቀበሌ ሳሑን አግብቶ አምስት ሴቶችና አንድ ወንድ ልጅ ወለደ። የሴቶቹ ስም ተረፍሽ፣ ጠቋሪት፣ ሁኚ እንዳሻሽ፣ እስታሉ፣ ወለቴ ሲሆን የወንዱ ስም ገብረ ክርስቶስ የተባለው ነው።

አለቃ ገብረ ክርስቶስ የብሉይና የሐዲስ ሊቅና የቅኔ መምህር ከመሆናቸው የተነሣ በንጉሥ ኃይለ መለኮትና በአጼ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እጅግ የተከበሩ ሰው ነበሩ። በአጼ ዮሐንስም ዘንድ የታወቁና የተከበሩ ነበሩ። አጼ ዮሐንስ በ1873 ዓ.ም. አራት ጳጳሳት ለማስመጣት ወደ ግብጽ አራት መልእክተኞችን በላኩ ጊዜ ከሸዋ በኩል የተላኩት መልእክተኛ አለቃ ገብረ ክርስቶስ ናቸው። ወደ ግብጽ ሄደው የተላኩበትን መልእክት ፈጽመው ተመልሰዋል። የሹመት በታቸው አፈር ባይኔ ተክለ ሃይማኖትና እንኮበር ሚካኤል ነው። ስለ አለቃ ገብረ ክርስቶስ የታላቅነት ታሪክ የአንኮበር ካህናት በሰፊው ይተርካሉ[31]። አለቃ ገብረ ክርስቶስ በ1883 ዓ.ም. ዳግማዊ ምኒልክ ጠርተዋቸው አዲስ አበባ መጥተው ሳሉ ጥር 8 ቀን በድንገት ሞተው በመካነ

[30] ደብርቼ ከጋይንት ወደ ሸዋ በ1500 ዓ.ም. ገደማ በአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት እንደመጣ ይገመታል። ምንጭ - የታሪኩ ጸሐፊ ለአዘጋጁ ከነገሩት።

[31] ከ "ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ፤ መጽሐፈ ትዝታ" የተወሰደ። ገጽ 114 - 116

. . . አለቃ ገብረ ክርስቶስ የተባሉ ሊቅ - ያንኮበር ሚካኤል አለቃ ናቸው - የመጣፍ ባለቤት የቅኔ ባለቤት፤ የናለቃ ወልደ ያሬድ መምር፤ የነ መምር አካለ ወልድ መምር (ሰዋስው ያስተማሯቸው ናቸው) የናለቃ ወልደ ሐና (ትንሹ፤) ያለቃ ጉሹ፤ ያለቃ ወልዳማኔል፤ ያለቃ ወልደ መስቀል፤ የኒህ ሁሉ መምር ነበሩ። ባለሚያ ናቸው ባያሌው፤ በልጅነት ቅኔ አስተማሪነታቸው ሽኔ አገር ነው። የነዚህ ሁሉ መምር የብሉይ የቅኔ መምር - ባለሚያ ናቸው። . . .

. . . ዋድላ ሳሉ - እኒያ ላሊበሎች ሦስት ልደቶች ናቸው፤

'ኢጸድቀሂ ላሊበላ ወኢያድኃና ለነፍሱ
አዕዱግ ካህናቲሁ እስመ ደብረ ያፈልሱ'

ስሉ አለቃ ገብረ ክርስቶስ መወድስ። (ላሊበላ አልጸደቀም፤ ነፍሱንም አላዳናት። አህዮች ካህናቶቹ ደብርን ቤተክሲያን - ያጠፋሉና). . .

. . . እዚያ ዋድላ ሆነው ሲያላግጡ እንዲህ አሉ ይባላል።. . .

. . . ኻዲያ ቅኔ መምር ሆኑ። ዋድላ ማስተማራቸውን አውቃለሁ። ሕደው ጉጃም ብሉዩን አጠኑ፤ ብሉይ መምር ሆኑ። ከዚያ በኋላ ወደ ሸዋ መጡ፤ በሣህለ ሥላሴ።

በሸዋ ሦስት ልደቶች ሠልጥነዋልና፤ ሁለት ልደት የተባለ ሁሉ ሕዶ ትግሬ በስደት አለቀ፤ ተምቤን ከሚባል አገር በየገዳሙ በየገዳሙ ሕዶ አለቀ ሞተ። አለቃ ገብረ ክርስቶስም በዚህ በሃይማኖት ምክንያት ተሰደው ሕደው ትግሬ ይኖሩ ነበረ። አድዋ ነበር ኑሮአቸው፤ ያስተምራሉ። ኋላ፤ አጤ ዮሐንስን እግዚአብሔር አስነሣ ባጤ ዮሐንስ ጊዜ ነው መመለሳቸው አገራቸው።

ሸዋ መጥተው አንኮበር ጉባኤ ዘረጉ። አንኮበርማ አሳቸው ናቸው መምሩ። ኧረገኝ! ጳጳስም እንደሳቸው አይከበርም። . . .

ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል[32]። እንግዲህ የትውልዱን ዝርዝር እቀጥላለሁ።

እስታሉ ከእንጀራ ማርያም አልታመንን አግብታ በሰሙን፣ ወለተ ወልድን፣ ወለተ ሚካኤልን፣ ወልደ ቂርቆስን ወለደች። ወልደ ቂርቆስ መርስዔ ኀዘንን፣ ፈትለ ወርቅን፣ አምሳለ ወርቅን ወለዱ። አምሳለ ወርቅ መካን ስትሆን የቀሩት ሁለቱ ብዙ ልጆች ወልደዋል። የልጅ ልጅም አይተዋል።

ተረፍሽ ዓለም ሲያልቅን ወለደች፣ ዓለም ሲያልቅ አጫወቱኝን ወለደች። አጫወቱኝ ወልደ መስቀልን አግብታ መምሬ ራስ ወርቅን ወለደች፣ መምሬ ራስ ወርቅ[33] ብዙ ልጆች ወልደዋል። የልጅ ልጅም አይተዋል።

ጠቋሪት ቢያዝልቀውን ወለደች፣ ቢያዝልቀው አባ የምሩን ወለደ። አባ የምሩ ድንግላይ መነኩሴ ናቸው።

ሁኚ እንዳሻሽ ሳልልን ወለደች፣ ሳልል ወለተ ማርያምን፣ ወለተየስን፣ ወለተ ገብርኤልን ወለደ። ወለተ ማርያም መምሬ እንደሻውንና በለድን ወለደች። በለድ ኃይለ ማርያምን ወለደ። እርሱም አሁን የላምዋሻ ርስታችንን ይዞ እዚያው ላምዋሻ ላይ ይገኛል። መምሬ እንደሻውም ነጋሽን ወለደ። ወለተ

---

[32] አጼ ምኒልክ የሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ከመትከላቸው ከጥቂት ሳምንታት በፊት የአንኮበር ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበሩትና በሊቅነታቸው የተመሰገኑትን አለቃ ገብረ ክርስቶስን ወደ አዲስ አበባ አስጠሯቸው። ጃንሆይ የጠሩዋቸው የአዲሱን ቤተ ክርስቲያን አለቅነት ሊሰጡዋቸው ስለሆነ በታኅሣሥ 24 ቀን 1883 ዓ.ም. በመቃኞ ቤተ ክርስቲያን ሲተከል አለቃ ገብረ ክርስቶስ ዋና አስተባባሪና አሳዳሪ ሆነው በዓሉን አስከበሩ። ቀጥሎም ሹመቱ ተሰጥቷቸው ሳለ ገና ሥራው ሳይቋቋም ወዲያው በ14ኛው ዕለት ጥር 8 ቀን 1883 ዓ.ም. በዕለተ ኀሙስ በድንገት ሞተው መጀመሪያ ተቀበሩበት። ለሹመት የተዘጋጁት ሊቅ ለመቃብር ማሟሻ በመሆናቸው በዚያ ሰዓት ዕፁብ ድንቅ ተብሎ ነበር። ምንጭ - ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ*፡

[33] *መምህር ራስ ወርቅ መስከረም 14 ቀን 1879 ዓ.ም. ተወለዱ።* ፀዋትወ ዜማን ከዘመዳቸው ከመሪጌታ ወልደ ቂርቆስ ደብረ ሊባኖስ ተማሩ። እዛው ደብረ ሊባኖስ ከመምህር ገብረ ኢየሱስ ዘንድ ቅኔ ተምረው፣ ተቀኝተው እንደጨረሱ ወረኢሉ አለቃ ጸጋ ዘንድ ሄደው አቋቋም ተምረው የዜማና የአቋቋም መምህር ተብለው ተመረቁ። መምህር ራስ ወርቅ በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከዓቃቤ ሰዓት እስከ ርዕሰ ደብርነት ሹመት ተሰጥቷቸው 30 ዓመታት አገልግለዋል። ዘመዳቸው አለቃ ገብረ ክርስቶስ ያስተዳድሩት የነበረውን የአፈር ባይኔ ተክለ ሃይማኖት ገዳም በ1925 ዓ.ም. ተሾመው ለ19 ዓመታት ያህል አስተዳድረዋል። በጠላት ወረራ ዘመን አፈር ባይኔ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ጸሎተ ምህላ በማድረስ፣ ከልጃቸው ከጥሩነህ ጋር አርበኞችን በማበረታታትና ስንቅ በማቀበል፣ በዓቅማቸውም ገንዘብና መሣሪያ እየረዱ አሳልፈዋል። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናቱ መጻሕፍትና ቅርሳ ቅርስ እንዲጠበቁ አድርገዋል። ሌላው ልጃቸው፣ ሻለቃ ዮሐንስ ራስ ወርቅ፣ የሆለታ ጦር ትምህርት ቤት ምሩቅ፣ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. በኢጣልያኖች ተይዞ በግፍ ተገድሏል። ከጠላት ወረራ በኋላ የፊደገ ሕይወት ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትን በመመሥረት አገልግለዋል። ቀጥሎም ጠራ ወረዳ የደብረ በግዕ ሕፃን ሞአ ገዳምና የአንኮበር ተክለ ሃይማኖት አለቅነት፣ የመንፈሳዊ ጉባኤ ምክር ቤት አማካሪነትና የመንፈሳዊ ጉዳይም ዳኝነት ተሹመዋል። ጥቅምት 7 ቀን 1954 ዓ.ም. ዐርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው እንጦጦ መንበረ ፀሐይ ተፈጽሟል። ምንጭ - መልአከ ፀሐይ ገብረ ሥላሴ ገብረ ጊዮርጊስና አቶ ተረፈ ራስ ወርቅ።



ገብርኤል የሐናዬ እናት ናት። የቄስ ደፈር ዘር እጅግ ብዙ ስለሆነ በሙሉ አልተዘረዘረም፣ ባጭሩ ተጽፏል።

ቄስ ደፈር ከሞረት ጥዱ የሚዛመድበት የትውልድ ዘርፍ ባጭሩ ይህ ነው። የመራቤቴው መዘምር ተክለ ሃይማኖትን ወለደ። ተክለ ሃይማኖትም ኢሳኢያስን ወለደ። ኢሳኢያስ እልፍዮስንና አቢሳን ወለደ። አቢሳም ከጠሉሽ እኅት ከግብዋት ገብሬ ሰባት ልጆች ወለደ። እነርሱም ጥዱ፣ ያበገረድ፣ ጎዲር ዮሐንስ፣ እልፍዮስ፣ እምዬ፣ ገነቴ፣ ሰቆቃው ይባላሉ። እንግዲህ ጠሉሽ የቄስ ደፈር አያት ናት። ጥዱም የሞረት ባላባት በመሆን የታወቀ ገናና ሰው ነው። እልፍዮስም ለቄስ ደፈር በእናታቸው በኩል አያታቸው ነው። የነግራዝማች ድልነሣሁ ዘር በዚያ በኩል ይቈጠራል። ያበገረድም የወይዘሮ በዛብሽ እናት ናት። ወይዘሮ በዛብሽም የንጉሥ ኃይለ መለኮት እናት ናቸው።

## ስለ አስተዳደጋቸውና ስለ ትምህርታቸው

ከዚህ ቀጥሎ የምጽፈው ስለ አባቴ አስተዳደግና ስለ ትምህርታቸው ጥቂት መግለጫ ለመስጠት ነው። አለቃ ወልደ ቂርቆስ በ1848 ዓ.ም. ከመምሬ አልታመንና ከወይዘሮ እስታሉ ላምዋሻ አቦ ላይ ተወለዱ። በዚያው ስፍራ ንባብና ተጕለቴ ዜማ እየተማሩ አደጉ። ዕድሜያቸው ሐያ ዓመት ያህል ሲሆን አጎታቸውን አለቃ ገብረ ክርስቶስን ለመጐብኘት ወደ አንኮበር ሄዱ። አንድ ቀን በአንኮበር ሚካኤል ማኅሌት ተቁሞ[34] ሳለ ከጐንደር የመጣ አንድ ደቀ መዝሙር ዜማውን ሲያንቆረቁረውና ካህናቱ ሁሉ "ዕፁብ" እያሉ ሲያደንቁት ተመለከቱ። የዜማው ስልት እርሳቸው ከተማሩት ከተጕለቴው ይልቅ በጣም ያማረና የተጣራ መሆኑን በቶሎ ተገነዘቡት። ወዲያው "የየት አገር ዜማ ነው?" ብለው ቢጠይቁ "የቤተልሔም ዜማ ነው" ብለው መለሱላቸው። በዚህ ጊዜ ይህን ዜማ ከቤተልሔም ተምሬ መጥቼ ለወንድሞቼ ለሸዋ ልጆች አተርፍላቸዋለሁ ብለው ቈርጥ ሐሳብ አደረጉ። ይህንንም ለአጎታቸው ለአለቃ ገብረ ክርስቶስ ቢያማክሩዋቸው "መልካም ነገር አሰበሃል እኔም ለቀለብህ የሚሆን እህል እጨጌ ቴዎፍሎስ[35] ከዚያው ከቤተልሔም ከዘኰዳዳቸው እንዲያዝዙልህ አደርጋለሁ" ብለው አበረታቱዋቸው።

---

[34] ከበሮ እየተመታ በመቋሚያና በጸናጽል ታጅቦ በኅብረት ዜማ ሲዜም ማኅሌት ተቆመ ይባላል።

[35] እጨጌ ቴዎፍሎስ ሃምሳ ሁለተኛው የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ነበሩ። ሀገራቸው ጐጃም የተማሩት ሞጣ ላይ ብሉይ፣ ሐዲስና ሊቃውንት ነበር። በምግባራቸውም ቀናነትና በሰውተኛነታቸው ጥልቀት በአጼ ዮሐንስ ዘመን እጨጌነት ተሾሙ። አጼ ዮሐንስ የኢትዮጵያን ታሪክ መርምረው ነበረና እንደ ጥንቱ ነገሥታት ልማድ ሊቀ ካህናትነቱን ለእጨጌው መለሱ። እጨጌ ቴዎፍሎስ የተከበሩና የተፈሩ ስለነበሩ አጼ ዮሐንስ ሳይቀሩ እጨጌ ዘንድ ሲገቡ አጎንብሰው እንደነበረ ይነገራል። አጼ ዮሐንስ መተማ ደርቡሽን ለመውጋት ሲዘምቱ አብረው ዘምተዋል። ምንጭ - ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ *የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት*፣ የብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የሰበሰቡት፣ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ዘንድ የሚገኝ የአለቃ ተክለ ኢየሱስ በእጅ የተጻፈ የታሪክ መጽሐፍ።

ቤተልሔም የሚባለው ቀበሌ በመቄት[36] ውስጥ የሚገኝ የእጨጌዎች የሹመት አገር ነው። አለቃ ገብረ ክርስቶስ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ትግሬ ላይ የቅኔና የመጽሐፍ አስተማሪ ሆነው ተቀምጠው ነበረና በዚያ ጊዜ ከእጨጌ ቴዎፍሎስ ጋር ጓደኞች ነበሩ። እንደዚህ ያለ ተስፋ ለአባቴ መስጠታቸውም የጓደኝነት ፍቅራቸውን በመተማመን ነበር። አለቃ ገብረ ክርስቶስ ወዲያው ደብዳቤ ጽፈው ለእጨጌ ቴዎፍሎስ ላኩባቸው። እጨጌውም ትምህርቱን ጨርሶ እስከተመለሰ ድረስ በየወሩ አንዳንድ ዳውላ እህል ዳርጌዋለሁ የሚል መልስ ላኩላቸውና አባቴ ያን ወረቀት ይዘው ወደ ቤተልሔም ተጓዙ።

ወልደ ቂርቆስ ቤተልሔም ሲደርሱ ያን ወረቀት ለአስተማሪው ለሊቀ ካህናት ደረሰ አሳዩ። እርሳቸውም ተቀበሏቸውና የዜማውን ትምህርት አስጀመሯቸው። ሊቀ ካህናት ደረሰ ስመ ጥምቀታቸው ገብረ እግዚአብሔር ነው። የአባቴ የትምህርት ጓደኞችም እነ ሊቀ ካህናት መርሻ፣ እነ አለቃ ዘውዴ፣ እነ አለቃ ሣህሉ ነበሩ። ወልደ ቂርቆስ ትምህርቱ እየቀናቸው በመሄዱ በአስተማሪያቸውና በጓደኞቻቸው እንደበት ይመሰገኑ ጀመር። በስማቸውም ላይ ሕዝቡ በፈቃዱ የቅጽል ቃል ጨምሮበት "ሸዌ ወልደ ቂርቆስ" ይሏቸው ጀመር። እንጦጦ በነበርንበት ጊዜ እንኳ እርሳቸውን ለመጎብኘት የሚመጣ የበጌምድር ሰው በጥያቄም ሆነ በጨዋታ ላይ "ሸዌ ወልደ ቂርቆስ" እያለ ይናገር ነበር።

ወልደ ቂርቆስ ዜማን በቤተልሔም ሰባት ዓመት ከተማሩ በኋላ ባለመዝገበ ድጓ ምስክር[37] ሆነው ተመረቁ። ከዚያም በኋላ እዚያው ቤተልሔም በአስተማሪያቸው ሥር ሆነው እያስተማሩ ተቀመጡ። መምህር ደረሰ ወደፊት የምስክርነቱን ወንበር ለወልደ ቂርቆስ ሊያወርሱት ነው ተብሎ ተወርቶ የነበረውም በዚያ ጊዜ ነው። ነገር ግን የወልደ ቂርቆስ ፍላጎትና ምኞት ወደ ሸዋ ለመመለስና ወገኖቹን ለማስተማር የተጐለቴውንም ዜማ በቤተልሔም ለመተካት ስለሆነ ከአስተማሪያቸው አስፈቅደውና ተሰናብተው በ1878 ዓ.ም. ወደ አንኮበር ተመለሱ።

[36] ቤተልሔም በጌምድር ክፍለ ሀገር ጋይንት አውራጃ የሚገኝ ቤተ ክርስቲያንና የድጓ ማስመስከሪያ ቦታ ነው። ቤተ ክርስቲያኑን ያሠራው አጼ ዳዊት በ15ኛው ምዕት ላይ ነው። ምናልባት የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የድጓ መምህር ከአባ ጊዮርጊስ ዘንድ ደብረ ነጐድጓድ የተማረው ልሳነ ዕፍረት ሳይሆን አልቀረም። እርሱም መራሔ የሚባለውን ማዕርግ አግኝቷል። ቤተልሔም ማስመስከሪያ መሆን የጀመረው ከ16ኛው ምዕት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ እንደሆነ ይነገራል። ይኸውም ሊሆን የቻለው በግራኝ ወረራ ምክንያት የያሬድ ድጓ ጠፍቶ ሲፈለግ ቤተልሔም በመገኘቱ አጼ ሠርፀ ድንግል (1555-1589 ዓ.ም) የድጓ ማስመስከሪያ እንዲሆን ወሰነ። ምንጭ - ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ *የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት።*

[37] ድጓ ተማሪው በአግባቡ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ለማስተማር እንዲችል በሊቀ ምሁራኑ ፊርማ በቤተልሔም ተረጋግጦ ለተመራቂው የሚሰጥ የዋናው ድጓ ቅጅ ነው። የሚጻፈውም በራሱ በተመራቂው ነው።



አንኮበር በደረሱ ጊዜ አጎታቸው አለቃ ገብረ ክርስቶስ በደስታ ተቀበሏቸውና ወዲያው ወምበር ዘርግተው እንዲያስተምሩ አደረጓቸው። ከዚህም በላይ ለማስከበርና ለማስወደድ ሲሉ እርሳቸው ራሳቸው ጾመ ድጓ ዘርግተው መማር ጀምረው ነበር ይባላል።

አለቃ ወልደ ቂርቆስ (በዚያ ጊዜ መሪ ጌታ) በአንኮበር ሚካኤል ሲያስተምሩ የቈዩት አንድ ዓመት ያህል ነው። ከዚያ በኋላም ሰላ ድንጋይ ማርቆስ በአቡነ ማቴዎስ ደብር እንዲያስተምሩ ጋበዙአቸውና ወደዚያ ሄደው ሦስት ዓመት አስተማሩ። የትምህርቱ ጉባኤም ስለተስፋፋ ብዙ ደቀ መዛሙርት አወጡ። ከደቀ መዛሙርታቸው አንዱ አለቃ ሠረቀ ብርሃን ፀዳሉ (የብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ ወንድም) የዚያን ጊዜውን ትጋትና የትምህርት መስፋፋት እየዘረዘሩ አጫውተውኝ የነበረውን አስታውሰዋለሁ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ የራስ ዳርጌ የጦር አበጋዝ ደጃዝማች ለየህ የጎሐ ጽዮን ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠርተው አስደብረዋት ነበርና ለዚህ ደብር አስተማሪ ሁንልኝ ብለው አባበሏቸው። ስለዚህም ሰላ ድንጋይን ትተው ወደ ጎሐ ጽዮን ሄደው አራት ዓመት ተኩል አስተማሩ። በዚህ ጊዜም ጉባኤው ተስፋፍቶላቸው ነበርና ብዙ ተማሪዎችን ለማውጣት ችለዋል። ከተማሪዎቹ መካከል አለቃ ይኄይስ የተባለው ሰው ስሙ የታወቀ ነው። በዚያ ጊዜና ከዚያም በኋላ ዜማውን አጠናቆ ስለዐወቀ የመዝገበ ድጓ አስተማሪ ሆኖ ተመርቋል። በኋለኛውም ጊዜ የጎሐ ጽዮን ደብር አለቃ ሆኖ ነበር።

አለቃ ወልደ ቂርቆስ ከዚህ በኋላ ጎሐ ጽዮንን ትተው ወደ ሀገራቸው ወደ ጅሩ ተመለሱና እምቢሎ መግደላዊት ሆነው ያስተምሩ ጀመር። የአስተማሪነታቸውም ዝና በሁሉም ዘንድ ተሰምቶ ነበርና ከልዩ ልዩ ስፍራ ልጆቻቸውን እየላኩ እባክህ አስተምርልኝ ይሏቸው ጀመር። በዚያ ጊዜ ከነበሩት ተማሪዎች በጣም የታወቁት የሚከተሉት ናቸው።

ርእሰ ደብር ምክሩና ተክለ አጋእዝት የእንጦጦ ማርያም፣ አለቃ ደስታ የድንባሮ ማርያም፣ አለቃ ደስታ የእንጦጦ ራጉኤል፣ አለቃ ዘለቀ (በኋላ መልአከ ፀሐይ የተባሉት) የጋልይ ማርያም፣ አለቃ ባልከው (በኋላ አፈ ንጉሥ ገብረ ክርስቶስ የተባሉት) የሠርፀ ክርስቶስ፣ መምህር ራስ ወርቅ የሸማ ገብርኤል፣ መሪጌታ አፈ ወርቅ የይፋት፣ እውሩ አለቃ ወልደ ማርያምና ይትባረክ የአባሌ ሚካኤል ናቸው። ለምሳሌ ያህል እነዚህን ጠቀስሁ እንጂ ተማሪው ብዙ ነበር። በዚሁም ጊዜ ዋቢ ሥላሴ በተባለ ቤተ ክርስቲያን በደብተርነት አንድ መሬት ተተክለው ነበርና አንዳንድ ጊዜ ወደ ዋቢ እየወጡ ያስተምሩ ነበር።

## ደብረ ሊባኖስ ስለመውረዳቸው

ከአድዋ ጦርነት በኋላ በ1889 ዓ.ም. እጨጌ ገብረ ሥላሴ[38] መልእክት ላኩባቸውና በደብረ ሊባኖስ ገዳም መሬት ተተክለህ አስተምርልኝ ሲሉ ጠየቁአቸው። እሳቸውም በዚሁ ስለተስማሙበት የዋቢው የደብተርነት መሬታቸውን በተፋ[39] እንዲያስገብሩ ተደረገና ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረዱ። ወዲያው ጉረኔ በሚባል ስፍራ ላይ አንድ ጋሻ መሬት ሰጡአቸውና ዜማውን ማስተማር ጀመሩ። የዜማው ጉባኤ በዚህ ጊዜ ከመቼውም የበለጠ ተስፋፍቷል። እምቢጮና ዋቢ ላይ ሲያስተምሩዋቸው የነበሩት ተማሪዎች አሁንም ተከትለዋቸዋል። በተጨማሪም ሌሎች አዲሶች ገብተዋል። ለምሳሌ እነ አለቃ ተሰማ እነ ሊቀ ጠበብት ክፍሌ፣ እነ ሣህሌ የገቡት በዚያን ጊዜ ነበር። ተማሪዎችን የሚቀጡበት «በላዔ ሰብእ» የተባለው አለንጋቸው ሥራ የተጀመረበትና ስም የወጣለት በዚህ ጊዜ ነበር። በላዔ ሰብእ የተባለበትም ምክንያት አለንጋው በተማሪዎቹ እግር ላይ ሰምበር እየጣለ ያሳምም ስለነበረ ነው።

አባቴና እናቴ የተጋቡት ደብረ ሊባኖስ በነበሩበት ጊዜ በ1889 ዓ.ም. ነው። ደብረ ሊባኖስ ለአባቴ የተከበሩበትና የታፈሩበት ስፍራ ነበረ። ዳሩ ግን ምን ይሆናል በትንሽ ነገር ተቈጥተው ከገዳሙ ሹም ጋር ተጋጩና ወደ ብዙ መዘዝ ደረሱ።

ስለ ግጭቱ ሁናቴና ስለ ምክንያቱ የሰማሁት ነገር እንደሚከተለው ነው። በዚያ ወራት ባገር ውስጥ የከብት በሽታ ገብቶ ነበርና ጸባቴ ወልደ ጻድቅ የሚባል የገዳሙ ሹም ከመንግሥት የተላከውን የከብት በሽታ መድኃኒት ለባለከብቶች ያድል ጀመር። አባቴ ሁለት ላሞች ነበሯቸውና ከመድኃኒቱ አግኝተዋል፣ ሌላውም ሰው እንደዚሁ በየደረጃው ሲቀበል ሰንብቷል። ነገር ግን ደብተራ ወልደ አረጋይ የተባለ ሰው አልተቀበለም ነበር። ይህ ሰው የአባቴ ወዳጅና አበ ልጅ ነው። ጸባቴው «መድኃኒት አልቋል» በሚል ምክንያት ይህን ደብተራ ከለከለው። ደብተራ ወልደ አረጋይም ይህን የተነገረውን ምክንያት ሳላመነም ና እኔን ለመጉዳት ሲል ከለከለኝ ብሎ ስለተበሳጨ፣ ወዲያው ለአባቴ ብስጭቱን ገልጾ ስሞታ ነገራቸው። እሳቸውም ወደ ጸባቴው ሄደው "እባክህ ከብቶቹ እንዳያልቁበት መድኃኒቱን ስጠው" ብለው ለመኑት። ጸባቴው ግን

---

[38] እጨጌ ገብረ ሥላሴ የሐማሴን ተወላጅ ናቸው። ቀደም ሲል የአክሱም ጽዮን ንቡረ ዕድ ነበሩ። እጨጌ ቴዎፍሎስ ከአጼ ዮሐንስ ዕረፍት በኋላ ሹመታቸውን በፍቃዳቸው ስለ ለቀቁ ንቡረ ዕድ ገብረ ሥላሴ እጨጌነቱን ተሾሙ። አጼ ዮሐንስ ሊቀ ካህናትነቱን ለእጨጌ ቴዎፍሎስ ነበር የሰጡት። አጼ ምኒልክ ግን ሊቀ ካህናትነቱን ለግብጻዊው ለአቡነ ማቴዎስ ነበር የሰጡት። እጨጌ ገብረ ሥላሴ ደግነታቸው የበዛ፣ ከነገር የራቁ ነበርና ሊቀ ካህናትነቱ ለእኔ ይገባኛል ብለው የክስና የሙግት ነገር አልፈለጉም። ምንጭ ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ *የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት።*

[39] ለባለ ርስት የመሬት ግብርን እየተቀበለ የሚገብር።



እምቢ ከማለቱም በላይ የስድብ ኃይለ ቃል ጨምሮ ለአባቴ መለሰላቸው። እርሳቸውም ለዚያ መልሱን ሲሰጡ ነገሩ ተባባሰና እስከ ብርቱ ጠብ ደረሱ። እንግዲህ የመድኃኒቱ ጉዳይ በጠብና በእምቢኝ ተሰናክሎ ቆመ። እንዲያውም ቂምን አትርፎ የተቀመጠ ነገር ሆነ።

እንግዲህ አንድ ያልታሰበ ነገር ሊፈጠር ነው። የደብረ ሊባኖስ ትክለኞች የሆኑ አምስት መነኰሳት እንዳጋጣሚ በዚያው ዘመን በእጨጌ ገብረ ሥላሴ ላይ የወንጀል ክስ አቅርበውባቸው ነበር። እጨጌውም በቀረበባቸው ክስ ተናደውና ተቈጥተው ወደ አጼ ምኒልክ ቀርበው "እኔ እግሬን ለጠጠር ግንባሬን ለአረር[40] ሰጥቼ በሞትሁለት መንግሥት እንዴት መነኰሴ ይከሰኛል" ብለው ተማረውና አዝነው ነገሯቸው። አጼ ምኒልክም "ከእርስዎ ይልቅ መነኰሴ ሊበልጥብኝ ነው ወይ፤ የወደዱትን ያኑሩት የጠሉትን ያባሩት" ብለው መለሱላቸው። እጨጌውም በዚሁ ቃል መሠረት "ከሳሾቼን ነቅለህ አባርልኝ" ብለው ለጸባቴ ወልደ ጻድቅ ትእዛዝ ጻፉለት።

እንግዲህ አስገራሚው ነገር አሁን ሊመጣ ነው። ጸባቴው ይህንን ትእዛዝ ባገኘ ጊዜ እነዚያን አምስቱን መነኰሳት ነቅሎ ሲያባርር በነገሩ ወስጥ ያልገቡትን ወልደ ቂርቆስንም ስድስተኛ አድርጎ ቀላቀላቸውና መሬታቸውን በሹም እጅ አስያዘባቸው።

ይህ ነገር የሆነው በ1894 ዓ.ም. በየካቲት ወር ነው። አባቴ ወዲያው አዲስ አበባ መጥተው "በቂም በቀል በግፍ ተነቀልሁ" እያሉ አቤት ቢሉ የሚሰማ ታጣ። ከእጨጌውም መልስ እንኳ ለማግኘት ችግር ሆነ። ከዚህ በኋላ አቤቱታቸውን ወደ ንጉሥ ለማቅረብ የሚችል ባለሟል ለማግኘት በደጅ ጥናት ይደክሙ ጀመር። በዚሁም ጊዜ ጸባቴው ተስፋ ለማስቈረጥ ሲል በአባቴ መሬት ሌላ ሰው እንዲተከልበት አደረገ። መሬቱ የተሰጠውም የቅኔ መምህር ለነበሩት ለአለቃ ገብረየሱስ ነበር። እንግዲህ ለአባቴ የቀረላቸው ንዴትና ብስጭት ብቻ ሆነ።

## ወደ እንጦጦ ማርያም ስለመምጣታቸው

ይህ በሆነ በዓመቱ ጥቅምት 24 ቀን 1895 ዓ.ም. እጨጌ ገብረ ሥላሴ አዲስ አበባ ላይ ሞተው ሬሣቸው ደብረ ሊባኖስ ወርዶ ተቀበረ። በዚህ ጊዜ "በግፍ ተነቀልሁ፣ ፍርድ አጣሁ፣ ዳኝነት ይታይልኝ" ሲሉ የአቤቱታ ወረቀት ጽፈው አባቴ ለእቴጌ ጣይቱ ላኩ። ወረቀቱን ያቀረቡላቸው የእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አለቃ መልአከ ፀሐይ አፈ ወርቅ ናቸው። እርሳቸው ስለ አባቴ ሙያና ስለ አስተማሪነታቸው ዝና ለእቴጌ ጣይቱ አስረዱላቸው። እቴጌ

---

[40] ጥይት።

ጣይቱም ነገሩን ከሰሙ በኋላ ለአባቴ በሌላ መንገድ መልስ ሰጡአቸው:: ቃሉም ይህ ነው:: "ባለሞያ ነህ አሉ:: አስተማሪነትህም የተመሰገነ መሆኑን ሰምቻለሁ፣ አሁን አቤት የምትለው መሬት ተነቀልሁ ብለህ ነው፣ እኔ መሬት እሰጥሃለሁና በተከልኳት ቤተ ክርስቲያን በእንጦጦ ማርያም ሆነህ አስተምርልኝ በሉት" ብለው ላኩባቸው:: የአባቴ ምኞት ያን በግፍ የሄደውን ቀላድ በፍርድ ለማግኘት ብቻ ነበር:: ዳሩ ግን እንደዚህ ያለው አቋራጭ ነገር ሲመጣ ጊዜ ከእቴጌ የቀረበላቸውን ግብዣ እምቢ ማለት የማይገባ መሆኑን ተመለከቱና እሺ ብለው ተቀበሉ:: እቴጌም የአባቴን መልስ በሰሙ ጊዜ እሳቸው ደግሞ በበኩላቸው ተቈጥተው፣ ምህርካ ከተባለ ደብተራ ላይ የነቀሉት መሬት እድአ ላይ ነበረና "እርሱን ተክዬዋለሁ ስጡት" ብለው በፍጥነት አዘዙ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አባቴ የእንጦጦ ማርያም ትክለኛ[41] ሆኑ:: መሬቱንም ተረከቡ:: እኔ ወደ እንጦጦ የመጣሁትም ይህ ነገር በሆነ በዓመቱ ነበር::

## እንጦጦ ማርያምን ስለመልቀቃቸው

አሁንም ስለ አባቴ ሁናቴ ጥቂት ቃል እጨምራለሁ፣ በእንጦጦ ማርያም የትምህርት ጉባኤ ሰፍቶላቸውና ተከብረው እስከ 1904 ዓ.ም. ድረስ ዘጠኝ ዓመት ተቀመጡ:: ይህ ሁሉ ሲሆን በግፍ የተነቀልሁትን የደብረ ሊባኖስ መሬቴን በፍርድ አስመልሳለሁ የሚለው ሐሳብ ገና አልተለያቸውም ነበር:: ስለዚህ የጊዜውን መለወጥ እያዩ አቤቱታ ከማቅረብ አልቦዘኑም:: የመንግሥቱ እንደራሴ ራስ ቢትወደድ ተሰማ ናቸው:: በ1903 ዓ.ም. በሞቱ ጊዜ የመንግሥቱን ሥልጣን ልጅ ኢያሱ በእጃቸው አደረጉና አሽከሮቻቸውን በሥልጣን ላይ አስቀመጧቸው:: በተለይም የእናታቸው የወይዘሮ ሸዋ ረጋ ርስት ጠባቂና ነገረ ፈጅ የነበሩትን አቶ ጥላሁንን በፍጥነት በሥልጣን ከፍ ከፍ አደረጓቸው፣ ማለት ራስ ተሰማ ከሞቱ ከአንድ ወር በኋላ በግንቦት ወር አቶ ጥላሁን ቀኛዝማች ተባሉ፣ ቀጥሎም ወዲያው በሐምሌ ወር ፊታውራሪ ተባሉ:: ቀጥሎም በነሐሴ ወር ለቤተ መንግሥቱ እንደ ቢትወደድ ሆነው ያዝዙበት ጀመር፣ በተከታዩም ዓመት 1904 ዓ.ም. የመንዝ ወምበርነት[42] ተጨመረላቸውና የስማቸው ገናናነት በአንድ ጊዜ ወደ ሰማይ ዘለለ::

እንግዲህ አባቴ ያን የደብረ ሊባኖስ መሬት ነገር በፍርድም ሆነ በባለሥልጣን ትእዛዝ ለማግኘት የምችልበት ጊዜው እነሆ ደረሰ ብለው አሰቡ:: ተፈጻሚነቱም በፊታውራሪ ጥላሁን አማካይነት ሊሆን እንደሚችል አመኑ:: ይሁን እንጂ ከፊታውራሪ ጥላሁን ጋራ በሚገባ ለመተዋወቅ አስቀድሞ አንድ ስጦታ ወይም ውለታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆነ:: በነገሩ ካሰቡበት በኋላም እቴጌ

[41] ለሚሰጠው የቤተ ክርስቲያን ቋሚ አገልግሎት ከመንግሥት የቋሚ ርስት ባለቤትነት መብት የተሰጠው::

[42] ዳኝነት::



ጣይቱ የተከሏቸውን የአድአውን ቀላድ ለፊታውራሪ ጥላሁን በውርስ መስጠትና የደብረ ሊባኖሱን መሬት ማግኘት ይሻላል ብለው አሰቡ:: ይኸውም ነገር በወዳጃቸው በልጅ ሥዩም ወልደ ያሬድ አማካይነት ለፊታውራሪ ጥላሁን ቀረበና "መልካም ነው፣ አስቀድሞ ውርሱን በዳኛ ላይ ያረጋግጥልኝ፣ ከዚያ በኋላ የእርሱን ነገር እንፈጽመዋለን" ተባለና የቃል ስምምነት ተደረገ::

አለቃ ወልደ ቂርቆስ በማግሥቱ ወደ ወምበሩ ወደ ቀኛዝማች ከፈለው ችሎት ሄደው የአድአ መሬቱን ለፊታውራሪ ጥላሁን አውርሻለሁ ሲሉ ተፈጥመው አስመዘገቡ:: የፊታውራሪ ጥላሁንም ነገረ ፈጅ አለቃ ምንተስኖት (በኋላ ቀኛዝማች የተባለ) ውርሱን ተቀብያለሁ ብሎ በመዝገብ አስጻፈና ነገሩ በዚህ አለቀ:: ከዚህ በኋላ አባቴ ስለ ደብረ ሊባኖስ መሬት ነገር ፊታውራሪ ጥላሁንን መለመንና ደጅ መጥናት ሆነ:: ሁለት ወር ያህል እየተመላለሱ ከደከሙ በኋላ ፊታውራሪ ጥላሁን ለደብረ ሊባኖሱ ጸባቴ አንድ የትእዛዝ ደብዳቤ ጽፈው ሰጡአቸው:: ቃሉ የሚለው "ከባላጋሮቹ ጋር በቶሎ አፈጣጥመህ[43] ላክ፤ ባለጋራ ካልቀረበም መሬቱን ለአለቃ ወልደ ቂርቆስ አስረክብ" የሚል ነበረ:: ፊታውራሪ ጥላሁን ወምበርነታቸው ለመንዝ እንጂ ለደብረ ሊባኖስ ስላልሆነ ይህን ትእዛዝ የጻፉት በዘመናይነት ሥልጣናቸው ነበር:: ሆኖም በዚሁ ሥልጣናቸው ሁሉንም ያዝዙበት ነበርና አባቴም ይህን ትእዛዝ በማግኘታቸው ተደስተው ማኀተሙን ይዘው ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረዱና በዘመኑ ለነበሩት ሹም ለጸባቴ ታመነ ሰጡ:: ጸባቴውም ደብዳቤውን አክብሮ ተቀበለና እንደ ትእዛዙ ይፈጸም ብሎ አዘዘ:: በትእዛዙ መሠረት ባለጋራ እንዳለ ተብሎ ቢጠየቅ መሬቱን የተተከሉት አለቃ ገብረ ኢየሱስ ቀረቡ:: እሳቸው ደግሞ ደግፌ የተባለውን ተማሪያቸውን ነገረ ፈጅ አደረጉና ወደ አዲስ አበባ ለመውጣት ተፈጣጠሙ:: በዚህ ጊዜ እኔ የ14 ዓመት ዕድሜ ሆኜ ሳለሁ አባቴን ተከትዬ ሄጄ ነበርና ሁሉንም አስታውሰዋለሁ::

አዲስ አበባ ስንደርስ ሙግቱ በአፈ ንጉሥ እስጢፋኖስ ላይ እንጂ በፊታውራሪ ጥላሁን ላይ አለመሆኑን ተረዳን:: ምክንያቱም የደብረ ሊባኖስ ገዳም ዳኝነት የአፈ ንጉሡ ክፍል ስለነበረ ነው:: እንግዲህ በአፈ ንጉሥ ችሎት ተከራክሮ መዋልና ባልተወሰነ ቀጠሮ ሲጓተቱ መክረም ሆነ::

በዚሁ መካከል ከእቴጌ ጣይቱ የተወረወረው የቊጣ ቃል በአባቴ ላይ የችግር መጀመሪያ ሆነ:: እቴጌ ጣይቱ በዚያ ዘመን በመሃል ሰፋሪ አድማ[44] ከመንግሥት ሥልጣን ወጥተው በቤተ መንግሥቱ ግቢ ብቻ አጼ ምኒልክን

[43] አዋውለህ፣ አፈራርመህ::

[44] . . . መሃል ሰፋሪ የሚባለው የመንግሥት የጦር ኃይል በእቴጌ ጣይቱ ላይ አድማ መቋጠር ያዘ:: የአድማው ዓላማ ባጭሩ "እቴጌ በመንግሥት ሥራ ላይ አይግቡብን፣ እንደራሴው ብቻ ያስተዳድሩን" የሚል ነው:: በዚህ ጊዜ ለአድማው አፈ ጉባኤ ሆነው የተነሡት ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብርና እነ ደጃዝማች ደምሰው ነሲቡ እነ ቀኛዝማች ወሰኔ ትርፌ ነበሩ:: . . . ምንጭ - መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ* ገጽ 62::

እያስታመሙ ተቀምጠው ነበር። አንዳንድ ጥቃት እንዳይደርስባቸውም የዘመናይዎቹን የእነፊታውራሪ ጥላሁንን ወዳጅነት የሚፈልጉበት ሰዓት ነበረ። አባቴ የአድአውን መሬት ለፊታውራሪ ጥላሁን እንዳወረሱት በሰሙ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ በጣም ተቈጥተው ነበር። ምክንያቱም መሬቱን ለዘመናይ ሰው ለጥላሁን ያወረሰው እኔን ለማጥቃት አስቦ ነው ወይ በማለት ነበር ይባላል። ከዚህ በኋላ ወደ ፊታውራሪ ጥላሁን ሰው ልከው እንዲህ አሏቸው፣ "እኔ የሰጠሁትን መሬት ወልደ ቂርቆስ ምን ያወርስሃል እርሱን ነቅዬ ለአንተ ሰጥቼሃለሁ" ብለው ላኩባቸው። ወዲያውም ይህንኑ ትእዛዝ በማኅተማቸው አትመው ለደብሩ አለቃ አስተላለፉላቸው። ፊታውራሪ ጥላሁን ይህን ቃል በሰሙ ጊዜ "አንድ ደብተራ ከሚሰጠኝና ከሚያወርሰኝ ይልቅ የእቴጌ ጣይቱ ስጦታ አይበልጥም ወይ" ብለው በደስታ ተቀበሉት። የአድአውም መሬት በአባቴ ስም መሆኑ ቀርቶ በፊታውራሪ ጥላሁን ስም ተዛውሮ በደብሩ መዝገብ ላይ ተጻፈ።

የደብረ ሊባኖሱ መሬት ሙግት በአፈ ንጉሥ እስጢፋኖስ ችሎት እንደ ቀጠለ ነበር። አንድ ቀን ነገሩ በችሎት ላይ ቀረበና የአለቃ ገብረ ኢየሱስ ነገረ ፈጅ ደግፌ ነገሩን ዘረዘረ። ማስረጃ ያደረገውም እጨጌ ገብረ ሥላሴ የወደዱትን እንዲያኖሩ ያልወደዱትን እንዲነቅሉ ከጃንሆይ ከአጼ ምኒልክ ተፈቅዶላቸዋል የሚለውን ቃል ነበር። የአባቴም መልስ "ይህ ፈቃድ የተሰጠው ስለ አምስቱ መነኰሳት ነው፣ እኔ ግን በማናቸውም ነገር ያልገባሁ ነኝ፣ ጸባቴው በግል ጥላቻ ብቻ ቀላቅሎ ነቅሎኛልና ይህንኑ ላስረዳ" የሚል ነበር። አፈ ንጉሥ እስጢፋኖስም ነገሩን ቀበል አድርገው "እጨጌ ገብረ ሥላሴ የወደዱትን እንዲያደርጉ መፈቀዱን ዐውቃለሁና አላከራክርም ተመለስ" ብለው ነገሩን በብይን ዘጉት፣ አባቴም እያዘኑ ከችሎት ተመለሱ።

አባቴ ይህን የደረሰባቸውን ነገር ለፊታውራሪ ጥላሁን በመግለጽ እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ጠየቁ። ያገኙትም መልስ በአፈ ንጉሥ ችሎት የተበየነውን የሚገለብጠው የጌታዬ የልጅ ኢያሱ ችሎት ስለሆነ እኔ የምገባበት መንገድ የለኝም የሚል ነበር። አባቴ አቤቱታቸውን ለልጅ ኢያሱ ለማቅረብ ፈልገው ቢወጡም ቢወርዱም የማይሳካ ሆነ። ልጅ ኢያሱን ለማግኘትና አቤት ለማለት እንኳ በፍጹም የማይቻል ሆነባቸው። ከዚህ በኋላ ልባቸው እያዘነ ወደ ሀገራቸው ወደ ጅሩ ወርደው ተማሪዎቻቸውን እያስተማሩ ቀድሞ በነበራቸው በጅሩ ርስታቸው ላይ ተቀመጡ። ይህ የሆነው በ1905 ዓ.ም. ነው።

## ቀበና አቦን ስለ መሾማቸው

አፈ ንጉሥ እስጢፋኖስ በ1907 ዓ.ም. በዘመነ ሉቃስ ተሻሩና ፊታውራሪ ጥላሁን አፈ ንጉሥ ተብለው ተሾሙ። ወዲያው በዚያው ጊዜ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም አንድ ቤተ ክርስቲያን ተከሉ። በዚህ ጊዜ አባቴን ከጅሩ አስጠሩዋቸውና ለዚህ ቤተ ክርስቲያን አለቃ አድርገው ሾሟቸው። አፈ ንጉሥ ጥላሁን ይህን ማድረጋቸው የአድአውን መሬት ምንም እንኳ እቴጌ ጣይቱ በስጦታ ቢተኩሏቸው ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የውርሱ ጉዳይ



መሆኑን በማሰብና ውለታ ለመክፈል ሲሉ ነው። ሹመቱንም ከቤተ መንግሥት አስፈቅደው አጸደቁላቸው።

አባቴ በዚህ በቀበና አቦ ሹመታቸው ሁለት ዓመት ተኩል ያህል ቈይተውበታል። ሹመቱንም ሲቀበሉ የደብረ ሊባኖሱን መሬት ነገር ወደ ልጅ ኢያሱ ለማቅረብ ምናልባት ጊዜ ያጋጥመኝ ይሆናል በሚል ተስፋ ነበር እንጂ ለሹመቱ አንዳችም ጉጉት አልነበራቸውም። ወዲያው እንደ ተሾሙ ደብተራ ወልደ መስቀልን አጋፋሪ አድርገው ሹመትና ማናቸውንም የአስተዳደር ሥራ እርሱ እንዲፈጽም አደረጉ። እርሳቸውም ከያገሩ የተሰበሰቡትን የድሮ ደቀ መዛሙርትና አዲሶቹንም ተማሪዎች እያስተማሩ በአፈ ንጉሥ ጥላሁን ግቢ ተቀምጠው ነበር።

## ቀበና አቦን ትተው ወደ ሀገራቸው ስለመመለሳቸው

በ1909 ዓ.ም. ልጅ ኢያሱ ከዙፋን ተወግደው የመንግሥቱ ሥልጣን ለሌላ ተላለፈ። ወይዘሮ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ተብለው በአልጋው ላይ ሲቀመጡ ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ልዑል ራስ ተብለው አልጋ ወራሽና እንደራሴ ሆኑ። ሰገሌ ላይ በተደረገው ውጊያ ንጉሥ ሚካኤል ድል ሆነው ተማረኩ። ከልጅ ኢያሱ ባለሟሎች አብዛኞቹ ከማዕርጋቸው ተዋረዱ። አፈ ንጉሥ ጥላሁን በዚህ ጊዜ ምንም እንኳን አፈ ንጉሥነቱን ገና ባይለቁ ሥልጣናቸው እየደከመና እየቀዘቀዘ መሄድ ጀምሮ ነበር። አባቴም ስለ ደብረ ሊባኖሱ መሬት ጉዳይ በአፈ ንጉሥ ጥላሁን ላይ የነበራቸው ተስፋ ዋጋ የሌለው መሆኑን ተመለከቱ። ስለዚህ በዚሁ ዘመን 1909 ዓ.ም. ሹመቱን በገዛ ፈቃዳቸው ትተው ወደ ሀገራቸው ገብተው ተቀመጡና ምድቅ በተባለ ስፍራ የትምህርት ጉባኤ ተስፋፍቶላቸው ያስተምሩ ጀመር። በዚህ ጊዜ ከነበሩት ደቀ መዛሙርት ለጊዜው የማስታውሳቸውን ቀጥሎ እጽፋለሁ።

| | |
|---|---|
| ዘሊባኖስ ፣ | የሽማ ገብርኤል |
| ወልደ ዮሐንስ፣ | የሽማ ገብርኤል |
| ወልደ ሐና፣ | የሽማ ገብርኤል |
| አፈ ወርቅ ወልዱ፣ | የመግደላዊት |
| ወልደ ማርያም ይደመሙ፣ | የአባሌ ሚካኤል |
| ሀብተ ማርያም ገብረ መድኅን፣ | የተጕለት |

ሌሎችም ብዙዎች ነበሩ።

አባቴ አለቃ ወልደ ቂርቆስ በ1914 ዓ.ም. ጥቅምት 10 ቀን በዕለተ ኀሙስ ዐርፈው በደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ተቀበሩ። መቃብራቸውም የጠበሉ አሸንዳ ካለበት ጥቂት ዝቅ ብሎ አንድ ትልቅ አፀድ አጠገብ ነው። እነሆ ስለ አባቴ ታሪክ በዝርዝር ሳይሆን በአጭሩ የጻፍሁትን እዚህ ላይ አቆማለሁ።

## ስለ እናቴ ዜና

የእናቴ የወይዘሮ የሸዋ ወርቅ የትውልድ አገር በአባትም በእናትም በኩል መራቤቴ ነው። አባትዋ ምናጣ፣ እናትዋ መካለያ ይባላሉ፣ የአባትዋ አገር ግሬት እግዚአብሔር አብ፣ የእናትዋ አገር ሠርግና ማርያም የተባለው ስፍራ ነው። የግሬቱ ትውልድ የግንድ አባቱ አዲሱ ይባላል። የምናጣ የወንድሞቹ ልጆች በግሬት ይገኛሉ። ከእነርሱም አንዱ አባ ሀብተ ማርያም የተባለ ትልቅ ሰው ነበረ።



10 እመቤት የሸዋ ወርቅ ምናጣ

የሠርግናው ትውልድ የግንድ አባት ስም ምሰለው ይባላል። የርስቱ ልዩ ስም አስቀሬጣ ይባላል። የትውልዱም አኳኋን እንደሚከተለው ነው።

ምሰለው ከሠርግና የአዲሱን ልጅ አስፋሁን አግብቶ ወሰንን፣ በለጥህን፣ ታየርን፣ እነዚህን ሦስቱን ወለደ። ወሰን መካለያን ወልደ ጊዮርጊስን ወለደ። መካለያ ከግሬት ምናጣን አግብታ የሸዋ ወርቅን ወለደች። የሸዋ ወርቅም መርስዔ ኀዘንን መሻገሪያንና ቦጋለችን ወለደች (ገጽ 32 ይመልከቱ)። የወልደ ጊዮርጊስ ልጅ ዘርጊ፣ የዘርጊ ልጅ ባዩ ይባላል።

የታየር ልጆች ያጅቡና ወለተ አማኑኤል ናቸው። ያጅቡ መምሬ ገስጥንና ደሴን ወለደች። የደሴ ልጅ ማሙዬ ይባላል።



በለጥህ አጃቢንና ዘርፍነሽን ባፈናን ወለደ፣ አጃቢ ፈለቀችን ወለደች፣ ባፈና ድባቧን ወለደች፣ ድባቧ ጅሩ ምድቅ ላይ አግብታ ተከተልንና ለማን ሌሎቹንም ወለደች።

ከዚህ ቀጥሎ የምጽፈው ስለ እናቴ ሁናቴ ጥቂት መግለጫ ለመስጠት ነው። እናቴ ወይዘሮ የሸዋ ወርቅ በ1863 ዓ.ም. ከግሬቱ ከአቶ ምናጣና ከወይዘሮ መካለያ ሠርግና ላይ ተወለደች። ያደገችውም ግሬት በአባትዋ አገር ነው። አባትዋ አቶ ምናጣ የመንግሥት ነፍጠኛ ነበርና ጅሩ ላይ የማደሪያ መሬት ተሰጥቶት ሲሄድ ተከትላው ወደ ጅሩ መጣች። እዚያ ሳለች ለአንድ የመራቤቴ ሰው ተዳረችና ወደ መራቤቴ ተመልሳ ሠርግና ላይ ሰባት ዓመት ያህል ተቀመጠች።

ከዚህ በኋላ ከባሏ ተፋትታ ወደ ጅሩ እንደገና መጣችና ከአባትዋ ዘንድ ተቀመጠች። በዚሁ ጊዜ ሲሳይ የተባለ የቄላ ሰው ከጠንበላ እስጢፋኖስ መጥቶ አገባት። ከእርሱም እኅቴን መሻገሪያ ሲሳይን በ1882 ዓ.ም. ወለደች። ቀጥሎም ከአቶ ሲሳይ ተፋትታ የፊታውራሪ ተክሌ ባልደረባ የሆነ አንድ ወታደር አግብታ ወለጋ ሄደች። እዚያም ሳለች በ1886 ዓ.ም. እኅቴን ወለተ ጻድቅን ወለደች።

ከዚህ በኋላ ከባልዋ ተፋትታና ከወለጋ ተመልሳ ጅሩ ሳለች በ1889 ዓ.ም. አባቴን አለቃ ወልደ ቂርቆስን አገባች። በ1891 ዓ.ም. እኔን ወለደች። ቀጥሎም ከአባቴ በ1892 ዓ.ም. ተፋታችና ባሻ ዳምጠው የተባሉትን የመንግሥት ነፍጠኛ አግብታ ሰባት ዓመት ያህል አብረው ተቀመጡ። ከዚያም በኋላ ከአባቴ ጋር እንደገና ታርቃ ጥቂት ወራት እንጦጦ ላይ ተቀመጠች። ከዚያም እንደገና ወደ ጅሩ ተመልሳ ጥቂት ጊዜ እንደ ቈየች በ1902 ዓ.ም. ጭራ ወንዝ ላይ አቶ ይገዙ የተባሉ ነፍጠኛ አግብታ ሐያ አንድ ዓመት አብረው ኖሩ። ከዚያ በኋላ በእርጅና ምክንያት ተለያዩ። እናቴ ወይዘሮ የሸዋ ወርቅ በታላቂቱ ልጅዋ በእመቤት መሻገሪያ አጠገብ ቤት ተሠርቶላት ዲላሞ ጊዮርጊስ ላይ በጡረታ ተቀምጣለች[45]።

የእናቴ አባት አቶ ምናጣ በንጉሥ ኃይለ መለኮትና በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ነፍጠኛ ከመሆኑም በላይ በግብርና ሥራም የተመሰገነ ገበሬ ነበረ። ጅሩ ሜንሮሙ በሚባል ስፍራ አንድ የማደሪያ መሬት[46] ተሰጥቶት በዚያው ይቀመጥ ነበር። አቶ ምናጣ «ክፉ ቀን» በሚባለው በረሃቡ ጊዜ ለወገኖቹና ለጎረቤቶቹ እህል እየሰጠ ከዚያ ከረሃብ ዘመን ስላወጣቸው፣ "በምናጣ ወጣሁ ስቀናጣ" ተብሎ ግጥም ተገጥሞለት ነበር። የአቶ ምናጣ ልጆች ሁለት ሴቶች ብቻ

[45] እመቤት የሸዋ ወርቅ ሐምሌ 4 ቀን 1946 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ሥርዓተ ቀብራቸው ጅሩ ዲላሞ ጊዮርጊስ ተፈጽሟል።

[46] ጉልት ርስት።

ናቸው። አንዷቱ የእኔ እናት ወይዘሮ የሸዋ ወርቅ ስትሆን፣ ሁለተኛዋ ታናሽቱም ወይዘሮ ቸሩኝ ናት። እርስዋም ያጅቡሽን ወለደች። ያጅቡሽም ብዙ ልጆች ወልዳለች።

አቶ ምናጣ በዚያች በማደሪያ መሬቱና በነፍጠኛነት ተግባሩ አድዋ ላይ ከኢጣልያኖች ጋር ሲዋጋ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. በጦርነት ውስጥ ሞቶ ቀርቷል። እነሆ የወላጆቼን ዜና ባጭሩ ጽፌ አቆምሁ።

# ምዕራፍ 4

## 1897 ዓመተ ምሕረት

ስለ ዳዊት ትምህርት፣ የዜማ ስልት ለማዳመጥ እንደ ተመደብሁ፣ በስሕተት ስለደረሰብኝ ቅጣት

## ስለ ዳዊት ትምህርት

ገበተዋሪያ[47] (ወይም ገበተ ሐዋርያ) የሚባለውን የትምህርት ክፍል ከጨረስሁ በኋላ ወደ ዳዊት ተዛወርሁና በዚያው ዓመት ውስጥ ዳዊት ደገምሁ። በዚህ ጊዜ የሰባት ዓመት ዕድሜ ሆኛለሁ። ዘመኑም በ1897 ዓ.ም. ነው። ዳዊት ለመማር እምብዛም ጊዜ አልወሰደብኝም። ምክንያቱም በገበተዋሪያ ላይ የንባቡን ስልት በሚገባ ተለማምጄ ስለነበረ ነው። ደግሞም አባቴ እርሳቸው ራሳቸውና ባለቤታቸው ወይዘሮ ወለተ እስራኤል በጥንቃቄና በትጋት ያስተምሩኝ ስለነበረ፣ ዳዊት ተምሮ ለመጨረስ ከመንፈቅ የበለጠ ጊዜ አላባከንኩበትም።

እንጦጦ በደረስሁበት ጊዜ ከቤት የነበረችው የአባቴ ሚስት ከአዲስ አበባ የመጣች አንዲት ወጣት ስለመሆንዋ ባለፈው ምዕራፍ ገልጫለሁ (ገጽ 36)። አሁን በዚህ ዘመን ግን አባቴ እርስዋን ፈትተው ወይዘሮ ወለተ እስራኤልን አግብተዋል። እኒህ ሴት የትውልድ አገራቸው ይፋት ወረዳ ማህፉድ[48] ሚካኤል ነው። አባታቸው በዚያ ደብር የተጉለቴ ዜማ መምህር ስለሆኑ ሴቲቱ በሚገባ ዳዊት ተምረዋል። እንዲያውም ዜማውን በድምጫ ለምደውት ዜማ ዐዋቂ እስከ መባል ደርሰዋል። ወይዘሮ ወለተ እስራኤል ጠባየ መልካምና መልከ ከደም ግባት ያስተባበሩ በዕድሜ ከሙሉ ሰውነት የደረሱ፣ ድልድል ሴት ናቸው። የፊተኛይቱ የአባቴ ሚስት በሆነ ባልሆነው ነገር ስለምታመናጭቀኝ ሁልጊዜ እሳቀቃት ነበር። አሁን ግን እኒህ አዲሲቱ የእንጀራ እናቴ እንደ ልጃቸው አድርገው በርኅራኄ ስለተመለከቱኝ ዕድል አገኘሁ። ዳዊት በተማርሁበትም ጊዜ በትርፍ ጊዜያቸው ያስጠኑኝ ነበር። ከዚህ የተነሣ ዳዊቱን ከሥር እስከ ጫፍ አንድ ጊዜ ዘለቅሁትና እንደገና ሁለት ጊዜ ከለስሁት። በዚህ ጊዜ ከዳዊት አብዛኛውን ከሞላ ጎደል በቃል ለመያዝና ለመድገም እስከመቻል ደርሼ ስለነበረ ወይዘሮ ወለተ እስራኤል እገሌን ውጣልኝ እያሉ ይጠይቁኝ ነበር። ለጥያቄውም መልሱን ወዲያው ስሰጣቸው

47 ከፊደል ቀጥሎ ንባብ የሚጠናበት ትምህርት።

48 ይፋት ውስጥ የሚገኝ የነጋዴዎች መናኸሪያ።

"ጎሽ፣ አበጀህ" እያሉ በአባቴ ፊት ስለሚያሞግሱኝ በትጋት ላይ ትጋትን ለመጨመር ምክንያት ሆኑልኝ።

## የዜማ ስልት ለማዳመጥ እንደ ተመደብሁ

ዳዊት ከጨረስሁ በኋላ በዜማ ጀማሪዎች ክፍል ሆኜ የዜማ ስልት እንዳደምጥ ተመደብሁ። ይሁን እንጂ ዳዊቱን እንዳልገድፍ አባቴ አሁንም ገና ይቈጣጠሩኛል። «ወደፊት ከመቀጠል የተያዘውን ማብሰል» እንደሚባለው ሁሉ የአባቴም የማስተማር ዘዴ ይህንኑ የተከተለ ነበር። ስለዚህም ዳዊት እንዳልገድፍ አዘውትሬ የምደግመውን ከፋፍለው መድበው አስታወቁኝ። የሰኞ ድጋም ከፍካሬ እስከ አኮኑ ሲሆን፣ የማክሰኞ ድጋም ከአኮኑ እስከ ብፁዕ ብእሲ ድረስ፣ የረቡዕ ድጋም ከብፁዕ ብእሲ እስከ ሰሎሞን መጨረሻ ድረስ ነበር። በዚህም ዓይነት ኀሙስና ዓርብ ቅዳሜ መድገም ነበረብኝ።

ከዚህ በላይ የጠቀስሁትን የዳዊት ክፍል የምደግመው የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ወደሚቀመጡበት ወደ ዕቃ ቤቱ እየሄድሁ ነበር። ምክንያቱም መጽሐፍ ለማግኘት ሲባል ነው። በዚያ ጊዜ እንደ ዛሬው ዘመን በወረቀት የታተመ ዳዊት ፈጽሞ አልነበረም። ማናቸውም መጽሐፍ የሚጻፈው ከበግ ወይም ከፍየል ቆዳ እየተፋቀ በሚዘጋጀው በብራና ላይ ነበር። ስለዚህ ሃብታሞች ካልሆኑ በቀር ሌሎች በመጽሐፍ ረገድ ይቸገሩ ነበር። የዕቃ ቤቱ ጠባቂ ደብተራ ወልደ ጻድቅ ይባላል። ይህ ሰው ሁለት እግሮቹ የተሽመደመዱና በሁለት የእንጨት ብርኩማ እየተንኳተተ የሚሄድ ነው። ቤተሰቦቹ የሚቀመጡበት አንድ ቤት በእኛ ቤት አጠገብ አለው። ይሁን እንጂ እርሱ የማያድረውና አብዛኛውን ጊዜ የሚውለው በዚያው በዕቃ ቤቱ ውስጥ ነው።

እኔ ጧት ወደ ዕቃ ቤቱ ስሄድ ደብተራ ወልደ ጻድቅ ከተከመሩት መጻሕፍት መካከል አንድ የብራና ዳዊት ይሰጠኛል። እኔም እጅ ነሥቼ ተቀብዬ እደግምና መልሼ አስረክባለሁ። ቤተሰቦቹን ለመጐብኘት ወደ ቤቱ ሲሄድ ሳለ፣ መንገዱ በኛ ቤት በኩል ነውና ከአባቴ ጋር ሲገናኙ "ያ ውርፍ" እየመጣ ይደግማል ወይ?" እያሉ ሁልጊዜ ይጠይቁታል። እርሱም "አዎን ይደግማል አስታጉሎ አያውቅም" እያለ ይመልስላቸዋል፣ «ያ ውርፍ» የሚለው ቃል እኔን የሚያመለክት የተግሣጽ ቃል ነው።

## በስሕተት ስለደረሰብኝ ቅጣት

አንድ ቀን ደብተራ ወልደ ጻድቅ ነገር በማሳሳት በእኔ ላይ ችግር ፈጠረ። ሰዓቱ እኩለ ቀን ላይ ነው፣ ወደ ቤቱ ለመሄድ በእኛ ቤት በኩል ሲያልፍ አባቴ አዩትና ሰላምታ ከሰጡት በኋላ "ያን ውርፍ አይተኸዋል ወይ?" ብለው ጠየቁት። እርሱም "እኔ አላየሁትም" ብሎ መለሰላቸውና መንገዱን ቀጠለ። እኔ በዚያ ጊዜ ከዜማ ተማሪዎች ጋር ስለነበርሁ ጥያቄውንም መልሱንም ከቶ



አልሰማሁም። አባቴ ግን ዳዊት ያልደገምሁ መስሏቸው ተናደዋል። ጥቂት ቈይተው ጠሩኝና "ዛሬ ዳዊት ደግመሃል ወይ?" ብለው በጥሞና ቃል ጠየቁኝ። እኔም ያለ ምንም ማመንታት "አዎን ደግሜአለሁ" ብዬ ወዲያውኑ መለስሁላቸው። እርሳቸው ግን ቀና ብለው አዩና "ተው እውነቱን ንገረኝ የዋሸህ እንደሆነ በአለንጋ እገርፍሃለሁ" ብለው አስጠነቀቁኝ። እኔም "ኧረ እውነት ነው፣ ደብተራ ወልደ ጻድቅ እንኳ አይቶኛል፣ ዳዊቱንም የሰጠኝ እርሱ ነው" ብዬ መለስሁላቸው። ከዚህ በኋላ "አንተ ውርፍ ለምን ትዋሻለህ አሁን ደብተራ ወልደ ጻድቅ አላየሁትም ብሎኝ የለም ወይ?" አሉና በላዔ ሰብእ የተባለ አለንጋቸውን አነሡ። ቀጥሎም አንዱን ተማሪ "በል ጣለው" ብለው አዘዙትና ብድግ አድርጎ ከመሬት አጋደመኝ። እንግዲህ በአለንጋ ይጠበጥቡኝ ጀመር። እኔም "ኧረ ማርያምን እውነት ነው ደግሜአለሁ አልዋሸሁም" እያልሁ እለፈልፍ ጀመር። ነገር ግን ቃሌን የሚያምንልኝ አላገኘሁም። ሰውነቴ ተቈጥቶ ነበርና ያ ሁሉ ድብደባ ሲወርድብኝ እንባ እንኳ ከዓይኔ ላይ አልወጣም። ንግግሬም ከዚያው ከፊተኛው ቃል ምንም አልተዛባም ነበር። ከዚህ በኋላ መደብደብ ሰለቻቸውና "ወስዳችሁ እሰሩት እውነቱን ካልተናገረ ምሳ አይብላ" ብለው አዘዙ። ወዲያው አንድ ተማሪ የእንስራ ማንገቻ ገመድ ከወደ ጓዳ ፈልጎ አመጣና እግሬን አስሮ በአመራሮ ዛፍ ሥር አስቀመጠኝ።

ከእኩለ ቀን በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ደብተራ ወልደ ጻድቅ ወደ ዕቃ ቤቱ ለመመለስ በዚያው በእኛ ቤት በኩል ሲያልፍ አዩትና ጠርተው እንዲህ አሉት። "ይህ ውርፍ ውሸት ለመደ የጉዱ ብዛት ዛሬ ጧት ደብተራ ወልደ ጻድቅ አይቶኛል ዳዊት የሰጠኝም እርሱ ነው ሲል በውሸት ቃል ስለረጋ ተገርፎ ታስሯል" አሉትና፣ ገና ነገሩን ሳይጨርሱለት ደብተራ ወልደ ጻድቅ ቀበል አድርጎ "ጧትማ መጥቶ ደግሟል፣ ዳዊት የሰጠሁትም እኔ ራሴ ነኝ፣ አላየሁትም ያልኩዎት እኮ በዚያ እኔን በጠየቁኝ ሰዓት ነው" አላቸው። ቀጥሎም "አዬ የኔታ መልካም አላደረጉም በሕፃን ልጅ ይህን ያህል ለምን ይጨክናሉ" ብሎ ወቀሳቸው።

ይህን በሰማሁ ጊዜ መጠቃቴን ተገንዝብሁትና እንባዬ ይዝረከረክ ጀመር። በዚህ ቀን የተደረገብኝን ቅጣትና ልቅሶዬን እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ እያስታወስሁት ይቆጨኝ ነበር። ከዚህ በኋላ ከእስራት እንድፈታ አዘዙልኝና ወደ ትምህርቴ ተመለስሁ። ደብተራ ወልደ ጻድቅም "አዬ ጉድ በእኔ ምክንያት ተገረፈ" እያለና እያዘነ ወደ ዕቃ ቤት ተጓዘ። ከዚህ ቀን በኋላ «ያ ውርፍ» የሚሉትን የተግሣጽ ስም ፍቀውልኛል። ቅጣት ግን ያጠነክሩብኝ ነበር። ተማሪዎችን የሚቀጡበት አለንጋቸው በላዔ ሰብእ የተባለ ስም ነበረው። ምክንያቱም የሰውን አካላት ክፉኛ ያቈስል ስለነበረ ነው። በዚህም ጊዜ ሥራውን እንደ ቀጠለ ነበርና አብዛኛውን ጊዜ እኔን የሚቀጡኝ በዚህ አለንጋ ነበር።

# ምዕራፍ 5

## 1898 ዓመተ ምሕረት

**ስለ ዜማ ትምህርት፣ ስለ መሬት መንቀጥቀጥ፣ ክህነት ስለመቀበሴ፣ ስለ ሆሳዕና በዓልና ስለ ጽጌ በዓል**

### ስለ ዜማ ትምህርት

ለዜማ ተማሪ የዜማ መልመጃው ውዳሴ ማርያም ነው፣ ከዚያ ወደ መስተጋብእ ያልፋል፣ ይኸውም በመጽሐፍ ሳይሆን በቃል የሚጠና ትምህርት ነው[49]:: መስተጋብእ ካለቀ በኋላ ቀን ጾመ ድጓ በመጽሐፍ ይማራል:: ማታ ማታ አርባዕት፣ አርያም፣ ሠለስት፣ የተባሉትን የቃል ትምህርቶች እንደየተራቸው ይማራል:: እኔም ደንቡን በመከተል ጾመ ድጓና የቃል ትምህርቶችን ተማርሁ:: አባቴ ጾመ ድጓ ስለነበራቸው እንደ ሌላው ተማሪ በመጽሐፍ በኩል አልተቸገርሁም፣ ወይም በወምበር ገፍ እንድማር አልተገደድሁም:: ስለዚህ ከወምበረተኛዬ[50] ከገብረ ኪዳን ወረደ ጋር ዘወትር እየተማርን ጾመ ድጓውን በቶሎ ጨረስንና እንደገና ክላሽ ተያያዝነው:: ዋናውንና ክላሹን ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ ችለናል:: በአስተማሪም ረገድ ምንም እንኳ እንደ ሌላው ሁሉ በተወራጅ መማራችን ያልቀረ ቢሆን አብዛኛውን ጊዜ ያስተማሩን አባቴ ራሳቸው ናቸው::

ጾመ ድጓ የጨረስሁት በ1898 ዓ.ም. ላይ ነው፣ ጊዜውን ለማስታወስ ምክንያት የሆነልኝንም ነገር እነሆ ከዚህ ቀጥሎ ጠቅሼዋለሁ:: በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በሁዳዴ ጾም ውስጥ ጾመ ድጓ ተቆሞ ሳለ አንድ ቀን ከአዲስ አበባ የመድፍ ድምፅ ተሰማ፣ በዚያ ሰዓት እኔና ጓደኞቼ የሰሙነ ገብር ኄርን[51] ጾመ ድጓ ስንቃኝ እንደ ነበርን አስታውሳለሁ:: የመድፉን ድምፅ ስንሰማ ከቅኔ ማኅሌት ወጣንና ቁልቁል ወደ አዲስ አበባ እንመለከት ጀመር:: ጥቂት ቈይቶም የእንጦጦ ስልከኛ መጥቶ እንዲህ አለ:: "ራስ መኰንን ሐረርጌ ላይ መሞታቸው ተሰማ:: አሁን መድፉ መተኰሱም መርዶው ለጃንሆይ ስለተነገረ ነው" ብሎ ምክንያቱን ገለጸ:: እንግዲህ እኔና ጓደኛዬ ገብረ ኪዳን ወረደ ጾመ ድጓ የጨረስነው ከዚያ በሚቀጥለው በፋሲካው ወራት ነበርና በዚህ ምክንያት ጊዜውን አስታውሰዋለሁ::

---

[49] ለዜማ ትምህርት መግለጫ አባሪ ለ ገጽ 242 ይመልከቱ::

[50] አብሮ የሚማር::

[51] የሁዳዴ ጾም ሳምንታት እያንዳንዳቸው ስም አላቸው:: ስድስተኛው ሳምንት ሰሙነ ገብር ኄር ይባላል::



በዚህ ዘመን (1898 ዓ.ም.) እምዬ በስሙ እኔን ለማየት ከጅሩ መጥታ ሁለት ወር ያህል ከቈየች በኋላ ተመልሳ ሄደች:: እንዲሁ ደግሞ በዚሁ ዘመን አባቴ ሚስታቸውን ወይዘሮ ወለተ እስራኤልን ፈትተው ዓሥር ወር ያህል ብቻቸውን ነበሩ:: ከዚህ በኋላ (ምናልባት በሐምሌ ወር ይመስለኛል) ከእናቴ ጋር ታርቀው እንደገና ባልና ሚስት ሆነው ክረምቱን መክረማቸውንና በተከታዩ ዓመት ላይ መፋታታቸውን አስታውሳለሁ::

### ስለ መሬት መንቀጥቀጥ

በነሐሴ 19 ቀን 1898 ዓ.ም. ቅዳሜ ከእኩለ ቀን በላይ ትልቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ሆነ:: በዚህ ቀን መብረቅና ነጐድጓድ የተቀላቀለበት ዶፍ ዝናም ሲዘንም ዋለ:: በዚያው በዶፉ ዝናም መካከል ኃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ስለተደረገ ሕዝቡ መዓት መጣብን ብሎ ተደናገጠ:: እናቴ በዚያ ቀን ገበያ ለመገበየት ወደ አዲስ አበባ ወርዳ ነበርና በመሬቱ መንቀጥቀጥ ተደናግጣ በቶሎ ወደ እንጦጦ ተመለሰች:: የከተማውም ሕዝብ የገብርኤል ቍጣ ነው እያለ መደናገጡንና መሸበሩን ነገረችን::

እኔ በዚያ ሰዓት የቤታችንን ምሰሶ ተደግፌ ቆሜ የቃል ትምህርት እማር ነበር:: መሬቱ ሲንቀጠቀጥ ምሰሶው ተወዛወዘና ደንግጬ ወደቅሁ:: የቤቱም ጣራ ስለተንጫጫ በተለይ በእንጦጦ ላይ የደረሰ መዓት መስሎን ያለመጠን ፈራን:: በኋላ ግን በአገር ላይ የመጣ ቍጣ መሆኑን ስንሰማ ተጽናናን:: ሕዝቡም ወዲያው "እግዚኦ" እያለ ጸሎቱን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ:: በዚያ ጊዜ ሃይማኖት በሰዎች ልቦናና አስተሳሰብ ቦታው ከፍተኛ ነበረ::

ከጾመ ድጓ ቀጥሎ የቃል ትምህርት ድጓ[52] ቀጠለ:: የቃል ትምህርት ምዕራፍ[53] የሚባለውን ተራ በተራ ቀጥያለሁ:: ምዕራፍ የሚባለው ትምህርት በውስጡ ልዩ ልዩ ክፍሎችን የያዘ ነው:: እነርሱም፤ ዋዜማ ምዕራፍ፣ ስብሐተ ነግህ፣ መወድስ ክስተት አርያም፣ የጾም ምዕራፍ ናቸው:: እነዚህ ሁሉ በድጓ ትምህርት ጊዜ ማታ የሚጠኑ የቃል ትምህርቶች ናቸው:: አንዳንድ ተማሪ ስብሐተ ነግህና መወድስ የተባሉትን ክፍሎች በጾመ ድጓ ትምህርት ጊዜ ሊያጠናቅቃቸው ይችላል:: እኔና ወምበረተኛዬም እንደዚሁ አድርገን ነበር::

---

[52] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዜማ መሠረት የሆነ መጽሐፍ:: መሠረቱ የያሬድ ሲሆን ሊቃውንት ሲቀዱት ሥርዋጽ (እንደ ማስረጃ ሆኖ በነገር መካከል የሚገባ) አስገብተውበታል:: ድጓ በ4ቱ የዓመት ክፍሎች በሐጋይ (በበጋ)፣ በፀደይ (በልግ)፣ በክረምት፣ በመፀው (የመኸር ወራት) ይከፈላል::

[53] በእሑድና በዓበይት በዓላት፣ በዓቢይ ጾም ዘወትርም ከቃል ትምህርት፣ ከአንቀጸ ብርሃን ጋር የሚነገር ጸሎት::

እኔና ወምበረተኛዬ በተከታዩ ዓመት በ1899 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ድጓ ጀመርን፣ በዚህም ጊዜ የአባቴ የራሳቸው መዝገበ ድጓ ስላለ የመጽሐፍ ችግር አላገኘንም። ስለዚህ የወምበር ገፍ ተራ ሳንጠብቅ አባቴ በቀጥታ ያስተምሩን ጀመር። በአንድ ጊዜ ከእርሳቸው ዘንድ የሚዘረጋው ድጓ ሦስት ሲሆን አንዱ የእኛ ድጓ ነበረ። ስለዚህም ድጓውን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ዘለቅነው። የቃል ትምህርቶቹም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ማታ ማታ ተካሄደዋል። ድጓውን አንድ ጊዜ ከዘለቅነው በኋላ መጽሐፉን ለሌሎች ተረኞች ለቀቀንላቸው እኛ በማናቸውም ክፍል በተደራቢነት እንድናዳምጥ ተፈቀደልን። እንዲሁም ሌላውን ልጅ በተወራጅ እናስተምር ጀመር።

## ክህነት ስለመቀበሌ

በእንጦጦ ማርያም ደብር የምንገኘው ሕፃናት ክህነት እንድንቀበል አለቃችን መልአከ ፀሐይ አፈ ወርቅ ስለፈለጉ በ1898 ዓ.ም. በግንቦት ወር ከአንድ መላእክተኛ ጋር ወደ አዲስ አበባ ላኩን። ለዚህ ጉዳይ የተመረጥነው ሕፃናት ሐያ ሁለት ያህል እንደ ነበርን አስታውሳለሁ። አዲስ አበባ ስንደርስ ከአቡነ ማቴዎስ ግቢ በስተሰሜን በኩል ከሚገኝ ከአንድ መኳንንት ቤት አስገብተው አሳደሩን። ቤቱ የምሥጢር ጸሐፊው የቀኛዝማች አፈ ወርቅ መሆኑን በሌላ ጊዜ ሰምቻለሁ።

በማግሥቱ ጧት ወደ ጳጳሱ ግቢ ወሰዱን። እዚያም ስንደርስ ቅስናና ድቁና ለመቀበል ከያገሩ የመጣ ብዙ ሰው አገኘን፣ አቡነ ቀሲስ[54] የሚባሉት የጳጳሱ ሹም ከበር ላይ ሆነው ይጠባበቁ ነበርና ከያገሩ የመጡትን ቅስና ተቀባዮች በአንድ ወገን፣ እንደ እኛ ክህነት የሚቀበሉትን በሁለተኛው ወገን እያደረጉ በሰልፍ ደረደሯቸው። ቀጥሎም ወንጌልና ዳዊት አቅርበው በየደረጃው የንባብ ፈተና እየሰጡ ችሎታቸውን መረመሩ፣ በመጨረሻም ለጳጳስ የሚከፈለውን ገጸ በረከት ከቀሳውስት ሁለት ሁለት ከዲያቆናት አንድ አንድ ብር እየተቀበሉ ወደ ውስጥ አስገቧቸው። እኛ የእንጦጦ ልጆች ግን ይህ ሁሉ አልደረሰብንም። ምክንያቱም በእቴጌ ጣይቱ ቃል አንድ መልእክት ተልኮልን ስለነበረ ነው፣ ስለዚህም አቡነ ቀሲሱ በነፃ አስገብተውን ከሌሎቹ ጋር ቀላቀሉን።

ከዚህ በኋላ አቡነ ማቴዎስ ከመነኰሳት ጋራ መጥተው ከፍ ባለ የቤቱ በረንዳ ላይ ቆሙ፣ ወዲያው በዐረቢኛ ቋንቋ ጸሎት ያደርሱ ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከበረንዳው ወርደው በስተግርጌ ካለው ከደረጃው ላይ ሲቆሙ፣ መጀመሪያ ቅስና ተቀባዮቹ ቀረቡ። ጳጳሱም በእጃቸው እየባረኩና መስቀል እያሳሙ በግምባራቸውም ላይ እያማተቡና "እፍ እፍ" እያሉባቸው አለፉ። ለቀሳውስቱ የተደረገ ሌላም ሥርዓት ነበረ፣ አሁን አላስታውሰውም። ከዚያም

[54] የጳጳስ ጸሐፊ፣ ረዳት አቡነ ቀሲስ ይባላል።



ቀጥሎ ክህነት ተቀባዮች ቀረብን። አቡነም መስቀል እያሳለሙንና እፍ እያሉብን በየተራ አለፉን።

ጳጳሱ በዚህ አኳኋን ቅስናና ድቁና መስጠታቸውን አብቅተው ከተመለሱ በኋላ አቡነ ቀሲስ እኛን ክህነት ተቀባዮቹን በአንድ ላይ ሰብስበው፣ "ከነገ ጀምሮ እስከ አርባ ቀን ድረስ ጾም ጹሙ፣ በየቀኑም አርባ፣ አርባ ስግደት ስገዱ፣ ይህም የክህነት ማዕርግ የእግዚአብሔር ምሥጢር ስለሆነ አክብራችሁ ጠብቁት፣ ባታከብሩትና ባትጠብቁት ግን ትቀሠፉላችሁ" ብለው ተናገሩን።



11 አቡነ ማቴዎስ

ከዚህ በኋላ ከጳጳሱ ግቢ ወጥተን ወደ እንጦጦ ተመለስን። ቤተሰቦቻችን ጎረቤቶቻችን እንኳን ለዚህ ማዕርግ አበቃችሁ እያሉ አሞገሱን። ጾሙንና ስግደቱን ሁላችንም እንደ ትእዛዙ ፈጸምን። አቡነ ቀሲሱ የክህነት ሥልጣን የእግዚአብሔር ምሥጢር ነው ብለው የተናገሩት ቃል ለማንም ሰው እንዳትናገሩ ማለታቸው መሆኑ ስለመሰለን፣ ሁላችንም ምሥጢር አድርገነው ነበር። ነገር ግን በዚህ በኩል በኔ ላይ የደረሰብኝን እንቅፋት እነሆ እገልጻለሁ።

ዘውዱ የሚባል አንድ የወታደር ልጅ ነበረ፣ አገሩ ጉጃም ነው፣ በዕድሜም ከእኔ ከፍ ይላል፣ አባቱ በዳር አገር የሚኖር የደጃች ባልቻ ወታደር ነበረ።

ዘውዱ ግን ከአባቱ ተለይቶ መጥቶ እንጦጦ ላይ በአጎቱ በደብተራ ከንፈር ኃይሉ ዘንድ ሆኖ ከእኛው ጋር ዜማ ይማር ነበር። የዘውዱ ዝንባሌ ከትምህርት ይልቅ ወደ ወታደርነት ስለሆነ በትምህርቱ እምብዛም ነበረ፣ ስለዚህም እኛ ለክህነት ተመርጠን ስንሄድ እርሱ ተለይቶ ቀርቶ ነበርና ክህነት ምን እንደሆነ ለማወቅ ጉጉት አደረበት፣ በየጊዜውም ክህነት እንዴት ያለ ነገር ነው እያለ ይጠይቀን ነበር። አንድ ቀን እኔና እርሱ በሜዳ ላይ ኳስ ስንጫወት ከቆየን በኋላ ወደ ጎድጓዳ ስፍራ ወሰደኝና "ክህነት እንዴት እንደሆነ እባክህ ንገረኝ" ብሎ ለመነኝ። እኔም "ምሥጢር ነው የተናገርህ እንደሆነ ትቀሰፋለህ ብለውኛል አልናገርም" አልሁት፣ እርሱም እየመላለሰ ሲለምነኝ ቆየና እንደማልነግረው በተረዳ ጊዜ በጠብ ዓይን ተመለከተኝ። ቀጥሎም ዱላውን ጎትተና "ዛሬ ካልነገርከኝ እደበድብሃለሁ" ብሎ ክፉኛ አስፈራራኝ፣ እኔም ዱላውን በመፍራት ሁሉንም ዘከዘክሁለት። ከዚያ በኋላ የመቅሠፍቱ ነገር እየታሰበኝ እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ በሕሊናዬ ስጨነቅና ስፈራ ከረምሁ። ዘውዱ ከአንድ ዓመት በኋላ ትምህርቱን ትቶ ወደ ዳር አገር ሄደ፣ እኔም ከዚያ ጊዜ ወዲህ ከቶ አላየሁትም።

## ስለ ሆሳዕና በዓል

የሆሳዕና በዓል እንደ አክሱም ሥርዓት ሆኖ እንጦጦ ላይ ሊከበር የተጀመረው በ1898 ዓ.ም. መጋቢት 30 ቀን ነው። ከአክሱም የመጡ አንድ መምህር ከበዓሉ ቀን ቀደም ብለው የሥነ ሥርዓቱን አፈጻጸም ለካህናቱ ሲያስጠኑ ሰነበቱ። እኛ ን ሕፃናቱንም «ቄሮስ ሜሮስ»[55] የተባለውን መዝሙር እያስጠኑ አስለመዱን። እንግዲህ በበዓል ቀን እንዲህ ሆነ። አንዲቱን የበቅሎ ግልገል በወርቅ ጥልፍ የተጠለፈ ኮርቻ ጭነውባትና በመረሻት አስጊጠዋት ድባብ ተደብቦላትና ሕዝብ አጅቧት ከከንቲባ ወልደ ጻድቅ ቤት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አደባባይ አመጧት። ከንቲባ ወልደ ጻድቅ ለዚህ ለሆሳዕና በዓል ድግስ ለመደገስና የሆሳዕናን በቅሎ ጠብቆ ቀልቦ ለማኖር ዓሥራ ሁለት ጋሻ መሬት የተቀበሉ የደብሩ ትክለኛ ናቸው። እንግዲህ ወደ በዓሉ ታሪክ እመለሳለሁ። ለእኛ ለሕፃናቱ ከነጭ ሐር የተሰፋ ቀሚስ አጠለቁልንና «ቄሮስ ሜሮስ» እያልን እንድንዘምር አደረጉን። በቅሎይቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን እስክትደርስ ድረስ አርእዩነ ፍኖተ[56] የሚለው መዝሙር በየምዕራፉ እየተመራ[57] ወንጌል ይነበብ ነበር። ቃጭልም ይቃጨል ነበር። በቅሎይቱ ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ስትደርስ በስተውጭው ዑደት ተደርጎ የበቅሎዋ ጣጣ አለቀ። ይህ ዓይነት ሥርዓት መፈጸሙም ክርስቶስ

[55] ቄሮስ ሜሮስ ከግሪክ የተወሰደ ቃል ይመስለኛል። ትርጉሙ ምን እንደ ሆነ አልታወቀም ነበር። ምንጭ - መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ* ገጽ 33።

[56] *መንገዱን አሳዩን።*

[57] በታላቅ በዓል ቀን መስቀሉን ተቀብሎ ዜማውን ወይም ቅኔውን ቁጥር ሲቀኝ መሪ ይባላል። ተመሪው ከመሪው የሚሰማውን የሚያዜመው ነው።



በሆሳዕና ቀን በአህያ ግልገል ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሽማግሌዎችና ሕፃናት አጅበውት ነበርና የዚያን ምሳሌ ለመከተል ወይም ለማስታወስ ነው።

ከዚህ በኋላ የመዘምራኑ ሥነ ሥርዓት ተጀመረ። ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት በዐውደ ምሕረቱ[58] ላይ ከመዘምራኑ በስተኋላ ተሰለፉ። መዘምራኑ በድርብና በአብደላከኒ ቀሚስ አጊጠውና ተሰልፈው በስተፊት ቆሙ። የተቀሩት ካህናት ግን በዐውደ ምሕረቱ በምንጣፍ ላይ ተቀመጡ። እንግዲህ መዘምራኑ «ተጽዒኖ ዲበ ዕዋል ኢየሩሳሌም ቦአ በክብር»[59] የሚለውን የያሬድን ዜማ በዝማሜ[60] ስልት እየቀነቀኑና በዝግታ እርምጃ እየተራመዱ መጡ። በየዜማው መጨረሻ መቋሚያቸውን ደቅ እያደረጉና እጅ እየነሡ ቀረቡ። በዐውደ ምሕረቱም የተቀመጡት ካህናት ለመዘምራኑ የዜማ መልስ ይሰጧቸው ነበር።

ከአክሱም የመጣው የሆሳዕና በዓል ሥነ ሥርዓት በዚያ በመጀመሪያው ጊዜ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ባሉበት በዚህ አኳኋን ተከበረ። ሥነ ሥርዓቱ በሸዋ የመጀመሪያ ጊዜና እንግዳ ነገር ስለሆነ ዕፁብ እየተባለ ተደነቀ። በኋላ ግን ሌሎችም አድባራት ይከተሉት ጀመር። ለምሳሌ በአራዳ ጊዮርጊስ ይኸው ሥነ ሥርዓት ገብቶ አይቻለሁ፣ ሆኖም የሥነ ሥርዓቱ ሁኔቴ በዚያ በመጀመሪያው ጊዜ ከነበረው አኳኋን በጣም የተቀነሰና የተጓደለ ነው።

በዘመነ መፀው (በጥቅምት ወር) የእንጦጦ ካህናት እሑድ እሑድ በማኅሌት የሚያደምቁትን ማኅሌተ ጽጌ[61] ለመስማት ጃንሆይና እቴጌ መኳንንቱም ጭምር እንጦጦ እየመጡ ያድሩ ነበር። ማኅሌተ ጽጌ በየሌላውም ደብር የሚፈጸም ነው። ወደ እንጦጦ መውጣታቸውም አዲስ ነገር ለማየት ሳይሆን ስፍራውን ለማክበር ነው። ያ ዘመን «የእንጦጦ ማርያም ወርቃዊ ዘመን» ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል። ደብሩ ከመከበሩ የተነሣ መኳንንት እያንዳንዱን የጽጌ እሑድ እየተካፈሉና ድግስ እየደገሱ ለካህናቱ ግብር ያገቡ ጀመር። በዚያ ዘመን ግብር ጠርተው ታላቅ በዓል ያደረጉትን መኳንንት አስታውሳቸዋለሁ። እነርሱም ራስ ወልደ ጊዮርጊስ፣ ራስ ተሰማ፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፣ ቀኛዝማች ከፈለው፣ አዛዥ ዛማኔል፣ ቀኛዝማች ትእዛዙ ናቸው። እቴጌ ጣይቱ ለእንጦጦ ማርያም ደብር በተደረገው ክብር ከልክ ያለፈ

[58] በቤተ መቅደስ ፊት ለፊት ስብከት የሚሰጥበት ቦታ።

[59] በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ፣ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ።

[60] ዝማሜ ከሰውነትና ከመቋሚያ ውዝዋዜ ጋር እየተቀናጀ የሚዜም የአቋቋም የዜማ ስልት።

[61] ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና አባ ጽጌ ብርሃን የሚባለው ከአይሁድ ሃይማኖት ወደ ክርስትና በአባ ዜና ማርቆስ የተመለሰውና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ አብረው የደረሱት መዝሙር። ምንጭ ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ *የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት።*

ይደሰቱ ነበር። መኳንንቱም ይህን ዓይነት እርምጃ መውሰዳቸው ለጽድቅ ብቻ ሳይሆን እቴጌይቱን ለማስደሰትና ለመወደድ እንደ ነበረ ይሰማኛል።



12 አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን (የመጀመሪያው ሕንፃ)



13 አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን (ከአድዋ ጦርነት በኋላ የተሠራው)

# ምዕራፍ 6

## 1899 ዓመተ ምሕረት

**የማርያምና የራጉኤል የደብር ቦታ ስለመከለሉ፣ ከጃንሆይ እጅ ብር ስለመቀበሌ**

### የማርያምና የራጉኤል የደብር ቦታ ስለመከለሉ

በማርያምና በራጉኤል መካከል ስላለው ቦታ ካህናቱ በወሰን ምክንያት ብዙ ጊዜ ይከራከሩ ነበር። በ1899 ዓ.ም. በጥቅምት ወር ቦታው እንዲከለል ጃንሆይ ስላዘዙ ሊጋባውና አጋፋሪው፣ አፈ ንጉሥ ነሲቡና ሌሎቹም መኳንንት በተገኙበት ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት እንደሚከተለው ሆኖ ተከለለ። የሊቀ ጳጳሱ የአቡነ ማቴዎስ እርዌ ብርት[62] ተይዞ ቀሳውስትና ዲያቆናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀል ተሸክመው ከስፍራው ላይ ተገኙ። ሊጋባውና አጋፋሪዎቹ የቦታውን ወሰን እየረገጡና ምልክት እያስቀመጡ ቀደሙ፤ ካህናቱም ከዚያ ቀጥለው ተከተሉ። አፈ ንጉሥ ነሲቡና ከመኳንንት ታላላቆቹ ከፍ ካለ ከደልዳላ ስፍራ ተቀምጠው የቀረበውን በዓይን፣ የራቀውን በመነጽር ሲመለከቱ ነበር። ለምስክርነት የተመደቡት ሰዎች ግን በወሰኑ ላይ አብረው ተጓዙ። የክልሉ ወሰን የተጀመረው ከጃንሆይ ጉተራ[63] በምሥራቅ በኩል ከሚገኘው ቦታ ላይ ሆነና የራስ ሚካኤልን ቤት ወደ ራጉኤል፣ የከንቲባ ወልደ ጻድቅን ቤት ወደ ማርያም አስቀርቶ በመካከል ላይ አለፈ። ከዚያም ወደ ሰሜን አልፎ ከዘብጡ ደረሰ። ከዚያም የደጃዝማች ለየህን ቤት ወደ ማርያም፣ የጦረኛ ወልደየስን ቤት ወደ ራጉኤል አድርጎ አለፈና ወንዙን ተሻግሮ ወደ ሱሉልታ ከሚያሳየው ከገደሉ አፋፍ ደረሰ። ከዚያም የአፋፉን ጠርዝ ተከትሎ ወደ ጓሳ ታጠፈና ሽንቁሮ ከበሩ ላይ ደርሶ ቆመ። ከዚህ በኋላ የክልሉ ፍጻሜ ሆነና ከላዮቹ አውራውን መንገድ ይዘው ወደ ማርያም ተመለሱ።

በዚህ ጊዜ የተደረገውን አንድ ነገር አስታውሳለሁ። የክልሉ ሥራ ገና ሲጀመር ምስክር የሚሆኑላችሁን ሰዎች አቅርቡ ብለው ሊጋባው ሁለቱን ወገኖች አዘዙ። የራጉኤል ደብር አለቃ በዕድሜና በማዕርግ ከፍ ከፍ ያሉትን የአገር ሽማግሌዎች መርጠው አቀረቡ። የማርያም ደብር አለቃ ግን የተለየ ነገር አደረጉ። ከ8 እስከ 15 ዕድሜ ያላቸውን ሕፃናት አቀረቡና ምስክሮቻችን

[62] በእባብ አምሳል የምትሠራ ጳጳሳት የሚይዟት በትር፣ አመጣጧ ከሙሴ ጋር የተያያዘ ነው፤ ዘጸአት ምዕ. 4 እና 7 እይ።

[63] ከምኒልክ ቤተ መንግሥት በስተ ምሥራቅ አሁን ፈረስ ቤት የሚባለው።

እነዚህ ናቸው አሉ። ሊጋባውም ተደነቁና በምን ምክንያት ነው ብለው ቢጠይቋቸው፣ "እነዚህ ትልልቆቹ ሰዎች ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዕድሜ ውሳኔ ደርሶባቸው በቶሎ ያልፋሉ፤ እነዚህ ሕፃናት ግን ከሽማግሌዎቹ ይልቅ በዕድሜ ይቆያሉ፤ ለማስታወስም ቢሆን የሕፃንነት አእምሮ የበለጠ ያስታውሳልና በዚህ ምክንያት ነው" ብለው መለሱላቸው። ሊጋባውና መኳንንቱም እውነት ነው ብለው አብረው ተጓዙ። እኔም ራሴ ከእነዚህ ሕፃናት አንዱ ነበርሁ። በዚያ ጊዜ የተደረገው የወሰን መስመርና የነገሩ ሁናቴ ሁሉ በእእምሮዬ ስለተቀረጸ እስከ ዛሬ ትዝ ይለኛል።



14 ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን

## ከጃንሆይ እጅ ብር ስለመቀበሌ

ጃንሆይ አጼ ምኒልክ የእጅ ሥራ ሠራተኞችን እንደሚወዱና እንደሚያነቃቁ ሁሉ፣ በትምህርትም ረገድ ተማሪዎችን ማነቃቃት ልማዳቸው ነበር። ለዚህ ማስረጃ የምጠቅሰው ቀጥሎ ያለውን ነው። ዘመኑ 1900 ዓ.ም. ዕለቱ መስከረም 21 ረቡዕ ነው። ጃንሆይና እቴጌ የመስከረም ማርያምን በዓል ለማክበር እንጦጦ መጥተዋል። ማኅሌቱ ደምቆ ካህናቱ ሲያሸበሽቡ ጃንሆይ ከቅድስት ሆነው ይመለከቱ ነበር። በምልጣን[64] ጊዜ እስመ ለዓለም[65] መቃኘት የተለመደ ሥርዓት ነው። በዚህ ቀን የደብሩ አለቃ መልአከ ፀሐይ አፈ ወርቅ

[64] 1ኛ በመሪውና በተመሪው፣ 2ኛ ግራና ቀኝ በሁለት አንሺዎች (ተቀባዮች) የሚዜም መዝሙር።

[65] ከምልጣኑ በፊት በተረኛ መዘምራን የሚቃኝና መላው ካህናት እየተቀባበሉ የሚያዜሙት ዜማ።



እኔና ጓደኛዬ ገብረ ኪዳን ወረደ እንድንቃኝ አዘዙን። በዚያ ጊዜ ሁለታችንም የዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ነበርን። መልአከ ፀሐይ እኛን ትንንሾቹን ማዘዛቸው ጃንሆይ አይተው የደብሩን ትጋትና መነቃቃት እንዲያውቁላቸው ስለተመኙ ይመስለኛል።

እንግዲህ እኛ ወደ ቅኔ ማኅሌት መካከል ገባን። ቁመታችን ገና ትንሽ በመሆኑ በነጋሪት ላይ አቆሙንና እስመ ለዓለሙን በዜማ ቃኘን። ዜማው «ጸሎትክሙ ጽንዕት ሃይማኖትክሙ ርትዕት»[66] የሚለው ነው። በዚህ ጊዜ ጃንሆይ ቀጭን ድምፃችንን በመስማትና በዕድሜያችን ማነስ ተደንቀው፣ "እውነት እነዚህ ልጆች እስከዚህ ድረስ ተምረው ነው ወይ" ብለው መልአከ ፀሐይ አፈ ወርቅን ጠየቁ። እርሳቸውም "አዎን ተምረዋል ሁለቱም ድጓ ዐዋቂዎች ናቸው፣ ሌሎችም ልጆች እንደዚሁ የተማሩ ይገኛሉ"፣ ካሉ በኋላ ስለ ወላጆቻችን ምንያ አንዳንድ ነገር እየጠቀሱ ነገሯቸው። ጃንሆይም በአጠገባቸው ከነበሩት መኳንንት መካከል አጋፋሪ መርድን (በኋላ ደጃዝማች መርድ የተባሉትን) ጠርተው ለእያንዳንዳችን ሁለት ብር እንዲሰጡን አዘዟቸው። አጋፋሪ መርድም ወዲያው ብር ፈላልገው ሰጡንና በደስታ እየፈነደቅን እቤታችን ገባን። እንግዲህ ጃንሆይ ትምህርትን ለማነቃቃት ፈቃድ እንደ ነበራቸው አንድ ማስረጃ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

[66] ጸሎታችሁ የጸናች፤ ሃይማኖታችሁ የቀናች ናት።

# ምዕራፍ 7

## 1900 ዓመተ ምሕረት

ስለ ፈንጣጣ ክትባት፣ ስለ አጼ ምኒልክ መታመም

### ስለ ፈንጣጣ ክትባት

በዚህ ዓመት በበጋው የፈንጣጣ በሽታ እንጦጦ ስለገባ፣ የልጆች አባቶች ተጨንቀው ሁላችንንም አስከተቡን፡፡ የክትባቱም ዘዴ እንደሚከተለው ነበረ፡፡ ከታቢው ሰው የተከታቢውን ግራ ክንድ በትንሽ ቀረባ ምላጭ በጥቶ ያደማዋል፡፡ ወዲያው የሌላውን የፈንጣጣ ቍስል ቀርፎ ጥቂት ማር በነካው የባዘቶ ጥጥ ቍስሉን እያስነካ በተበጣው በተከታቢው ክንድ ላይ እየለጠፈ በጨርቅ ያስርለታል፡፡ እንግዲህ ከሦስት ቀን በኋላ ተከታቢውን ያተኵሰዋል፡፡ ፈንጣጣውም ይወጣለታል፡፡ እኔም በዚሁ ዓይነት ተከትቤ በእግዚአብሔር ቸርነት በቶሎ ተሻለኝ፡፡ ይሁን እንጂ በዚያ ዘመን ብዙ ልጆች በፈንጣጣ እንደ ሞቱ አስታውሳለሁ፡፡ በተለይም ገብረ እግዚአብሔር የተባለ አንድ የትምህርት ጓደኛችን በፈንጣጣ ታሞ ስለሞተ በእኛ በሕፃናቱ ኀዘንና ሥጋት አድሮብን ነበር፡፡

### ስለ አጼ ምኒልክ መታመም

አጼ ምኒልክ ሕመም የጀመራቸው በ1900 ዓ.ም. በነሐሴ ወር ነው፡፡ ለሕመማቸው መነሻ ስለሆነው ነገር ወሬው እየተለዋወጠ ቀርቧል፡፡ እኔ ግን ከሰማኋቸው ወሬዎች ውስጥ ሊታመን የሚገባው መስሎ የታየኝን ብቻ እጽፋለሁ፡፡ ይኸውም ቀጥሎ ያለው ነው፡፡ "በነሐሴ ወር በጾመ ፍልሰታ ውስጥ አንድ ቀን ጧት ጃንሆይ ለጸሎት ወደ ሥዕል ቤት[67] ኪዳነ ምሕረት ሄደው ጸሎት ከአደረሱ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ፡፡ እንቍላል ግንብ አጠገብ ያለው የወለሉ ሜዳ የድንጋይ ደረጃ ተነጥፎበታል፡፡ ጃንሆይ መንገድ ሲሄዱ ፈጠን ፈጠን እያሉ ነውና ከእልፍኛቸው አጠገብ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው የዝናም ውሐ የሸፈነው የድንጋይ ደረጃ አዳለጣቸውና በድንገት ሽብረክ አሉ፡፡ የተከተሏቸውም ሰዎች በቶሎ አንሥተው ከእልፍኝ አስገቧቸው፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ታመው እልፍኝ ዋሉ" ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ ስለ ሕመማቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ የተነገረው ግን እግራቸውን ታመዋል እየተባለ ነበር፡፡

---

[67] ጸሎት ቤት፡፡

# ምዕራፍ 8

## 1901 ዓመተ ምሕረት

ጃንሆይ ስጠበል ወደ ደብረ ሊባኖስ ስለመሄዳቸው፣ ወደ ጅሬ ስለመሄዴ፣ የቅኔ ትምህርት ስለመጀመሬ፣ ምሥጢር ስለማየቴ፣ ወደ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ስለመሄዴ

### ጃንሆይ ለጠበል ወደ ደብረ ሊባኖስ ስለመሄዳቸው

ስለ ጃንሆይ ሕመም የሰማሁትንና በአጋጣሚም እኔ ራሴ ያየሁትን ጭምር ለመግለጽ የታሪኬን መስመር እከታተላለሁ፡፡ እላይ እንደ ጻፍሁት፣ እግራቸውን ስለታመሙ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄደው ጠበል ቢጠመቁ ይሻላል ተብሎ ተመክረና በኅዳር 1 ቀን 1901 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ተነሡ፡፡ ለመጓዣ የተሰናዳው አንድ መኪና ነበረ፡፡ ይኸውም ከፈረንሳይ አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ አውቶሞቢል ነው፡፡ ሾፌሩ መኪናውን ለመፈተሽ እስከ እንጦጦ ድረስ እየነዳ አውጥቶት ነበርና በዚያ ጊዜ እኔ ራሴ መኪናውን አይቼዋለሁ፡፡ የራዲያተሩ ውሐ ቶሎ ቶሎ እየፈላ አስቸግሮ ነበር፡፡ እንጦጦ ላይ ከመንደሩ ውሐ ቶሎ ቶሎ እየተወሰደ ሲጨምሩበት ያየሁትም ትዝ ይለኛል፡፡

ከዚህ በኋላ መኪናው ለጃንሆይ ጕዞ የማይመች መሆኑ ስለተገመተ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ሌላ ዘዴ ይፈለግ ጀመር፡፡ የተገኘውም ዘዴ በባለ አጎበር ጋሪ እንዲሄዱ ማድረግ ነው፡፡ ባለ አጎበሩ ጋሪ ለሰው መቀመጫ ወይም ለመኝታ እንዲስማማ ሆኖ በአናጢዎች ተዘጋጀ፡፡ እርሱም በሁለት ምስንጅር[68] በቅሎዎች ተጭኖ ሊጓዙበት በሚችል ዓይነት ሆኖ ተሠራ፡፡ ከዚህም በኋላ ጃንሆይ በውስጡ ተኝተው ተጓዙበት፡፡ ድካም እንዳይሰማቸውም በቅርብ በቅርቡ ሰፈር እንዲደረግ ተወሰነ፡፡

ስለዚህም በመጀመሪያው ቀን ከአዲስ አበባ ቤተ መንግሥታቸው ተነሥተው እንጦጦ ተራራ ሥር አደሩ፡፡ ይህ ቦታ ዛሬ ቍስቋም የተተከለችበት ቍልልታ ነው፡፡ በሁለተኛው ቀን ከዚያ ተነሥተው እንጦጦ ማርያም አደሩ፡፡ በሦስተኛው ቀን ከእንጦጦ ተነሥተው ሱሉልታ እዘብጡ ላይ በባላባቱ በዋቆ ቱፋ ቤት አጠገብ ሰፈሩ፡፡ በዚህ አኳኋን እየተጓዙ በዓሥር ቀን ያህል ደብረ

---

[68] ምስንጅር የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ ሜሴንጀር ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡፡ ሜሴንጀር ማለትም መልእክተኛ ማለት ነው፡፡ ይህ የበቅሎ ዘር ፖስታና የጦር ዕቃ ለማመላለስ የተመረጠ ነው፡፡ (መ.ኀ.ወ.ቁ.)

ሊባኖስ ደረሱ። በደብረ ሊባኖስ ሦስት ወር ያህል ጠበል ሲጠመቁና ሲጠጡ ሰንብተው በየካቲት ወር ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።



15 አጼ ምኒልክ የመጀመሪያውን አውቶሞቢል ሲገቡኙ

## ወደ ጅሩ ስለመሄዴ

ዕድሜዬ ዓሥር ዓመት ሲሆን፣ በ1901 ዓ.ም. በጥር ወር አባቴ ስለ ቅኔ ትምህርት ወደ ጅሩ ሰደዱኝ። የወሰደኝ ሰው የላምዋሻይቱ አክስቴ የወለተ ማርያም ልጅ መምሬ እንደሻው ነው። በዚያ ጊዜ ጅሩ ላይ በቅኔ ትምህርት የተመሰገነ ዓይነ ስውር አስተማሪ ነበረ። ስሙ አለቃ ወልደ ማርያም ይባላል። ደግሞም አለቃ ጎሩይ ስለሚባል ሁለት ስም ነበረው። የፊተኛው የአገር ቤት ስሙ ሲሆን የኋለኛው የተማሪ ቤት ስሙ ነው። አባቴም ለዚህ አስተማሪ ስለ እኔ ጉዳይ የአደራ ደብዳቤ ጽፈውለታል።

እኔና መምሬ እንደሻው ከእንጦጦ ተነሥተን ተጓዝንና ውልቆ ተክለ ሃይማኖት ከመምሬ ይገዙ ቤት አደርን። በዚያ ወራት የበልግ ዝናም ይዘንም ስለነበረ ሌሊት ክፉኛ መብረቅ ሲበርቅ አደረ። የመብረቁም እሳት አንዱን ትልቅ የኮሶ ዛፍ፣ አቃጥሎት ኖሮ ጧት ቃጠሎውን ተመለከትን። የመብረቅ እሳት ለአጋንንት በሽታ መድኃኒት ነው እያለ ሕዝቡ በየዋህነት ስለሚያምን ከቃጠሎው ላይ እሳት በጭራሮ እየለኮሰ ወደ ቤቱ ለመውሰድ ሁሉም ይሻማ ነበር። ቃጠሎው ከበረደ በኋላም እንኳ ከሰሉን እየቀረፈ ከመውሰድ አልቦዘነም። በዚያ ቀን እዚያው ውልቆ ውሎ አደረግን።



በማግሥቱ ከውልቆ ተነሥተን ጉዞአችንን ቀጠልን። በሦስተኛውም ቀን ጅሩ መስቀለሶስ ከእናቴ ከወይዘሮ የሸዋ ወርቅ ቤት ገባን። እግሬን ጣምኖኝ[69] ክፉኛ ደክሜ ነበርና እስከ ሦስት ቀን ድረስ በቅባት እየታሸሁ ከቤት ተኛሁ። ከዚያ በኋላ ወደ በደበጅ ወርጄ እምዬ በሰሙንና ዘመዶቼን አየሁ። ከልጅነት ጓደኞቼም አብዛኞቹን ስላገኘሁ ስምንት ቀን ያህል በደስታ ሰነበትሁ። የቅርብ ጓደኛዬ የነበረው ሣህሌ እንደብልሃቱ ግን (ገጽ 25) በፈንጣጣ ሞቶ ነበርና ከአባቱ ከደብተራ እንደብልሃቱና ከእናቱ ከእመዬት ዘርጊ ዘንድ ሄጄ ኀዘኔን በልቅሶ ገለጽሁ።

## የቅኔ ትምህርት ስለ መጀመሬ

በሁዳዴ ጾም መጀመሪያ ላይ መምሬ እንደሻው ወደ ጅሑር ወሰደኝና የአባቴን ደብዳቤ ሰጥቶ ከአለቃ ወልደ ማርያም ጋር አገናኘኝ። በዚያ ቀን እኔ ከዚያ ቀርቼ ቅኔ ጀመርሁ፣ መምሬ እንደሻውም ወደ አገሩ ወደ ላምዋሻ ተመለሰ። አለቃ ወልደ ማርያም ወዲያው ዕድሜዬን ጠየቁኝና ዓሥር ዓመት ነው አልኋቸው። ቀጥሎም ስለ ዜማ ትምህርት አንዳንድ ነገር ጠይቀው ፈተኑኝና በዜማ የደረስህበትን ደረጃ ካወቁት በኋላ ሕፃን ብትሆንም በዜማ ስለገፋህ ቅኔው አይከብድብህም፣ ሆኖም ግሡንና ዘይቤውን በቶሎ እንድትለምድ የሚረዳህ ጓደኛ እሰጥሃለሁ ብለው ከኤፍሬም ኃይሌ ጋር አስተዋወቁኝ። ይህ ሰው በዕድሜም ሆነ በቅኔ ትምህርት ደረጃ ከእኔ የቀደመ ነው። አባቱ አለቃ ኃይሌ የአዲስ አበባ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን አለቃ ናቸው። እርሱም በአባቴና በአባቱ በኩል ያለውን ወዳጅነት ያውቅ ኖሮ በደስታ ተቀበለኝና ትምህርቴን ጀመርሁ። በስንቅ ረገድ አልተቸገርሁም ነበር። ምክንያቱም የታላቅ እኅቴ የወይዘሮ መሻገሪያ ቤት በጅሑር አጠገብ ዲላሞ ከተባለ ቦታ ስለሆነና አስፈላጊውን ስንቅ ከዚያ አገኝ ስለነበረ ነው።

በቅኔ ተማሪ ቤት የትምህርቱ አሰጣጥ ሥርዓት እንደሚከተለው ነው። አስተማሪ ማታ ማታ ግሥ ይገሥል[70]። ተማሪዎቹም ግሡን እየተቀበሉ ያጠናሉ። ቀጥሎም አስተማሪ ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ በየደረጃው ቅኔ ያዘርፋል። ተማሪዎች ቅኔውን በቃል ካጠኑ በኋላ አስተማሪው ዘይቤውን እየፈታ ምሥጢሩን ያስረዳቸዋል። ከዚህ በኋላ የጉባኤ ፍጻሜ ይሆንና እያንዳንዱ ተማሪ ከየጎጆው ገብቶ በየትምህርቱ ደረጃ መጠን የተዘረፈውን[71] ቅኔ ሲቀጽል ቈይቶ ይተኛል። በማግሥቱ እስከ እኩለ ቀን ድረስ ትምህርቱን ሲያሰላስልና ማታ በተዘረፈለት አምሳል ቅኔ ሲቈጥር ይውላል። የቈጠረውን ቅኔ ከእኩለ ቀን በኋላ ለአስተማሪው እየነገረ ያሳርማል ወይም ያስመርቃል።

---

[69] የእግሬ ጅማት ተሳስሮ።

[70] ለቅኔ ትምህርት ተጨማሪ መግለጫ አባሪ ለ ገጽ 243 ይመልከቱ።

[71] እዚያው በዚያው ቅኔ ሲቈጥርና ሲያሰማ።

እንግዲህ ተማሪው ቅኔ እስከሚቀኝበት ጊዜ ድረስ በዚሁ አኳኋን ይቀጥላል። ብርቱ ተማሪ ከዓመት በፊት አለዚያም ከዓመት በላይ ሊቀኝ ይችላል። የቅኔ ቤት ሥነ ሥርዓት ደስ የሚያሰኝና የሚመሰገን ነው። በአስተማሪና በተማሪዎች መካከል ያለውም መከባበርና መተሳሰብ እጅግ ብዙ ነው።

ለቅኔ ሰባት የትምህርት ደረጃዎች አሉት። እነርሱም፣ ጉባኤ ቃና፣ ዘአምላኪየ፣ ሚበዝኁ፣ ዋዜማ፣ ሥላሴ፣ ዘይእዜና መወድስ የተባሉ ናቸው። ተማሪ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላው ሊተላለፍ የሚችለው አስተማሪው ችሎታውን አይቶና ፈትኖ ሲፈቅድለት ብቻ ነው። ይህንንም ከዛሬው ዘመን የትምህርት ሥርዓት ጋር ብናስተያየው ይብዛ ይነስ እንጂ ከክፍል ወደ ክፍል እንደ መዘዋወር ዓይነት ነው። ዓይነቱና ሥርዓቱ ይህ ብቻ አይደለም፤ ሌላም ብዙ አለ። እኔም ሥነ ሥርዓቱን ለመጻፍ እችል ነበር። ነገር ግን አሁን የተነሣሁበት ጉዳይ ስላልሆነ እርሱን ትቼ ወደ ታሪኬ መስመር እመለሳለሁ።

ከአለቃ ወልደ ማርያም ዘንድ ቅኔ የቈጠርሁት በዚያ በጾም ወራት ውስጥ ሁለት ወር ያህል ብቻ ነው። ገና ጉባኤ ቃና ላይ ሳለሁ አለቃ ወልደ ማርያም ከአገሩ ካህናት ጋር በነገር ተጋጩና የዘለፋ ቅኔ ጽፈው ትተው ወደ ጐንደር ጠፉ። እኔም ወደ ሌላ ተማሪ ቤት መሄድ ግድ ሆነብኝ።

ስለ አስተማሪውና ስለ ግጭቱ ሁናቴ ጥቂት ቃል እጽፋለሁ። አለቃ ወልደ ማርያም የዚያው አገር የጅሩ ተወላጅ ናቸው። የተወለዱትም አባሌ ሚካኤል ላይ ነው። ቀድሞ በልጅነታቸው ከአባቴ ዘንድ ዜማ በሚገባ ተማሩ (ገጽ 49 ይመልከቱ)። ከአደጉ በኋላም ወደ አማራ አገር ሄደው ቅኔውን ከዋድላና ከበጌምድር፣ አቋቋሙን ከጐንደር ተምረው ጨረሱና ለመምህርነት ተመረቁ። በነዚህም በሁለቱ ሙያዎች ስለተመሰገኑና ስለተወደዱ እዚያው በጌምድር ላይ እያስተማሩ ጥቂት ዓመታት ተቀመጡ። በኋላ ግን ወደ ጅሩ ለመመለስና የአገራቸውን ወጣቶች ለማስተማር ስለፈለጉ በ1900 ዓ.ም. ወደ ጅሩ መጡ። ወዲያው ጅሑር መድኃኔ ዓለም በሚባል ቤተ ክርስቲያን ላይ ተማሪ ቤት አቋቁመው ማስተማር ጀመሩ። ደቀ መዛሙርት ተሰበሰቡላቸው። እኔ ባለሁበት ጊዜ እንኳ ከሠላሳ ያላነሱ ተማሪዎች ነበሯቸው።

ጅሑር መድኃኔ ዓለም በሻለቆች የተተከለ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ደረጃው ከገጠር ነው። ስለዚህም ታላቅ የዓመት በዓል በሆነበት ጊዜ ካልሆነ በቀር በየሳምንቱ እሑድ መወድስ መቆምና ቅኔ መቀኘት ያልተለመደበት ስፍራ ነበረ። አሁን አለቃ ወልደ ማርያም ከመጡ ወዲህ ግን ተማሪዎቻቸውን ይዘው በየሳምንቱ እሑድ መወድስ እየቆሙ ቅኔ ይቀኙ ጀመር። ይኸውም የሚያስወድዳቸውና የሚያስመሰግናቸው መስሎ ይታያቸው ነበር። ነገር ግን እነዚያ የገጠር ካህናት "የመወድስና የቅኔ ግብር ተከለብን" ብለው ጠሉአቸው። እንዲያውም ተሰብስበው ቀርበው "ይህን መወድስና ቅኔ አንፈልግም" ብለው በግልጽ ተቃወሟቸው። እርሳቸውም "የእናንተን ሙያና ግብር (ሳታቱንና ቅዳሴውን) አልነካሁባችሁም። መወድሱንና ቅኔውን የምንመራው እኔና ተማሪዎቼ ብቻ ስንሆን እናንተ ምን አገባችሁ" ብለው በድፍረት ሥራቸውን



ቀጠሉ። ዳሩ ግን ካህናቱ በሌላ መንገድ ልዩ ልዩ ችግርና መሰናክል ፈጠሩባቸው። መወድስ በሚቆሙበት ሌሊት ቤተ ክርስቲያኑን እየዘጉ ጠፉባቸው። በቅዳሴ ጊዜ ክብር ይእቲ እንዳይናገሩና እጣነ ሞገር እንዳይቀኙ በፍጥነት ድርገት እየወረዱና[72] በቃጭል እያደነጋገሩ አስናከሉአቸው። አለቃ ወልደ ማርያምም በዚህ በካህናቱ ድርጊት ተመረሩና አንድ የዘለፋ ቅኔ (መወድስ) በብራና ጽፈው በቅኔ ማኅሌት በር በኩል በግንቡ ልስን ላይ ለጠፉትና ሌሊት ጠፍተው ወደ ጐንደር ሸሹ።

ቅኔው የተቃዋሚዎቻቸውን የያንዳንዱን ስም የሚጠቅስና በግልጽ የሚሳደብ ነው። ሸሽተው ባያመልጡ ኖሮ እነዚያ ቄሶች በዱላ በቀጠቀጥዋቸው ነበር። የዘለፋውንም ቅኔ በዚያው ጊዜ ስለሰማሁትና ስላወቅሁት እነሆ ከዚህ በታች ጽፌ እገልጸዋለሁ።

> ውስተ ደጀ ሰላም ጸርሐ ምስለ አዝማዲሁ፣
> ዘሐመደ መክፈልት ይቀምሕ፣
> የጫንጮ ገበሬ ዕዋል።
> አምጣነ ሐነቀ ስስተ አንበሳ ነዌ ዕዋል።
> ወይትኀሠይ ጊዜ ነጽሮቱ ለመክፈልት ፍየል
> ምስለ አጋጅየለህ ጥምልምል
> አንተ እፀደ ፍቅር ያማስን
> ሀብተ ጊዮርጊስ ቍንጽል።
> ተምዐዐ ጊዜ ድርገት ለነሚተ ቅኔ መርጡል
> ትብትብ መምሬ ብርቄ፣
> ወሀብተ ማርያም ደንጐላጕል፣
> ወደንገጽን ንሕነ እመ አልጸቀ ለሆኩል፣
> ቄስ በግርግታ ወዲያቆን በቃጭል። [73]

[72] ቄሱ ሥጋውን፣ ዲያቆኑ ደሙን ይዘው ቊርባን ለማቊረብ ከመቅደስ ወደ ቅድስት በሚወጡበት ጊዜ ድርገት ወረዱ ይባላል።

[73] ትርጕሙ

> መክፈልት/ዐመድን የሚቅም፣
> የአህያ ውርንጫ/ የጫንጮ ገበሬ፣
> ከዘመዶቹ ጋር በደጀ ሰላም ውስጥ አናፋ፤
> የባለጸጋው ነዌ አንበሳ/ስስት አንቆታልና።
> ፍቅር/ የወይን ቦታን የሚያጠፋ፣
> ቀበሮ/ ሀብተ ጊዮርጊስም
> ከጥምልምል አጋጅየለህ ጋር፣
> መክፈልት/ ፍየልን ባየ ጊዜ ደስ ይለዋል።
> አንተ የፍቅር ቦታን ሀብተ ጊዮርጊስ ቀበሮ ታጠፋለህ
> በድርገት ጊዜም ቅኔ/ አዳራሽን ለማፍረስ
> ተብታባው መምሬ ብርቄ፣
> ከነጭንጫው ሀብተ ማርያም ጋር ተቈጣ።
> እኛም ቄሱ በግርግርታ፣ ዲያቆኑም በቃጭል፣
> በደረሱ ጊዜ ደነገጥን።
>
> ምሥጢሩ
>
> ባለቅኔው፣ ሀብተ ጊዮርጊስ፣ አጋጅየለህ፣ ብርቄና ሀብተ ማርያም ከተባሉ ካህናት ጋር ተጣልተዋል፤ ስለዚህ ሀብተ ጊዮርጊስን በዐመድ ቃሚ የአህያ ውርንጫና በፍየለፊጅ ቀበሮ መስለውታል፤ የጠገበ የአህያ ውርንጫ በጋጥ ውስጥ ሆኖ እንደሚያናፋ ሀብተ ጊዮርጊስም በደጀ ሰላም ውስጥ ስለ ሙታን የሚገባውን ድግስ (ዝክር) በልቶና ጠጥቶ ከሌሎች ጓደኞቹ

ግርጌ ማስታወሻው በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል...



16 ጆሖር መድኃኔ ዓለም

## ምሥጢር ስለማየቴ

እንጦጦ በነበርሁበት ጊዜ የክህነት ጓደኞቼ ምሥጢር እያዩ ወደ ቤተልሔም [74]ሲገቡ እኔን ግን አባቴ ከልክለውኝ ነበር፡፡ የከለከሉበትም ምክንያት ምሥጢር አይቶ ወደ ቤተልሔም የሚገባና የሚቀድስ ልጅ ከትምህርት ይተንጎላል እያሉ ያስቡ ስለነበረ ነው፡፡ እነዚያም ጓደኞቼ ራሳቸውን ለማስከበር እያሰቡ፣ ምሥጢር ያላየ ሰው ከቤተልሔም የገባ እንደሆነ ዘንዶ ይውጠዋል እያሉ ያስፈራሩኝ ነበር፡፡ ቤተልሔሙም በዘንዶና በነብር እንደሚጠበቅ ስላረጋገጡልኝ ቃላቸውን አመንኩና ክፉኛ እፈራ ጀመር፡፡

---

ጋር መንጫጫቱ፣ የአህያ ውርንጫ ዓመድ ሲቅም አንበሳ ሲያንቀው እንደሚችል ሀብተ ጊዮርጊስ መክፈልት ሲፈልግ እንደ ሀብታሙ ነዌ (ሉቃ. 16፣ 18-22) በስስት መያዙ፣ እንደገናም ቀበሮ የወይን ቦታን እንደሚያበላሽ (መኃል. 2፣ 15) ፍየልንም ሲያይ እንደሚደሰት ሀብተ ጊዮርጊስ ከአጋጅየለህ ጋር ፍቅርን ማጥፋቱ፣ ፍየል ያየ ቀበሮ እንደሚደሰት መክፈልት ባየ ጊዜ ደስታ ማድረጉ በቅኔው መጀመሪያ ክፍል ተመሥጥሮአል፡፡ ጠላት በቍጣ ተነሣሥቶ ቤት እንደሚያፈርስ ቅኔ የመናገር ችሎታ የሌላቸው መምሬ ብርቄና ሀብተ ማርያም ቅኔ አፈረሱ ማለት የቅኔ ስንኝ አስተካክለው አለማወቃቸውን፣ በድርገት ጊዜ (በቅዳሴው ፍጻሜ ቀዳሾች በአንድነት በሚወጡበት ጊዜ) ሌላው ቅኔ ሲጀምር ቅኔው ከመፈጸሙ በፊት እየተቈጡ ቃጭል በማቃጨል ግርግር የሚፈጥሩ መሆናቸውን የቅኔው ሁለተኛ ክፍል ይገልጻል፡፡ ምንጭ - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፡፡

[74] ከካህናት በቀር መሃይማን የማይገቡበት የቍርባን ኅብስት የሚዘጋጅበት ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ የሚገኝ ቤት፡፡



በዚህ ዓመት ጅሩ ላይ ሳለሁ አንድ ቀን በዲላሞ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ማኅሌት ቆሜ አድሬ ነበር፡፡ ጧት ብርድ ስለተሰማን አብረውኝ ከነበሩት ካህናት ደብተራ ባንትረሴና አለቃ መዝለቂያ "እስቲ ወደ ቤተልሔም ሄደን እሳት እንሙቅ" ብለው ጋበዙኝ፡፡ እኔ ግን "ዘንዶ ይበላኛልና ወደዚያ አልሄድም" ብዬ በቅን ልቡና ብመልስላቸው "ገና ምሥጢር አላየህም እንዴ" ብለው ጠየቁኝ፣ "አዎን ምሥጢር አላየሁም" ባልኋቸው ጊዜ "ቅኔ እየተማርህ እንዴት ምሥጢር ሳታይ ቀረህ" ብለው ተገረሙብኝ፡፡ ቀጥለውም "ዛሬ ምሥጢር እናሳይሃለን" አሉኝ፡፡ በታየበትም ዕለት ቅዳሴ መቀደስ ሕግና ሥርዓት መሆኑን ከአስገነዘቡኝ በኋላ ወደ ቄሶቹ ሄደው ተመካከሩ፡፡ ቀጥሎም ወደ ቤተልሔም ወሰዱኝና ከደጃፍ ስደርስ «ተፈሥሒ ኦ ቤተልሔም»[75] የሚለውን ውዳሴ ማርያም ድገም አሉኝ፡፡ እኔም እስከ መጨረሻው ደገምሁት፡፡

በዚህ ጊዜ የኔ ሥጋትና ፍርሃት ስለ ዘንዶውና ስለ ነብሩ ብቻ ነበር፡፡ እነርሱም እንደ ሞኝ ቈጥረውኛልና ስለ ዘንዶውና ስለ ነብሩ ምሳሌ እያመጡ ያስፈራሩኝ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ዘንዶና ነብር በቤተልሔም ውስጥ ፈጽሞ አልነበረም፡፡ ከዚህም በኋላ ወደ ውስጥ አስገቡኝና ምሥጢር የሚሉትን ሁሉ አሳይተውኝ ሥጋቴና ፍርሃቴ ተወገደ፡፡ ከዚህም ቀጥሎ በገናንጥላ ያኸንነት ቅዳሴ አስገቡተውኝ ቀድሼ ወጣሁ፡፡ በዘመኔ ሁሉ በድቁና አገልግሎት ከቤተ መቅደስ የገባሁት በዚያ ቀን ብቻ ነው፡፡ የቤተልሔም ምሥጢር ከሃይማኖታዊ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በዚህ ታሪኬ ላይ ስለእርሱ መግለጫ ከመጻፍ በኅጹም እታገሣለሁ፡፡

## ወደ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ስለመሄዴ

ጆሖር መድኃኔ ዓለም ላይ የጀመርሁት ትምህርት እላይ በተጻፈው ምክንያት ስለተቋረጠ በአባቴ ፈቃድና ትእዛዝ ወደ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ሄጄ ዘሣይን ስውሩ ከአለቃ ወልደ አብ ዘንድ ቅኔ ጀመርሁ፡፡ በዚህ ጊዜ እናቴ ወይዘሮ የሽዋ ወርቅ አቶ ይገዙ የተባለ ነፍጠኛና ገበሬ አግብታ ጭራ ወንዝ ላይ ሆናለች፡፡ ስለዚህም ታላቅ እኅቴ ቦጋለች ስንቄን ከጭራ ወንዝ በየሁለት ሳምንት እያመጣችልኝ በብዙ ረዳችኝ፡፡

አለቃ ወልደ አብ ትውልዳቸው ላምዋሻና ቀጠብ ሲሆን ትምህርታቸውም ሠርጸ ክርስቶስ ላይ ከአለቃ ገብረ ተክሌ ነው፡፡ ቅኔ ዐዋቂ ተብለው የተመሰገኑ ናቸው፣ በዜማ ግን እምብዛም ናቸው፡፡ እኔ ከዚያ ስደርስ በዕድሜ ሆነ በትምህርት እኩያዬ የሆነ አንድ ልጅ እንኳ አላገኘሁም፡፡ የነበሩት ተማሪዎች ታላላቆቼና ከኔ በፊት ገብተው የተማሩ ናቸው፡፡ ከእነርሱም አሁን

---

[75] አንቺ ቤተልሔም ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

የማስታውሳቸው የሚከተሉት ናቸው። ብሥራት ኃይሌ የዘቋላ ሰው፣ ወልደ ኪሮስ ገብረ መስቀል የጠራ ሰው፣ አምኃ ጊዮርጊስ የጠራ ሰው፣ ወልደ ቂርቆስ የተጕለት ሰው፣ ወልደየስ አንካሳው የመንዝ ሰው፣ የቀሩትን አሁን ዘንግቻቸዋለሁ። እንግዲህ ከእነዚህ ሰዎች መካከል ከአምኃ ጊዮርጊስ ጋራ ተዋወቅሁና ግሡንና ዘይቤውን በማስቀጸል[76] እየረዳኝ እማር ጀመር። ጉባኤ ቃናውን ጅሑር ላይ አብስዬው ነበርና በቶሎ አስለቅቄ[77] ወደ ዘአምላኪየ ተራመድሁ።

ከዚህ በኋላ የክረምት ወራት ተከተለ። "ሁዳዴና ክረምት ለቅኔ መማሪያ ምቹ ወራት ነው" እየተባለ በልማድ ስለሚነገር ቅኔ ተማሪ በተስፋ የሚጠባበቀው ወራት ነው። እኔ ባለፈው ሁዳዴ ሳልጠቀምበት አልፎ ነበረ። አሁን ግን የክረምቱ ወራት በከንቱ እንዳያልፍብኝ ለትምህርቴ መጣጣር እንደሚገባኝ ዐውቄአለሁ። ስለዚህም በትጋት እማር ጀመር። ሆኖም የልጅነት ጠባይ እያሸነፈኝ ወደ ጨዋታ ማዘንበሌ አልቀረም። ጨዋታውም ጦጣ ማባረርና በየዛፉ ላይ መንጠላጠል ነበር። የሆነ ሆኖ በክረምት ወራት ትምህርቱ እየተብራራልኝ ሄደና በ1902 ዓ.ም. በመስከረምና በጥቅምት ወደ ሚበዝኀና ወደ ዋዜማ ደረጃ ተላለፍሁ። ቀጥሎም በታኅሣሥ መጀመሪያ ላይ ወደ ሥላሴ ደረጃ ተላለፍሁ። በዚህ ጊዜ ከመቼውም ይልቅ ትምህርቱ እየቀናኝ መሄድ ጀምሯል። እርባታዎችንና ግሦችንም ያለችግር መዝለቅ ችያለሁ።

# ምዕራፍ 9

## 1902 ዓመተ ምሕረት

### ወደ እንጦጦ ስለመመለሴ፣ ጅራታም ኮከብ ስለመታየቱ

### ወደ እንጦጦ ስለመመለሴ

በጥር ወር መጨረሻ 1902 ዓ.ም. ወደ ዘይእዜ ደረጃ ተላልፌ ሳለሁ በቶሎ ወደ አዲስ አበባ እንድመለስ ከአባቴ ዘንድ መልእክት መጣልኝ። አባቴ እኔን የጠሩበት ምክንያት መምህር ዐወቀ (ስመ ክርስትናቸው ገብረ ሥላሴ) የተባሉ የዋድላ ሰው እንጦጦ ላይ በቅኔ መምህርነት ተተክለው ማስተማር ጀምረው ነበርና እኔም እዚያው ተምሬ እንድጨርስ ስለፈለጉ ነው።

ከዚህ በኋላ እናቴ ከወር ተረኞች ጋር አገጣጠመችኝና ወደ አዲስ አበባ ተጓዝሁ። ሦስት ቀን ከተጓዝሁ በኋላ እንጦጦ ገባሁ። ወዲያው ወደ መምህር ዐወቀ ወስደው አገናኙኝና ተግቼ እማር ጀመር። አሁን በትምህርት ደረጃ እኩዮቹ የሆኑና ደግሞም የሚበልጡኝ ተማሪዎች አግኝቻለሁ። ከዚህም በላይ አባቴ ስለሚጠብቁኝና ስለሚቆጣጠሩኝ ወደ ጨዋታ እምብዛም አላዘነበልሁም። መምህር ዐወቀ ቅኔውን በሥላሴ ደረጃ አስጀመሩኝና ወዲያው በቶሎ ወደ ዘይእዜ አሳለፉኝ። በዘይእዜ አንድ ወር ያህል ዘገየሁበት። ከዚያም በኋላ ወደ መወድስ አሳልፈውኝ ሁለት ወር ያህል ከቈጠርሁ በኋላ ሰኔ 12 ቀን 1902 ዓ.ም. ዕለተ እሑድ ቅኔ አስቀኙኝ። በዚህ ጊዜ የተሰማኝ ደስታ ከመጠን ያለፈ ነበር።

ተማሪ ቅኔ እንዲቀኝ ሲመረቅለት ሥነ ሥርዓቱ እንዴት እንደሆነ ለማያውቁት አንባቢዎች ልገልጽላቸው እፈልጋለሁ። ተማሪው ከመወድስ ደረጃ ከደረሰ በኋላ አስተማሪው የተማሪውን ችሎታ መዝኖ ሲረዳለት በዚህ ቀን ትቀኛለህና ቅኔህን አሰናዳ ብሎ ይነግረዋል። ቀኑ አንድ በዓል ባለበት ቀን ላይ እንዲሆን ታስቦ ይደረጋል። ምክንያቱም በበዓል ቀን የሆነ እንደሆነ የተማሪውን መመረቅ ብዙ ሕዝብ ሊያይ ይችላልና የምርቃቱ ሥነ ሥርዓት እንዲደምቅ ነው። እንግዲህ ተማሪው ለዚያ ቀን የሚስማማ ክብር ይእቲና እጣነ ሞገር ቈጥሮ ጥሩ ቅኔ ማሰናዳት አለበት። በተባለውም ቀን የቅኔ መቀኛው ሰዓት ሲደርስ ተማሪው በቅኔ ማኅሌቱ መካከል ፊቱን ወደ መቅደሱ አድርጎ እንዲቆም አስተማሪው ያመለክተዋል። ተማሪውም እስከ መሬት ድረስ አጎንብሶ እጅ ነሥቶ ከስፍራው ላይ ይቆምና መጀመሪያ ክብር ይእቲውን በዜማ ይቀኛል። ከዝማሬም በኋላ እጣነ ሞገሩን ለአንድ ተማሪ እየነገረው ተማሪው ያዜመዋል። መሀይምናን በሞኝነት ያን የሚያዜመውን ሰው ባለቅኔ ይሉታል፤ ነገር ግን ተሳስተዋል፤ ቅኔው የእርሱ አይደለምና። ዜማው ሲያልቅ ባለቅኔው እጅ ነሥቶ ወደ ስፍራው ይመለስና ይቆማል። ጸሎቱ ሁሉ

[76] መምህር በሌለበት ከባልንጀራ ጋር ማጥናት።

[77] ማስለቀቅ አጠናቆ ወደሚቀጥለው ትምህርት መሻገር ማለት ነው።

አልቆ «እትው በሰላም»[78] በተባለ ጊዜ የተመረቀው ባለቅኔ ስንክሳር ያነባል:: ከዚያም በኋላ ወደ አስተማሪው ዘንድ ቀርቦ ጫማ ይስማል:: ቀጥሎም ከሽማግሌዎች ጀምሮ እስከ ዝቅተኛ ድረስ ጫማ ይስማል:: እነርሱም ጉንጩን እየሳሙ "እንኳን ለዚህ ያበቃህ፣ እንኳን ደስ ያለህ" እያሉ ይመርቁታል:: ምርቃቱም በዚሁ አኳኋን ይፈጸማል:: በዚያ ቀን ተመራቂው የገንዘብ ችሎታ ያለው ቢሆን በአቅሙ መጠን ግብግብ ያደርጋል:: ድኻ ከሆነም ግብግብ ግዴታ አይደለም፤ አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቹ ገንዘብ አዋጥተው ግብግብ ያደርጉለታል::



17 የቅኔ ትምህርት ቤት በ1900 ዓ.ም. ጎደማ

ተማሪው ተመርቆ ከተቀኘ በኋላ ካህናት በሚሰበሰቡበት ማዕድ ላይ ከቀድሞ የተሻለ የአቀማመጥ ደረጃ ያገኛል:: ይህንኑም አጋፋሪው ወይም ሊቀ ዲያቆኑ እያመዛዘኑ ለእነርሱ እንደመሰላቸው የሚያደርጉት ነው::

[78] በሰላም ወደ ቤታችሁ ሂዱ::



በዚህ ዓመት ከእኔ በፊትና ከእኔ በኋላ የተቀኙት (የተመረቁት) ሰዎች ብዙ ናቸው:: ከእነርሱም አሁን የማስታውሳቸውን በሚከተለው እገልጻለሁ:: መሸሻ ገብረ ማርያም፣ አበበ ወረደ፣ አብነት ዓይነ ስውሩ፣ እንሰ ጸዮን የቡልጋው፣ ገብረ መድኅን አራምዴ ዓይነ ስውሩ የጅሩ ሰው፣ ገብረ ማርያም ወልደ መድኅን የእንጦጦ፣ ገብረ ጻድቅ የእነርእሰ ደብር ምክሩ ወንድም፣ ወርቁ ገብረ ማርያም የእንጦጦ ናቸው::

## ጅራታም ኮከብ ስለመታየቱ



18 በ1902 ዓ.ም. የታየው ጅራታም ኮከብ

በዚሁ ዘመን (1902 ዓ.ም.) ጅራታም ኮከብ[79] ወጥቶ በሰማይ ላይ ታየ:: ኮከቡ ቀንም ሌሊትም እየታየ ጥቂት ቀን ያህል ስለቈየ ሁላችንም በአድናቆት እንመለከተው ነበር:: በመጨረሻም ወደ ምዕራብ ጠልቆ ከዓይን ተሠወረ:: እንዲህ የሆነውም በሚያዝያ ወር ነበር::

[79] በ76 ዓመት አንዴ የሚመጣው ሐሌ (Halley) የሚባለው ኮሜት ነው::

# ምዕራፍ 10

## 1903 ዓመተ ምሕረት

**ከእንጦጦ ስለመጥፋቴ፣ ወደ አዲስ ዓለም ስለመሄዴ፣ ወደ ሰላሌ ስሄድ ስለደረሰብኝ ችግር፣ አሮጌንዳን ስለማየቴ፣ ወደ ጅሩ ስለመሄዴ፣ ወደ እንጦጦ ስለመመለሴ፣ በእንጦጦ ሳለሁ፣ ልጅ ኢያሱ የመድኃኔ ዓለምን ታቦት ስለመትከላቸው**

### ከእንጦጦ ስለመጥፋቴ

ቅኔ ተቀኝቶ የተመረቀ ሰው ወደፊት ለአስተማሪነት እንዲመረቅ የፈለገ እንደሆነ ቅኔውን እያስፋፋና አገባብ እያጠና እስከ ሦስት ዓመት መቀጠል አለበት። ሌላው ግን ቅኔውን ለማስፋፋት ያህል ቅኔ እየቈጠረና አገባብ እየቀጸለ የፈለገውን ያህል በአስተማሪው ዘንድ መቈየት የተለመደ ነው። እኔም ከተቀኘሁ በኋላ ትምህርቴን እንዳላቋርጥ አባቴ ስለአዘዙኝ እዚያው ቈየሁ። የትምህርት ጓደኞቼ አንድ ሙሉ ቤት ብቻ ቅኔ እየቈጠሩ ሲነግሩ እኔ ግን በየቀኑ ሦስት ሙሉ ቤት ቅኔ እንድቈጥርና ለአስተማሪዬ እንድነግር አባቴ ልዩ ትእዛዝ ሰጡኝ። ለመቈጣጠር እንዲመቻቸውም ለአስተማሪዬ የነገርሁትን ሁሉ በየቀኑ ለእርሳቸው እንዳቀርብላቸው አዘዙኝ። ለጨዋታ የሚበቃ ጊዜ ባለመስጠታቸው ምንም እንኳ ብበሳጭ ትእዛዙን ተቀብዬ በመጀመሪያው አራት ወሮች ላይ ፈጸምሁ። በኋላ ግን ሰለቸኝና ትእዛዙን እያጓደልሁ ወደ ጨዋታ እሄድ ጀመር። በዚህ ምክንያት በባለ ቀለበት እግር ብረት አስረው እዚያው እተማሪ ቤቱ አስቀመጡኝ። በዚህ ጊዜ የ12 ዓመት ዕድሜ ሆኛለሁ። ቅኔም ስለተቀኘሁ መጠቃትንና መዋረድን የመጥላት ስሜት በልቤ ውስጥ አድሯል። ሁለት ሳምንት ያህል ታስሬ ከቈየሁ በኋላ እግር ብረቱን ሰብሮ ወደ ሌላ አገር መጥፋት እንደሚሻለኝ በልቤ አሰብሁ። ነገር ግን ወዴት እንደምሄድ ጨነቀኝ። የሆነ ሆኖ የእግር ብረቱን ቀለበት በማጭድ ደንደስ ወዲያና ወዲህ እያልሁ ሳወዛውዘው ጊዜ እየላላ ሄደ። በመጨረሻም ቀለበቱ ተፈለቀቀና እግር ብረቱ ተፈታልኝ። ነገር ግን ወዲያው ፍርሃትና ሥጋት ያዘኝና እግር ብረቱን መልሼ እግሬ ላይ ለማሰር ብፈትን የማይሳካልኝ ሆነ። መፈታቱ እንዳይታወቅ በልብሴ ለመሸፈንና በእስረኛነቴ ለመቀመጥ ተመኝቼ ነበር፣ ነገር ግን አባቴ በድንገት መጥተው ያዩብኝ እንደሆነ የበለጠ ቅጣት እንደሚደርስብኝ አሰብሁ። ስለዚህ እግር ብረቱን እዚያው ወርውሬ በካብ ላይ ዘልዬ ወጣሁና ቁልቁል ወደ አዲስ አበባ ኰበለልሁ። አራዳ ስደርስ ጊዜው መሸ። የምጠጋበት ስፍራ



ስላጣሁ በጊዮርጊስ ዕድሞ[80] ሥር ተጠግቼ በመሸ አዳሪነት ከመጡ መንገደኞች ጋር ብርድ ሲያንቀጠቅጠኝ አደርሁ።

በማግሥቱ ወደ መናገሻ ማርቆስ ብሄድ ይሻለኛል ብዬ ስላሰብሁ የተራራውን ሜዳ እያየሁና መንገደኞችንም እየጠየቅሁ ወደ ምዕራብ ገሠገሥሁ። ምክንያቱም አለቃ ምንደሲል የተባሉ የቅኔ መምህር እዚያ መኖራቸውን ዐውቅ ነበርና ትምህርት ፈላጊ መስዬ ለጊዜው መግቢያ ቦታ እንዳገኝ ነው። እንዳሰብሁትም አስተማሪውን አገኘኋቸውና "ለትምህርት የመጣሁ ነኝ" ብላቸው አንድ ተማሪ ጠርተው "ባልደረባ ሁነው" ብለው አገጣጠሙኝ። እርሱም ወደ ጎጆው ወስዶ አስተናገደኝ። ተማሪው ስለ ትምህርት ቢጠይቀኝ "ገና ጀማሪ ነኝ" አልሁት፣ እርሱም ይህንኑ ለአስተማሪው ነገራቸው። በሌላ ቀን ግን ይህን የተናገርሁትን ቃል ረሳሁትና በተማሪ ቤትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ቅኔ እነጥቅ ጀመር። ቅኔ ማወቄም ስለታወቀብኝ ሌላ ጣጣ ተፈጠረብኝ። "ይህ ልጅ ጀማሪ ነኝ ያለው በውሸት ኖሯል፣ ምን የተንኰል ነገር ቢኖረው ነው" እያሉ በክፋት ሐሳብ ጠረጠሩኝ።

### ወደ አዲስ ዓለም ስለመሄዴ

በመናገሻ ማርቆስ አንድ ወር ከቈየሁ በኋላ እንደገና ጠፍቼ ወደ አዲስ ዓለም ገሠገሥሁ። ወሩ ታኅሣሥ ነው። በመንገድ ሳለሁ ድካምኝና ረሃብ ይዞኝ አለቅስ ነበር። ከዚህም በላይ ወዴት እገባ ይሆን እያልሁ በመጨነቅ ላይ ሳለሁ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና የልጅነት ጓደኛዬን ሥዩም ወልደ አማኑኤልን በሩቅ አየሁት። ከዚህ ልጅ ጋር እንጦጦ ከአባቴ ዘንድ አብረን ዜማ እንማር ነበር። አገሩና ቤቱ አዲስ ዓለም ከተማ ውስጥ ነው። አባቱ አለቃ ወልደ አማኑኤልም የሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ገበዝ ናቸው።


እኔ እንዳየሁት ሁሉ እርሱም አይቶኝ ኖሮ እየሮጠ መጥቶ ሳመኝ ቀጥሎም "ምን እግር ጣለህ" ብሎ ጠየቀኝ። እያለቀስሁ ሳምሁትና ታሪኬን ሁሉ ዘረዘርሁለት። አባቴ ቅጣት እንደሚያጸኑብኝ ድሮ ያውቅ ነበርና የነገርሁትን ሁሉ አምኖ ተቀበለው። ከዚያ በኋላም "አይዞህ ወደ እኔ ቤት ሄደህ ትቀመጣለህ፣ ከአባቴ ጋር አስተዋውቅሃለሁ፣ ወደፊት ስለሚሆነውም ነገር እናስብበታለን" ብሎ አጽናናኝና ወደ ቤቱ ወሰደኝ። ከአባቱና ከዘመዶቹ ጋር አስተዋወቀኝና ደስ ብሎኝ ተቀመጥሁ። የልደትን በዓል የዋልሁትም ከዚያው ነው። ሥዩም የዋለልኝን ውለታ ምን ጊዜም አልረሳውም።

ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ ዓለም ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወጥቼ ስጠያይቅ የአባቴ ደቀ መዛሙርትና ወዳጆች የሆኑ ሰዎችን አገኘሁ። እነርሱም ደብተራ ክፍሌ፣ ደብተራ ወልደ ሚካኤልና ልጃቸው ዮናስ፣ ደብተራ ኃይለ ሚካኤል፣

---

[80] በኖራ ወይንም በጭቃ የተገነባ የቤተ ክርስቲያን አጥር።

ደብተራ እሸቴ ናቸው፣ ቀጥሎም አለቃ ተጠምቆ የተባሉ ትልቅ የቅኔ መምህር እዚያው አገር መኖራቸውን ሰማሁ:: አለቃ ተጠምቆ ቅኔና ብሉይ መጽሐፍ የሚያስተምሩ ዓይነ ስውር ናቸው:: ቀድሞም ሰምቼ ነበርና ደስ ብሎኝ ተገናኘኋቸው:: የአመጣጤን ነገርና የትምህርት ደረጃዬን ገልጬ ከነገርኋቸው በኋላ ከእርስዎ ዘንድ ቅኔ ለማስፋፋት እፈልጋለሁ አልኋቸው:: እርሳቸውም ከተማሪዎቻቸው መካከል አንዱን ዓይነ ስውር ባልደረባ አደረጉልኝ:: ይህ ሰው ርኅሩኅና ደግ ነው:: በጎጆው ውስጥ በአንድ ቆጥ ላይ አብረን እንተኛ ነበር:: አለቃ ተጠምቆ ለመዱኝና እየመራኋቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን እወስዳቸው ጀመር:: ባልደረባዬንም አንዳንድ ጊዜ እየመራሁት ወደሚፈልገው ቦታ አደርሰው ነበር::



19 አዲስ ዓለም ማርያም

አለቃ ተጠምቆ ማታ ማታ ቅኔ ይዘርፉልኝ ጀመር:: በሌላም ጊዜ አገባብ እንዳጠና አደረጉኝ:: ካህናቱ አሁን ለምደውኛል:: እኔም በማኅሌት ጊዜ ቅኔ ለመመራት ወይም ለመቀኘት ዜማ ለመቃኘትና ይህን የመሳሰለውን አገልግሎት ለመፈጸም ትጋትና ችሎታ አሳየሁ:: ከዚህ የተነሣ አንዳንዶቹ ሰዎች ወደ ቤታቸው እየወሰዱ እኔን ምሳ እስከ መጋበዝ ደረሱ:: እንዲህ ያደረጉልኝ ሰዎች የደብሩ አስተዳዳሪ አለቃ ዓምደ ሚካኤል፣ ዜማ አስተማሪው አለቃ ቴዎድሮስ፣ የተድባበ ማርያሙ በትረያሬክ ናቸው:: የአለቃ ዓምደ ሚካኤል ልጆች ሞገስና በጸሎት በዕድሜ እኩዮቼ ስለሆኑ በቶሎ ተለማምደናል::



አዲስ ዓለም ላይ በነበርሁበት ጊዜ በኑሮዬ ችግር አልደረሰብኝም፣ ነገር ግን የአባቴ ወዳጆች በብዛት ስለተገኙና ስላወቁኝ ምናልባት ይልኩባቸውና መጥተው ይይዙኛል ብዬ ሠጋሁ:: ስለዚህም የጥምቀትን በዓል ውዬ ወደ ሌላ አገር ለመሄድ ተመኘሁ:: ነገሩን ከመረመርሁት በኋላ ጅሩ ከእምዬ በሰሙ ዘንድ መሄድ እንደሚሻለኝ አሰብሁ:: ወደ ጅሩ ለመሄድ የሚቻለውም በሰላሌ፣ በደብረ ሊባኖስና በደነባ በኩል መሆኑን ከሰዎች ጠይቄ ተረዳሁ:: ርቀቱ ከአዲስ ዓለም እስከ ደብረ ሊባኖስ የሦስት ቀን ጉዞ ሲሆን ከዚያም እስከ ጅሩ የሁለት ቀን ጉዞ መሆኑንም ለማወቅ ቻልሁ፣ ነገር ግን በሙገር ቈላ ውስጥ ወስላቶች ብቸኛ የሆነውን ሰው እየደበደቡ ልብሱን እንደሚገፉት ሰማሁና በዚህ ረገድ ብቻ ፍርሃት ያዘኝ::

ከጥምቀት በዓል በኋላ ከሰላሌ የመጡ ካህናት በቤተ ክርስቲያኑ ገረገራ[81] ውስጥ ሰፍረው አየሁና ቀርቤ ባነጋግራቸው ታቦት ረክሶባቸው ለማስባረክ የመጡ መሆናቸውን ነገሩኝ:: ሊቀ ጳጳሳቱን የሚጠብቁ መሆናቸውንም ገለጹልኝ::

ስለ ታቦት መባረክ ጥቂት ሐተታ እሰጣለሁ:: በዚያ ዘመን ቀሳውስት ወይም ዲያቆናት በዝሙት ምክንያት ከሥልጣን ሲሰናከሉ ታቦት ረከሰ ይባል ነበር:: ምክንያቱም እነርሱ ሊቀድሱበት እጃቸው የዳሰሰውና የነካው በመሆኑ ነው:: በዚህ ዓይነት ረክሷል የተባለውን ታቦት ሌሎች ቀሳውስት ወደ ጳጳስ አምጥተው ያስባርኩታል:: በዚህም ጊዜ ለማስባረኪያ ሁለት ብር ለጳጳሱ ይከፍላሉ:: ይህ ልማድና ሥርዓት በዚያ ጊዜ ገና እንደጸና ነበር:: በኋላ ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሥልጣን በያዙበት ጊዜ ልማዱ ተነቀፈና ወደ ጳጳስ ማምጣት ቀርቶ በዚያው አገር የሚገኝ ቆሞስ እንዲባርከው ተደርጓል::

እንግዲህ ወደ ታሪኬ እመለሳለሁ:: እነዚያ ካህናት ወደ ሰላሌ በሚመለሱበት ጊዜ አብሬአቸው ለመሄድ እንዲፈቅዱልኝ ለመንኋቸው:: የምሄደውም ወደ ደብረ ሊባኖስ መሆኑን ከነገርኋቸው በኋላ እሺ ብለው ልመናዬን ተቀበሉት:: ስለዚህም እነርሱ ወደ ሰላሌ የሚመለሱበትን ቀን እጠባበቅ ጀመር::

በዚህ ዘመን የአስተርእዮ ማርያም በዓል እሑድ ቀን ነበረ:: በዓሉንም ለማክበር ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ማቴዎስ፣ እንዲሁም ራስ ቢትወደድ ተሰማ ከራስ ወሌ ጋር ገና በዋዜማው መጡ:: እሑድ ከሌሊቱ በ5 ሰዓት ተደውሎ ማኅሌት ተጀመረ:: ማኅሌቱም ደምቆ አደረ:: አዲስ ዓለም ስድስት መቶ ተክለኞች ካህናት ያሉባት ታላቅ ደብር ናት:: አጤ ምኒልክም ርእሰ አድባራት የሚል የማዕርግ ስም ሰጥተዋታል:: ሊቃውንቱ ባለ ግርማ ናቸው:: የመዘምራኑ ውበት ምሳሌ የሌለው ነው:: እነ ደብተራ ተክለ ማርያም፣ እነ

[81] የገጠር ቤተ ክርስቲያን አጥር::

ደብተራ ጐላ፣ እነ ደብተራ ክፍሌ፣ እነ ደብተራ ሐዋዝ ወረብ ሲወርቡና ሲያሸበሽቡ ክንፍ ያበቀሉ ይመስላሉ። አለቃ ዓምደ ሚካኤል የውብት መደምደሚያ ናቸው። በዚቅ አወራረድና ጸናጽል፣ መቋሚያ ይዘው በመወዛወዝ ከቶ መሰል አልነበራቸውም። የቤተ ክርስቲያኑም ሕንፃ ልዩ መልክና ልዩ ቅርጽ ያለው ነው። ቅኔ ማኅሌቱ ሰፊ አዳራሽ ይመስላል። በርሱ ላይ መዘምራኑ ከሁለት ተከፍለው ሲዘምሩ ደስ ያሰኙ ነበር።

ጧት በቅዳሴ ጊዜ ራስ ቢትወደድ ተሰማና ራስ ወሌ መጥተው አስቀደሱ። ራስ ወሌን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋቸው በዚያ ቀን ነው። ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ታቦት ወጥቶ ዑደት ተደረገ። ቀጥሎም አቡነ ማቴዎስ ቡራኬ ሰጥተው ታቦቱ ከገባ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ። አቡነ ማቴዎስ ግን እነዚያን ረክሱ የተባሉትን ታቦቶች ለመባረክ እንደ ገና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገቡ።

በወሬ እንደሰማሁት በዚህ ቀን ራስ ቢትወደድ ተሰማና ራስ ወሌ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ሥጋ ወደሙን ተቀብለው ቈረቡ ተባለ። የቈረቡበትም ምክንያት ሁለቱ ራሶች ወደፊት እንዳይከዳዱ ቃል ኪዳናቸውን በቍርባንና በመሐላ ለማጽናት ነው ተብሎ በሰፊው ተወራ።

## ወደ ሰላሌ ስሄድ ስለደረሰብኝ ችግር

እነዚያ የሰላሌ ካህናት ያስባረኩትን ታቦት ይዘው በጥር 25 ቀን 1903 ዓ.ም. ኀሙስ ከአዲስ ዓለም እንደሚነሡ ነገሩኝ። እኔም በዚያ ቀን ጧት በማለዳ ወደእነርሱ ሄድሁና አብረን እንጓዝ ጀመር። አስተማሪዬን አለቃ ተጠምቆንና በደግነት ያስተናገደኝን ያን ዓይነ ስውር "ደኅና ሁኑ" ሳልላቸው በመሄዴ ብቻ ሕሊናዬ ሲወቅሰኝ ዋለ። ጧት ለሽንት ወደ ጓሮ እንደምዞር በማስመሰል ከቤት ወጣሁና በዚያው እንደወጣሁ ቀረሁ። የኔ ሐሳብ አትሄድም ብለው እንዳያስቀሩኝ በመፍራት ነበር። እነዚያ ወዳጆቼ ግን "ከቶ ምን ሆኖ ይሆን" እያሉ ምናልባት ሳይጨነቁ አልቀሩም ይሆናል።

በዚያ ቀን ስንጓዝ ውለን በሙገር ቈላ አፋፍ አጠገብ ፋሌ ኪዳነ ምሕረት ከምትባል ከአንዲት ገጠር ቤተ ክርስቲያን ደረስን። ቤተ ክርስቲያኒቱ በታላላቅ አፀዶች የተከበበችና በጉብታ ላይ የተሠራች ናት። በዙሪያዋ መንደር ስለሌለ እዚያው እቤተ ክርስቲያኑ ስብሳብ ሰፍረን አደርን። በማግሥቱ ጥር 26 ዓርብ በማለዳ ተነሥተን የሙገርን ወንዝ ተሻግረን የሰላሌን ዳገት ጀመርን። የፀሐዩ ሙቀትና የረሞጫው[82] ግለት አንገፍግፎኝ ነበር። የታችኛውን ዳገት ወጥተን ከላይኛው ቀጣና ስንደርስ ጤፍ ሲያስወቃ የዋለ አንድ ከበርቴ ገበሬ ድግስ አዘጋጅቶ በዘጠኝ ሰዓት ገበሬዎቹን ሲጋብዝ አገኘነው። ታቦቱን ባየ ጊዜ ቀረብ

[82] በፀሐይ ነበልባል የተቃጠለ አሸዋ።




ብሎ ተሳለመና "እባካችሁ ምሳ ተጋበዙልኝ" ብሎ ለመነን። ቄሶቹ "ይመሽብናል እንሄዳለን" ብለው ተግደረደሩ። እርሱ ግን መሬት እየሳመ "እህል በረከት እንዲወርድበት አትለፉኝ ተጋበዙልኝ" እያለ አጥብቆ ለመነ። ከዚያ በኋላ በዛፍ ጥላ ሥር ዐረፍንና እስከሚበቃን በልተን ተነሣን። ወዲያው ዳገቱን ጨርሰን ከሰላሌ ሜዳ ደረስንና እስከ ማታ ተጕዘን በውድቅት ከአንድ ደግ ሰው ቤት ገብተን አደርን። ሰውዬው የካህናቱ ወዳጅ የሆነ የጉለሌ ሥላሴ ቄስ ገበዝ መሆኑን ሰምቻለሁ። እጅግ አክብሮ አስተናገደን።

በማግሥቱ ጥር 27 ቀን ቅዳሜ ሰውዬው ቁርስ አቅርቦ ጋበዘን። ቀጥሎም እስከ አውራው መንገድ ድረስ ሸኝቶን ተመለሰ። እኛም እስከ ረፋድ ድረስ ከተጓዝን በኋላ ከአንድ መንታ መንገድ ላይ ደረስን። በዚህ ጊዜ እነዚያ ቀሳውስት "እንግዲህ የኛ መንገድ በዚህ በኩል ነው" ብለውኝ ወደ ግራ በኩል ሲገነጠሉ ለእኔም "የደብረ ሊባኖስ መንገድ ይህ ነው" ብለው አሳዩኝና ተለያየን።

ከዚህ በኋላ ብቻዬን ሆኜ በዚያ በማላውቀው አገርና መንገድ እኳትን ጀመር። ጊዜው እየመሸ ሄደ። ፀሐይ ጠልቃ ጨለማው ስለመጣ ማደሪያ ለማግኘት እፈልግ ጀመር። ከወደፊቴ አንድ ቤተ ክርስቲያን አየሁና ወደዚያ ገሠገሥሁ። ይህች ቤተ ክርስቲያን እለተ ማርያም ናት። አሁን ጨለማ ሆኗል። ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ውስጥ ገብቼ ቆሜ ሳለሁ ከሁለት መቃብር ቤቶች መካከል አንድ ሰው ብቅ አለና "አንተ ማነህ" ብሎ ጠየቀኝ። እኔም "ማደሪያ ያጣሁ መንገደኛ ነኝ" አልሁት። ሰውዬው የዕቃ ቤት ጠባቂ ኖሯል፣ "እዚህ ሰው አያድርም በምኒልክ አምላክ ወግድ" ብሎ ተቈጣ። እኔም "መንገደኛ ነኝና እባክዎ በአጠገብዎ ተጠግቼ ልደር፣ ደግሞ እኔም ካህን ነኝ፣ አባቴም አስተማሪ ናቸው" አልሁና ምናልባት ስማቸውን ሳይሰማ አይቀርም በማለት ስማቸውን ጠቅሼ ነገርሁት። እርሱም ስማቸውን ያውቅ ኖሮ የአለቃ ወልደ ቂርቆስ ልጅ በዚህ ሰዓት እዚህ ምን አመጣው ብሎ ተጠራጠረ። ሆኖም እያለቀስሁ ልመና ስላበዛሁበት ሌባ በመፍራት እኔ ዘንድ ሰው ማደር ክልክል ነው። ወደ ዕቃ ቤቱ ሳትጠጋ እዚያ ዛፍ ሥር ተጠግተህ እደር አለኝና ሄጄ ተቀመጥሁ። ጨለማውና ብርዱ ከባድ ነበር። እስከ ዶሮ ጩኸት ድረስ እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም። ነፋስ የዛፉን ቅጠል ባንኰሻኰሸው ቍጥር ጅብ ሊበላኝ ወይም ጋኔን ሊያንቀኝ የመጣ እየመሰለኝ እፈራ ነበር። ዶሮ ሲጮህ ዲያቆን መጥቶ ደወል ደወለና ካህናቱ ለጸሎት ተሰበሰቡ፣ በዚህ ጊዜ ብቻ እንቅልፍ ጥቂት አሸለበኝ።

ጧት ጎሕ ሲቀድ ያን ርጉም ስፍራ ትቼ ወጣሁና ወደ ደብረ ሊባኖስ አቅጣጫ ስመለከት አንዲት ቀጭን መንገድ አገኘሁና እርሷን ይዤ እሄድ ጀመር። ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል እንደተጓዝሁ በቀጥታ ሸንኩርት ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አደረሰችኝ። እኔም ቤተ ክርስቲያኑን ገና ሳየው በምሕረት ሊቀበለኝ እንደሚጠብቀኝ ዓይነት ተሰማኝ። ወዲያው ተሳለምሁና ከቅኔ ማኅሌቱ ገብቼ ቆምሁ። ቅዳሴ ጉብተው እጋምሰውት ነበር። ራስ ዳርጌ የተከሉት ትልቅ ደብር ስለሆነ ደብተሮቹ እሑድ እሑድ መወድስ ይቆሙበታል፣ ቅኔ ይቀኙበታል።

በቅዳሴው መጨረሻ ላይ ባለተራው ደብተራ ክብር ይእቲ ቅኔ ተቀኘ። ክብር ይእቲው ሲዘመም እኔም አብሬ በመዝመም ሞያዬን ለማሳወቅ ተጣጣርሁ። ምክንያቱም ዜማና ቅኔ የተማርሁ ሰው መሆኔን አይተው እንዲያስጠጉኝ ስለተመኘሁ ነው። ከዚያ ቀጥሎ ዝማሬ ተቃኝቶ ሲዘመም እኔም እንደዚያው አደረግሁ። ካህናቱም ከየት አገር የመጣ ደብተራ ነው እያሉ በዓይናቸው እየሠረቁ ያዩኝ ነበር። ከዚህ በኋላ እጣነ ሞገር ለመመራት ደብተሮች ሲገባበዙ አየሁና እኔ ተሽቀዳድሜ "ሃሌ ሉያ" ብዬ ወደ ባለ ቅኔው ቀረብሁ። ቅኔውንም ተመርቼ ስጨርስ ወደ ነበርሁበት ተመለስሁና በዝማሜውና በመረግዱ[83] አለሁ አለሁ አልሁበት። እንግዲህ ሙያዬን ለማሳወቅ የሚበቃኝን ያህል ደክሜአለሁ። ካህናቱም ሳያደንቁልኝ የቀሩ አይመስለኝም።




2 ሸዋ

እጣነ ሞገር ካለቀ በኋላ እነርሱ ወደ ደጀ ሰላም[84] ሲገቡ እኔንም ጋበዙኝ። ጌራ ወርቅ የተባለ የዚያው አገር ልጅ (በዕድሜ እኩያዬ የሆነ) ቀረብ ብሎ ያነጋግረኝ ጀመር። ወዲያው ተለማመድንና ችግሬን አዋየው ጀመር። እርሱም "አሁን ወደ ደብረ ሊባኖስ ከምትሄድ ይልቅ እዚሁ አገር ከቅኔ ተማሪ ቤት ገብተህ ብትቈይና አገሩን ከለመድህ በኋላ ብትሄድ ይሻላል" ብሎ መከረኝ።

[83] በከበሮና በጸናጽል ተሸኝተው የሚዜሙ ዜማዎች።

[84] በቤተ ክርስቲያን በስተምዕራብ የሚገኝ መዳረሻ፣ መሳለሚያ።



ምክሩን ስለተቀበልሁት ወደ ተማሪ ቤት ወስዶ ከተማሪዎች ጋር አገናኘኝ። ባልደረቦች እንዲሆኑኝም አደራ አለልኝ። በዚያ ስፍራ አለቃ ዮሐንስ የተባሉ ቅኔ አስተማሪ ነበሩበት። እሳቸው ከአንድ ወር በፊት ሞተው ስለነበረ አሁን በእርሳቸው ስፍራ የተተካ ኃይለ ሚካኤል የተባለ ደቀ መዝሙራቸው ነው። እርሱም ለግል ጉዳይ ወደ አንድ አገር ስለሄደ በዚያ ጊዜ አልነበረም። የእኔም ፍላጎት ለጊዜው መጠጊያ ቦታ ለማግኘት ስለነበረ አሁን ምኞቴ ተፈጽሞልኛል። በዚህ ስፍራ የቈየሁትም ሁለት ሳምንት ያህል ብቻ ነው።

## እሮገንዳን ስለማየቴ

ከዚህ በኋላ አሮገንዳ የተባለው አገር ወዴት ነው ብዬ ብጠይቅ ከሸንኩርት ሚካኤል ሥር በቈላው ውስጥ መሆኑን ነገሩኝ፣ ስፍራውንና መንገዱንም አሳዩኝ። አባቴ ከሌላ ሴት የወለዷት የታናሽ እኅቴ የፈትለ ወርቅ የእናትዋ አገር አሮገንዳ መሆኑን ገና ድሮ ዐውቅ ነበር። እናቷ አመለ ወርቅና አያትዋ መምሬ አባዬ ዘመዶቿም ሁሉ እዚያው እንደሚገኙ ገና ድሮ ሰምቻለሁ። ስለዚህም እነሱን ለመጐብኘትና ወደ ሃገሬ ወደ ጅሩ እንዲሸኙኝ ለመጠየቅ በልቤ ሳስብ ቈየሁ። አንድ ቀን በአሳቤ ቈረጥሁና (ጓደኞቼን እንኳ ደኅና ዋሉ ሳልል) ቁልቁለቱን በስርጥ መንገድ ወርጄ አሮገንዳ ደረስሁ። ይህ አገር ውሐ በቦይ የሚገባበትና ብዙ አታክልት የበቀለበት ለም ስፍራ ነው። የፈትለ ወርቅ አያት መምሬ አባዬ በአትክልታቸው ውስጥ ሆነው ሽማ ይሠሩ ነበር። እኔም በዚያ በኩል ሳልፍ አየኋቸውና ተራ ሽማኔ መስለውኝ "እባክዎ የመምሬ አባዬን ቤት ያሳዩኝ" ብዬ ለመንኋቸው። ቀና ብለው አዩኝና "ከየት ነው የመጣኸው" አሉኝ። "ከእንጦጦ ነው" ብዬ መለስሁላቸው። እሳቸውም "አንተ ማነህ የማን ልጅ ነህ?" ብለው ጠየቁኝ። "የአለቃ ወልደ ቂርቆስ ልጅ ነኝ ስሜ መርስዔ ኀዘን ነው" ካልኋቸው በኋላ ከዚያው አያይዤ "እዚህ አገር የእኅቴ የፈትለ ወርቅ እናትና አያትዋ ስላሉ እነርሱን ለማግኘት ነው የመጣሁት" አልኳቸው። በዚህ ጊዜ ሥራቸውን ተወት አድርገው ተነሡና እጄን ይዘው ወደ ቤታቸው ወሰዱኝ። ቀጥሎም "የፈትለ ወርቅ ወንድም ይኸው መጥላችሁ" ብለው ለልጃቸው ለአመለ ወርቅና ለሚስታቸው ለእመዬት ወለተ ኢየሱስ ነገሯቸው። እነርሱም ጉንጬን እየሳሙ "እንደምን ሰንብተሃል" ይሉኝ ጀመር።

እህል፣ ውሐ ሰጥተውኝ ጥቂት ካረፍሁ በኋላ "ኧረ ለመሆኑ ምን እግር ጣለህ" ብለው ጠየቁኝ። ከዚያ በፊት በስም ብቻ እንጂ በመልክ አንተዋወቅም ነበር። እኔም ለጥያቄው መልስ አባቴ ድብደባና እስራት ስላጸኑብኝ እግር ብረት ሰብሬና ኮብልዬ መምጣቴን፣ አሁንም መንገደኛ ፈልጌ ወደ ጅሩ ወደ እምዬ በሰሙ ለመሄድ ማሰቤንና በመንገድ ላይ የደረሰብኝን ችግር ሁሉ ምንም ሳላስቀር ነገርኋቸው። ይህን በሰሙ ጊዜ የበለጠ አዘኑልኝና ደኅና አድርገው አስተናገዱኝ። ፈትለ ወርቅ በዚህ ጊዜ ያለችው ጅሩ እምዬ በሰሙ ዘንድ ነው። የእርስዋ ናፍቆት በልባቸው ውስጥ ስለነበረ እንደ እርስዋ አድርገው ተመለከቱኝ። ስሜን በመጥራት ፈንታም የፈትለ ወርቅ ወንድም እያሉ

ይጠሩኝ ነበር። ቤተሰቡም ያደረገልኝ ፍቅር ከቶ የማይረሳ ነው። አመለ ወርቅ በዚያ ጊዜ አቶ በየነ የተባለ ገበሬ አግብታ ታፈሰ የተባለውን ልጅዋን ወልዳለች። የቤተሰቡም መኖሪያ በዚያው በአንድ መንደር ወስጥ የተሰበሰበ ነው። ታፈሰ በዚያ ጊዜ የሦስት ዓመት ልጅ ነበረ። እኔም ያን ሁሉ ችግር አሳልፎ እዚህ ስላደረሰኝ እግዚአብሔርን አመሰገንሁት።

## ወደ ጅሩ ስለመሄዴ

በአርገንዳ ሦስት ሳምንታት ቈየሁ። ከዚያ በኋላም መምሬ አባዬ በጅሩ በኩል ወደ ወረይሉ የሚሄዱ ነጋዴዎች ፈልገው አገጣጠሙኝና ከእነርሱ ጋር ወደ ጅሩ ተጓዝሁ። በመጀመሪያው ቀን ከጉረኔ ተነሥተን ወበራ ላይ አደርን። በሁለተኛው ቀን ጅሩ ደረስንና ኩሳዬ ላይ ሰፈር ስላደረጉ እኔም እዚያው አብሬ አደርሁ። በማግሥቱ ነጋዴዎቹ ጉዞአቸውን ወደ ደቡብ ሲቀጥሉ እኔ ተነጥዬ ወደ በደበጅ መግደላዊት ወረድሁ። እምዬ በሰሙና ፊትለ ወርቅ ገና ሲያዩኝ በናፍቆት እያለቀሱ ተቀበሉኝ። ይልቁንም የአመጣጡን ሁናቴ ስዘረዝርላቸው በጣም አዘኑልኝ። ከዚያ በኋላ ወደ እምቧጮና ወደ ገና መምቻ እየሄድሁ የልጅነት ጓደኞቼንና ሽማግሌዎቹን ሰዎች ስጐበኝ ሰነበትሁ። ፋሲካን የዋልሁትም እዚሁ እምዬ በሰሙ ዘንድ ነው። በዚህ ዘመን ፋሲካ የዋለው ሚያዝያ 15 ቀን እንደሆነ አስታውሳለሁ።

ከዚህ በኋላ እምዬ በሰሙ ስለኔ ጉዳይ ደብዳቤ ወደ እንጦጦ ልካ ለአባቴ አስታወቀች። አባቴም ዕርቅ ማድረጋቸውን ስለገለጹና "በቶሎ ላኩት" ስላሉ ወደ እንጦጦ ለመመለስ እዘጋጅ ጀመር። የእምዬ በሰሙ ባል መምሬ ወሰን መሪ በግንቦት ወር የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን በዓል ለማክበር ወደ ደብረ ሊባኖስ ሲወርዱ እኔንም ይዘውኝ ወረዱ። ግንቦት 12 ቀን ቅዳሜ በዓሉ እጅግ ደምቆ ተከበረ። ሕዝቡም እጅግ ብዙ ነበር። የተሳላሚዎች ብዛት እንደዛሬ ሆኖ አያውቅም እየተባለ ይወራ ነበር። በእኔ አስተያየት ግን ሕዝብ የበዛበት ሌላ ምክንያት አለ። ራስ ቢትወደድ ተሰማ በ72 ዓመት ዕድሜያቸው ሚያዝያ 3 ቀን 1903 ዓ.ም. ስለሞቱ ሬሣቸው ደብረ ሊባኖስ መጥቶ ተቀብሯል። የአርባ ተዝካራቸውም ግንቦት 12 ቀን ላይ ስለዋለ ከበዓሉ ጋር ተጋጥሟል። እንግዲህ ሕዝብ የበዛው ለምጽዋት ፍለጋ ከያገሩ የተሰበሰበው ለማኝ፣ ድኻና ችግረኛ ሁሉ ስለተጨመረበት ነው እንጂ በተሳላሚዎቹ ምክንያት ብቻ አልነበረም። የተዝካሩ ድግስና ምጽዋቱ ከልክ ያለፈ ነበረ። እናታቸው ወይዘሮ ቆንጂት መንፈሳዊት ከመሆናቸው የተነሣ የልጄ ገንዘብ ለነፍሱ ይሁንለት እያሉ ምንም ሳያስቀሩ ለድግስና ለምጽዋት አዋሉት ይባላል። በጥሬ ገንዘብ ወጪ የሆነው እንኳ ሰባት መቶ ሺህ ብር ነው እያሉ ሂሳቡን ሲናገሩ ሰምቻለሁ።



## ወደ እንጦጦ ስለመመለሴ

ከበዓሉ በኋላ መምሬ ወሰን መሪ እኔን ወደ እንጦጦ ወስዶ ለአባቴ የሚያስረክብ ዘመድ ይፈልጉ ጀመር። ወዲያው አለቃ ገብረ ማርያም የተባሉትን የደብረ ሊባኖስ ካህን (ዓይነ ስውር) አገኙና ከደብዳቤ ጋር በእሳቸው እጅ ወደ እንጦጦ ላኩኝ። ከሦስት ቀን ጉዞ በኋላ እንጦጦ ደረስን። አለቃ ገብረ ማርያምም ደብዳቤውን ሰጥተው ሲያገናኙኝ ጫማ ሳምሁ። አባቴም ስመው ከመቀበል በቀር አንዳች ቍጣ ወይም ተግሣጽ አላመጡብኝም፤ ተመስገን እምላኩ።

## በእንጦጦ ሳለሁ

ከደብረ ሊባኖስ መጥቼ እንጦጦ ስደርስ አባቴ አሁንም ከዚያው ከቀድሞው ተማሪ ቤት ገብቼ ከመምህር ዐወቀ ዘንድ ቅኔ እንዳስፋፋ ፈለጉ። በዚያም ሰሞን ግንቦት 24 ቀን አዲስ አበባ ላይ ሽብር ሊሆን ነው ተብሎ ሕዝቡ በፍርሃት ዋለ። ምክንያቱም ልጅ ኢያሱና ራስ አባተ ማዶ ለማዶ ተሰላልፈው ስለነበረ ነው። ሆኖም ሽብር አልሆነም። ነገር ግን አስተማሪዬ መምህር ዐወቀ የጊዜው የጸጥታ ሁናቴ ስላሠጋቸው ወደ ዋድላ ለመግባት ይደራጁ ጀመር። ወዲያው በሰኔ ወር ከተማሪዎቻቸው መካከል ሁለት ብቻ አስከትለው ሌሊት በስውር ሄዱ። ተደብቀው በመሄዳቸው እኛ የቀረነው ተማሪዎቻቸው አዘነንባቸው ነበር።

እኔም ክረምቱን እዚያው እንጦጦ ከረምሁ። በክረምቱ ውስጥ እንጦጦ ራጉኤል ካሉት ከአለቃ ድንቂ የቅኔ አገባብ ለመቀጸል[85] ጀምሬ ነበር። ሁለት ሳምንት ያህል ተመላለስሁና ተውሁት። ምክንያቱም አባቴ ስለ ርስት ጉዳይ ጅሩ ወርደው ከርመው ስለነበረና የእንጦጦን የደብተርነት ግብር የምገብረው እኔ ስለነበርሁ ነው። በዚህ ጊዜ ቅኔ ለራሴ ብቻ ሳይሆን ለሌላም እየተለመንሁ አዘውትሬ እቀኝ ነበር። በነሐሴ ወር በፍልሰታ ውስጥ አንድ ቀን ቅኔ ስቀኝ መልአከ ፀሐይ አፈ ወርቅ (በኋላ መልአከ ፀሐይ ኤስድሮስ የተባሉት) በቅኔው ደስ ስላላቸው ወዲያው አንድ በለሴ ኩታ ሸለሙኝና ደስ አሰኙኝ። በዚህ ጊዜ ዕድሜዬ 12 ዓመት ተኩል ነበረ።

## ልጅ ኢያሱ የመድኃኔ ዓለምን ታቦት ስለ መትከላቸው

ልጅ ኢያሱ በዚህ ዓመት በክረምቱ ወራት በጦር ሚኒስትሩ በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቤት ነበሩ። በዚያም ሳሉ በሐምሌ ወር ታቦተ መድኃኔ ዓለምን ተከሉ። የተከሉበት ስፍራ በእንጦጦ ራጉኤል ደቡብ በአንድ ጉብታ

---

[85] ማጥናት::

ላይ ነው። ይህ ጉብታ አባ አየለ የተባሉ መነኩሴ የሚኖሩበት ክብ የሣር ክዳን ቤት ነበረበትና ዙሪያውን በረንዳ ተጨምሮለት መቃኞ[86] ሆኖ ተቀደሰበት። የዚህ በዓል የማኅሌቱ ምራት ለራጉኤሎች፣ ቅዳሴው ለእንጦጦ ማርያም ካህናት ስለተሰጠ በዋዜማው ወርደን ስናገለግል አደርን። በማግሥቱም ጧት አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ መጥተው አዲሱን ቤተ ክርስቲያን ባረኩ። ቀጥሎም ልጅ ኢያሱና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ መጥተው ታቦት አንግሠውና በዓሉን አክብረው ተመለሱ። በዚህ ቀን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ (ልጅ ኢያሱ ባሉበት) በአዳራሻቸው ለካህናት ግብር አድርገው ዋሉ። ግብዣውም በዚያ ቀን ለእርሳቸው ተሰጠ። ከዚህም በኋላ በለጣቂው ዓመት ጥቅምት 27 ቀን 1904 ዓ.ም. የመድኃኔ ዓለም በዓል በዚየው ቦታ እንደገና በታላቅ ክብር ተከበረ። በዚያ ቀን ስለ በዓሉ ክብር ነጋሪት ተመትቷል፣ መድፍም ተተኩሷል።



20 ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም

ልጅ ኢያሱ የመድኃኔ ዓለምን ታቦት ለመትከል የፈለጉበት ምክንያት፣ የተወለዱበት ቀን ጥር 27 1889 ዓ.ም. የመድኃኔ ዓለም ዕለት ነበርና የልደታቸው መታሰቢያ እንዲሆን በማሰብ መሆኑን ሰምቻለሁ። የክርስትና ስማቸውም ክፍለ ያዕቆብ ነው።

[86] ትልቅ ቤት ከመሠራቱ አስቀድሞ ለጊዜው ማገልገያ እንዲሆን የሚሠራ ትንሽ ቤት።

# ምዕራፍ 11

## 1904 ዓመተ ምሕረት

**ስለ ኪዳነ ምሕረት ጠበል፣ ናዝራዊና ባሕታዊ አስደንጋጭ ስብከት ስለመስበካቸው፣ የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ስለመተከሉ፣ ወደ አዲስ አበባ ስለመውረዴ፣ በአዲስ አበባ ሥላሴ ሳለሁ፣ ሥራ ለመያዝ ስለመሞከሬ**

### ስለ ኪዳነ ምሕረት ጠበል

አባ ምትኬ የተባሉ ሰው ከእንጦጦ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኝ ሸለቆ ውስጥ (አሁን ገዳመ ኪዳነ ምሕረት ከተባለው ስፍራ ላይ) ሕሙማንን የሚፈውስ ጠበል አገኘሁ ብለው ከሁለት ዓመት በፊት ተናግረው ስለነበረ፣ የእንጦጦ ማርያም ካህናት ወደዚያ ስፍራ ወርደው ጸሎት አድርሰው መስቀል ተከሉበትና ሕዝብ ይጠመቅበት ጀመር። አባ ምትኬ የእንጦጦ ማርያም ቄሰ ገበዝ የነበሩ የጐጃም ሰው ናቸው።

አባ ምትኬ ከዚያ ስፍራ ጥንት ታቦት እንደነበረበትና ጠበል መኖሩም በራእይ ተገለጸልኝ ሲሉ ተናገሩ። በእውነትም በጠበሉ ራስጌ ያለው ጉብታ ሲቆፈር የብረት መስቀልና የብረት ጽና[87] ተገኘ። ቀጥሎም የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱ ግንብ ተገኘ። ከግራኝ ወረራ በፊት በዚያ ቦታ ላይ የማርያም ቤተ ክርስቲያን ነበረበት። ደግሞም የመናገሻው መናኒ አባ ኤልያስ ወደዚህ ገዳም እየመጣ ጸሎት ያደርስ ነበር ይባላል።

ስለ አባ ኤልያስ የሰማሁትም ታሪክ ቀጥሎ ያለው ነው። ይህ ሰው በግራኝ ጊዜ የነበረና በ400 ዓመት ዕድሜው ኅዳር 6 ቀን 1874 ዓ.ም. ሞቶ መናገሻ ተራራ ላይ የተቀበረ ነው። ታሪኩም እንዲህ ሲል ይቀጥላል። አባ ኤልያስ የቤተ መንግሥት ተወላጅነት ያለው ሰው ነው። የተወለደበትም ዘመን በ15ኛው ምዕት በሦስተኛው ሩብ ላይ ነው ይባላል። ግራኝ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ በአምላክ ጸጋ ከተመረጡ ደጋግ ሰዎች ጋር በእግዚአብሔር ኃይል ተሰውሮ መናገሻ ከተራራው ላይ ቀረ። በግራኝ ጊዜና ኋላም በኦሮሞዎች ወረራ ጊዜ አንዳች ጉዳት አልደረሰበትም። ከመናገሻም ወደዚህ ገዳም (ገዳመ ኪዳነ

[87] ከሸክላ ወይም ከብረት የሚሠራ የዕጣን ማጠኛ። በቅዳሴ ጊዜ ወይም ጸሎት ሲደረስ ቄሱ መንበሩንና ሕዝቡን ያጥናል።